ተነሳ ተራመድ

የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል

፲ኛ ዕትም

ጁላይ 2017

ሲያትል

ተነሳ ተራመድ

ተነሳ ተራመድ .... ክንድህን አበርታ

ላገር ብልፅግና .... ለወገን መከታ ።

ሀ ሁ ...... ኢትዮጵያ ትቅደም

ሀ ሁ ..... ኢትዮጵያ ትቅደም ።

እንበል ሃሌ ሉያ .... ታላቅ የምስራች

ከብዙ እስር ዘመን ... ኢትዮጵያ ተፈታች ።

ኢትዮጵያችን ትቅደም ... ብለን እንገስግስ

ለትውልድ እንዲተርፍ ... የያዝነው ጥንስስ ።

ወንዞች ይገደቡ ... ይዋሉ ለልማት

በከንቱ ፈሰዋል ... ለብዙ ሺ ዓመታት ።

ይውጡ ማዕድናት ... ከአገራችብ ጥቅም

ህዝቡም ታጥቆ ይስራ በተቻለው አቅም ።

አሽብርቃ ታይታ ... በተፈጥሮ ሃብት

ተብላ እንዳልነበር ... የአፍሪካ እመቤት ።

ብለው እንዳልጠሯት ... የዳቦ ቅርጫት

እንዴት እናታችን ... ትባል እራባት ።

ይቅር ማንቀላፋት ... ይበቃል መኝታ

ይጥፋ ከአገራችን ... ድህነት በሽታ ።

ይነገር ይለፈፍ ... ይታወጅ በይፋ

አንድነት ኃይል ነው ... የርምጃችን ተስፋ ።

የናት አገራችን ... ጥቃቷን አንወድም

ህዝቧ ተበድሎ ... ማየት አንፈልግም ።

በዘር በኃይማኖት ... ልዩነት አንሻም

ይላሱ ልጆችሽ ... ኢትዮጵያችን ትቅደም ።

ከእናንተ ጋር እናለቅሳለን

እንፀልያለንም

ነፍስ ይማር !

አምናና ዘንድሮ የምንወዳቸውንና የምናከብራቸውን፣ የአየር ኃይል አባላትና ቤተሰቦቻቸውን በሞት ተነጥቀናል። "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ"፣ የሚል ሕግ ተጽፎብናልና ሳንጠግባቸው እንደመጡ ሄደውብናል። በሕይወት ዘመናቸው በገጠመኝ የተቆራኙን ድንገት ጥለውን ሲሄዱ ከእኛም ተነጥሎ አብሮአቸው የሚሄድ ነገር አለ። እናም ያጎድሉናል። የወደፊታቸውን በጉጉት ስንጠብቅ ሳይፈኩ ድንገት የተቀጠፉብን እምቡጥ አበቦች ጉዳይ ደግሞ የበለጠ ያመናል። ጨዋታቸው፣ ሳቃቸው ይናፍቀናልና ሐዘናችንን ያከብደዋል።

የተፈጥሮ ሕግ ሆኖብን ዘላለማዊነት የለም። ይህንን መቀበል ግድ ነው። መኖር የሚሉት ዕውነትም ያለውን ይዘን እንድንጓዝ ያዘናል። አናም ጽናትና ብርታቱን በቁም ላለነው፣ ጸጋ፣ በረከቱንና ምህረቱን ደግሞ ለተለዩን ሁሉ እንመኝ።

በውስጥ ገፅ

1. የመጽሔቱ መልዕክት ------------------------ ------------------------4

2. አዋሽ --- 5

3. የኰ/ሉ ጉዞ ---8

4. የአየር ኃይል ሙዚቀኛና ሻምበል ብሩ -----------------------------------13

5. ሚግ አብራሪውና የቤላሩሱ ሕይወት አድን ድራማ ---------------------- 16

6. የእናት ባለአደራ ---24

7. የጀት ኢንጂኑ ሰው --- 26

8. ያልተሳካው መፈንቅለ መንግስት በአሥመራ ----------------------------39

9. የአባቴ አሻራ ---39

ሀ. ክፍሉ ሁሴን ---39

ለ. የጄነራሉ ልጆች ---44

10. የጄነራሉ ፀሐፊ ---46

11. የሔሊኮፕተር ምርኮ ---48

12. የአዛዡ ሹፌር ---54

13. ደጀኖቹ ---56

14. From the M/tech's dossier --------------------------------------60

Contact Us @

www.formerethiopianairforce.com

unitedetaf@yahoo.com

unitedetaf@gmail.com

የመጽሔቱ መልዕክት

ተነስተናል፣ ተራምደናል

*ይህንን የሕብረት ጉዞ ከጀመርን አንድ ዓመት አለፈን ። ዓላማችን ግልፅ ነው ። **በአለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባላትንና ቤተሰብን የሚያስተሳስር ኔት ዎርክ መፍጠር ነው** ። የአምናው የእንነሳ እንራመድ ጥሪ ነበር ። ከአሰብነው ለመድረስ ይኸውና ተነስተናል ፣ ተራምደናልም ። ዓላማችን ከሩቁ ግባችን ለመድረስ ነውና እርምጃችን አይቆምም ።*

ለረዥም ጊዜ የልተገናኘንና ያልተያየን ሰዎች አምና በአካል ቶሮንቶ ከተማ ላይ ተገናኝተን ስላለፈው ተጫውተናል ። ትዝታችንን አውግተናል ። የጋራችን ቤት ስለነበረው አየር ኃይል ተወያይተናል ። ሰለወደፊቱም ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋውጠናል ።

መቼም እንደምታውቁት አንድ ጊዜ አየር ኃይል የነበረ ምንግዜም አየር ኃይል ነው ። ፈረንጆቹ (Once an Air Force always Air Force) እንደሚሉት ማለት ነው ። ይሄ ስሜት በጊዜ ርዝመት አይደበዝዝም ። በቦታ ርቀት አይወይብም ። ማንነታችን ፣ እገሌነታችን ነው ። ማነ ነህ? ምን ነበርክ? በሎ ለሚጠይቅ ሁሉ ። ይህንን አምና አይተናል ። አየር ኃይልን ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት የተሰናበቱ ሰዎች አየር ኃይል ነን ብለው ነው የተቀላቀሉን ። በዕንባ እንክብሎች ታጅበው "ተነሳ ተራመድን"ም አብረውን ዘምረዋል ።

ይህንን የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዓለም አቀፍ ሕብረትን ለመመስረት የተነሳነው የሕብረት ግንኙነታችንን ዕውን ለማድረግ ነው ። እህል-ውሃ በተለያየ የዓለም ጥግ እንዲኖር ያስገደደውን የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባልና ቤተሰቡን በአንድ መድረክ ላይ ማገናኘት ነው ጥረትና ድካሙ ። እናም አምና ከስዊዲን ፣ ከጀርመን ፣ ከአሜሪካና ከካናዳ የተለያዩ ከተሞች የመጡ የቀድሞ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባላትና ቤተሰቦቻቸው በአንድ ድንኳን ፣ በአንድ አዳራሽ ለመገናኘት ችለዋል ። በአካል ለመገኘት ያልቻሉም መልዕክታቸውን ልከው እንኳን ለዚህ አበቃን ብለዋል ።

በእርግጥ አየር ኃይልና ቤተሰቡ በየአመቱ የመነፋፈቅና የመገናኘት ፍላጐትና ባሕሉ የቆየ ነው ። አምና ላይ የተመሰረተው ታድያ ይህንኑ በጐ ባሕል የበለጠ የሚያጠናክርና የጋራና የሁላችንም ቤት ይኑረን የሚለውን ጥያቄ መሰረተ ሃሳብ ዕውን የሚያደርግ ነው ። ይሄ በጎ ግንኙነትም ባለበት አልቆመም ። አድጓል ፤ ጠንክሯልም ። ይህንን በጎ ሃሳብ የጠነሰሱ ግለሰቦች የድካማቸውን ፍሬ አይተዋል ። ለወደፊቱም ተስፋና ጉልበት ሰጥቷቸዋል ። ማሕበሩ እንደ አምናው ሁሉ ዛሬም ቀና መንገዶችን ይከተላል ። ሁሉንም የቀድሞ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባላትና ቤተሰብ እኩል የጋር ቤት እንዲኖራቸው ይጥራል ። መሰረታዊ ዕቅዱም ይኼው ነው ። ስለ አየር ኃይል ተብለው በሚታቀዱ ማናቸውም ፕሮጀክቶች ላይ ይሳተፋል ። ማሕበሩ ስለ አየር ኃይል በሚያቅደው ማንኛውም አይነት ፕሮጀክቶች ላይ ሌሎች እንዲሳተፉ ፣ ጉዳዩንም የራሳቸው እንዲያደርጉት በትህትና ይጋብዛል ።

እነሆ አምና አልፎ ለዛሬ በቅተናል ። ዛሬ አምና በነበርንበት ላይ አይደለንም ። ተነስተናል ። ተራምደናል ። ለከርሞውም ሌላ እርምጃ ጨምረን የተሻለ በታ ላይ እንገኝ ዘንድ እንበርታ !

የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዓለም አቀፍ ሕብረት

አዋሽ

ምስክር

"...አዋሽ ቡቡ በረኸኛ

የአሸዋ ዋሻ መተኛ

የበረሃ ዋናተኛ

የምደረ በዳ ብቸኛ

የዘላ'ለም መንገደኛ..." ።

ተብሎ በጸጋዬ ገብረመድሕን ሰለተገጠመለት አዋሽ ወንዝ አይደለም ልናወጋችሁ የተነሳነው ። አዋሽ ስለሚባለው ዕውቁ የአዲስ ምልምሎች መኖሪያ ቤት (ዶርሚተሪ) እንጂ።

አዋሽ ዶርሚተሪ የሚገኘው ደብረ ዘይት ሐረር ሜዳ የአየር ኃይል ቤዝ ውስጥ ነው ። ክበቡና ምግብ ቤቱ መካከል ተንጣሎ የተገነባና እስከ ሰማኒያ አዲስ ምልምሎችን በአንድነት ሊያኖር የሚችል ትልቅ የመኝታ አዳራሽም ነው። ስያሜውንም ያገኘው በዚሁ በትልቅነቱ እንደሆነ ተነግሮናል ። ከፊትለፊቱ አልፎ አልፎ አገልግሎት የሚሰጥ የመዋኛ ገንዳም ነበር ። መቼም የአየር ኃይል አባል ለመሆን ከየትምህርት ቤቱ ተመልምሎ ግቢውን የረገጠ ሁሉ ይህንን መኝታ ቤት ያውቀዋል የሚል ዕምነት አለኝ ። አብዛኛው አዲስ ምልምል ደግሞ አዋሽ ውስጥ ቢያንስ ሶስት ወር ያህል ኖሯል ።

በፈረንጆቹ ሰባዎቹ አጋማሽ ላይ ከየቦታው ተመልምለን ወደ ሐረር ሜዳ የመጣን ወጣቶች መጀመሪያ ያረፍነው አዋሽ ዶርሚተሪ ውስጥ ነው ። ወደ ስልሳ ሳንጠጋ አንቀርም ። ልንበልጥም እንችላለን ። ጊዜው እራቀና በትክክል ማስታወስ ይቸግራል ። ይሁንና በድርብርብ አልጋ ላይ ሁላችንንም አዋሽ ዋጥ አድርጎ ይዟል ። የመጣነው አዲስ አበባን ጨምሮ ከተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ነው ። ከመሃከላችን ጥቂቶቹ በዕድሜ ትንሽ ገፋ ያሉ ቢመስሉም አብዛኞቻችን ገና ጢም እንኳ አላበቀልንም ።



ለአቅመ-ዕዳም ብንደርስም ዓለማዊውን ነገር በሃሳብ ደረጃ ካልሆነ በተግባር ገና በቅጡ አላጣጣምንም ። ያው እንደምታውቁት የአዲስ ምልምልነት (የሬኩሪቲንግ) ዘመን ሰቆቃ ነው ። ላብ የሚፈስበት ። እንደ ቢላ የሚሳሉበት፣ እንደ ኔሾ የሚወቀጡበት ነው ።

በጠዋት ተነስቶ ሩጫ አለ ። ማለዳ እንቅልፍ ሳይጠግቡ ተነስቶ ጋራ ብሩን ወጥቶ መወረድ የተለመደ ነው ። ከዚያም አመዛኙን ቀን በስፖርትና በሰልፍ ልምምድ ሲናጡ መዋል ግድ ነው ። በእርግጥ ወታደራዊ የቀለም ትምህርትም ከስዓት በኋላ ክፍል ውስጥ ይሰጣል ። መቀመጫቻን ዕረፍት የሚያገኘው ታዲያ ያን ግዜ ብቻ ነው ።

የሶስቱ ወር ልምምድ ሳይጠናቀቅ ከግቢው ውልፍት የለም ። በዕረፍት ቀን እንደ ስድስት ኪሎ አንበሶች እዚያው ግቢው ውስጥ ስንጎማለል እንውላለን ። እሱም ገደብ አለው ። ወደ ጠቅላይ መምሪያ ዘር ማለት የለም ። ክበብ መግባትም ክልክል ነው ። ደጃፍ ላይ ተኮልኩለን ሙዚቃ ለማዳመጥ የምከርነበት ጊዜ አለ ። ተነሱ ተብለን እስክንባረር ድረስ ። የፕሮግራሙ ዋና ዓለማ የአካልና

የመንፈስ ጥንካሬን ለማስረጽ ይመስለኛል ። ወታደራዊ ስነ-ምግባርንም እንዲሁ ። እናም የወፈረው እስኪቀጥን ፣ የላላው እስኪጠብቅ ለሶስት ወር ይታሻል ። በዚህ ሶስት ወር ጊዜ ውስጥ እልኸኛው ይለዝባል ፣ ጉልበተኛውም አንገቱን ይደፋል ። በኛ ዘመን ታዲያ አዲስ ምልምሉ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የሚያልፈው አዋሽ ጣሪያ ስር እያደረ ነበር ። ምሽት ላይ መብራት ከጠፋ በኋላ ከአንዱ ጥግ ወደሌላው ቀልዶችን እየተቀባበለ ፣ እንኪያ ሰላምታዎችን እየወረወረ ። ሳይሰቀቅ እየሳቀ ይኖራል ።

ይን ጊዜ የዚያ ሁሉ ሰው ጸጉር ግንባር ድርስ ነበር ። ቀፈት የሚሉት ነገርም አልነበረም ። በቅርቡ ፌስ ቡክ ላይ የዚሁ የሰባ ስደስት ተቀጠሪ አባል የነበሩ ተሰባስበው ጥሩ ቀን ሲያሳልፉ የሚያሳይ ፎቶግራፍ ተለጥፎ አየሁ ። ገሚሱን በመልክ መለየት እንኳ ተሳነኝ ። ጸጉር ወደ ኋላ ሸሽቷል ። ያልሸሸውም ጥጥ መስሏል ። ቆዳ ሸብሸብ ማለት ጀምሯል ። ያም ሆኖ አሁንም የሚስቁ ፊቶችን ማየቴ አስደሰተኝ ። ይሄ እንግዲህ በሕይወት ከሌለው ፣ እንደጉም ከተበተነው መሃል ተርፎ አንድ ቦታ ላይ ለመገናኘት የበቃው ነው ። ረዥም ዕድሜና ጤና ተመኝሁላቸው ።

ወደ ነገሬ ልመለስ ።

ታዲያ አንድ ቀን እዚሁ አዋሽ ዶርሚተሪ ሆነን ምን ሆነ መሰላችሁ? የወር ደምዎዝ የተቀበልንበት ሳምንት ነው ። አርብ ምሽት ላይ አረንጓዴውን ቱታ አውልቀን ጣልንና ያለንን ለባብሰን ዘንጠን በምሽት ውልቅ አልን ። ያቺኑ የሰጡንን ሳንቲም ይዘን ። ከዚያም በአየር ወለድ አጥር በኩል አሳብረን ዋናው መሃል ከተማ "ሸቦ ጊቢ" ገባን ። አንድ ሶስት ወይም አራት የምንሆን ጓደኛሞች ነን ። የያዘናት ሳንቲም እስክታልቅ ድረስም ከአንዱ ቡና ቤት ወደ ሌላ እያልን ጂን ኦሬንጅና ግሪን ፋየር ስንጨልጥ ምሽቱን አጋመስን ። ተመልሰን ወደ ግቢ የመግባት ሃሳብ አልነበረንምና አልጋ ፍለጋ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ስንሮጥ ዓይን ውስጥ ገብተናል ። የደምዎዝ ጊዜ ነበርና ካስተማሪዎቻችን መሃከል አንዱ እንዲሁ እንደ እኛው ጥሩ ምሽት ለማሳለፍ ወደ አንዱ ቡና ቤት ጎራ ብሏል ። ሃምሳ አለቃ አለማየሁ (ቴክሱ-ነፍሱን ይማረውና) መቼም የቁራ ዓይን ያለው ሰው ነው ። በመስኮት አጮልቆ በማየት በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለይቶ አውቆናል ።

እኛ ዓለም ከዘጠኝ በላይ ሆና ያመሸንበት አደረን ። ደስ ብሎን ። የወጣንበትንም ጉዳይ ፈጽመን ። ካገኘነው ጋር ተቀቅፈን ፣ እንደ ላም እየታለብን ነጋ ። ጥዋት ገንዘባችንንም ጉልበታችንንም አሟጠን ጨረስን ጆሯችንን እንኳ መሸከም አቅቶን እንደ ላም ጆሮ ወደ ታች ጥለን በወጣንበት መንገድ ወደ ግቢያችን ገባን ። አዋሽ ስንደርስ በር ላይ የተቀበሉን ታዲያ ያዘኑ ፊቶች ነበሩ ።

ለካስ ሃምሳ አለቃ አለማየሁ ተኝቶ አላደረም ። ወዲያውኑ ሳምንት ሃላፊዎች ጋ ደውሎ መኪና ይጠይቅና ሌሎች አሰተማሪዎችን ከየቤታቸው ቀስቅሶ ወድቅት ላይ አዋሽ ዶርሚተሪ ከች ብሏል ። ተኝቶ እንቅልፉን መለጠጠ የጀመረው አዲስ ምልምልም ከተኛበት ተቀስቅሶ እንዲወጣ ይታዘዝና ሜዳ ላይ ተሰልፎ ቆጠራ ይጀመራል ። እኛን ጨምሮ ወደ አስር የሚሆን አዲስ ምልምል ቆጠራው ላይ አልተገኛም ። ጉድ ተባለ ። ያን ጊዜ አለም ቀውጢ ሆነች ። ለካስ ሸቦ ግቢ ያልሄደው አዲስ ምልምል ወደ አዲስ አበባ ጭልጥ ብሏል ።

"ምነው ሃዘን ተቀመጣችሁ?"፣ ብለን የጠየቅናቸው ጓደኞቻችን ወዲያው ሳምንት ሃላፊ ሄደን ሪፖርት እንድናደርግ መርዶ አረዱን ። ሳምንት ሃላፊው ቢሮ ስንደርስ የሳምንት ሃላፊው መቶ አለቃ በስላቅ ተቀበለን ። ጥፋት አጥፍተናል ። ሕግ ጥሰናል ። በተጠንቀቅ ቆመን አዳመጥነው ። ምሽት ላይ የነበረን ወኔና ጉርምስና እንደ ጎማ ለመተንፈስ ጊዜ አልወሰደበትም ። ወዲያው እንደበግ እየተነዳን ወደ አየር ኃይል ፖሊስ ተወሰድን ። ቅዳሜና እሑድን ቀንቀን እንጨት ለኤይር ፖሊስ ምግብ ቤት እየፈለጥን ፣ ምሽቱን ደግሞ አራት በአራት በሆነች ጠባብ ክፍል ውስጥ መሬት ላይ እየተኛን ሁለት ለሊት አሳለፍን ። ከእንጨት ፈለጣው በኋላም ፑሻፕ እንሰራ ነበር ። ያም ቅጣት መሆኑ ነው ።

ያ እስር ቤት አሁንም አገልግሎት ላይ እነደአለ ሰምቻለሁ ። እንዲያውም ደረጃው ከፍ ብሎ ሰው የማይደርስበት የሚስጥር እስር ቤት ሆኗል ይባላል ።

የት እንደደረሱ አይታወቅም የሚባሉ የፖለቲካ እስረኞች በጥብቅ የሚጠበቁበት እስር ቤት እንደሆነም ይነገራል ። ያን ጊዜ እስር ቤቱን የሚጠብቁ ፖሊሶች ወዳጆቻችን ሰለነበሩ ብዙአይጨክኑብንም ። የዛሬውንአላውቅም ። የምንቀጣውም በማንነታችን ሳይሆን በጥፋታችን ነበር ። ዛሬ በአሳሪውና በታሳሪው መሃከል ያለው ግንኙነት እንደድሮው ይሆናል የሚል ግምት የለኝም ።አዋሽስ እሁንም ይኖር ይሆን? ዛሬስ እዚያ ዶርሚተሪ ውስጥ የሚያድረው ሠራዊት ያኔ እንደነበረው ሁሉ አንድ ቋንቋ ፣

አንድ መንፈስ ይኖረው ይሆን? አንድ አይነት መዝሙርስ ይዘምር ይሆን?

እንደ ጀመርነው ለመጨረስ ይህንን የጸጋዬ ገብረመድሕንን ግጥም ጀባ ልበላችሁ ።

"...እስከመቼ ይሆን አዋሽ?...ወዝክን አሸዋ ሲውጥህ

ደምኽን በርሃ ሲመጥህ

ዘለዓለም ሲመዘምዝህ

መቼ ይሆን በቃኝ እምትል ፣ መቼ ይሆን በቃኝ የሚልህ?

ያሰንብተን ። እስቲ እናንተም ትዝታችሁን ጻፉ ።

---------////----------

ማ/ቴክ በላይ በዳዳ በአብራካቸው ክፋይ የሚወሱ የአየር ኃይሉ አንጋፋ ሙያተኛ

የኮሎኔሉ ጉዞ

ከስሬ ወለጋ እስከ ሎስ አንጀለስ አሜሪካ

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

አቅጣጫ ጠፍቶት መንደራቸው ላይ ያንጃብብ የነበረውን ትንሽ አውሮፕላን ተከትለው መሮጥ የጀመሩት ገና በተወለዱ በስምንት ዓመታቸው ገደማ ነበር። አውሮፕላኑ መሬት አርፎ የቴሌ ስልክ ማዞሪያ የት እንደሚገኝ ጠይቆ ስልክ የደወለበትን ምክንያት የተረዱት በኋላ ነው ። ይህ የሬዲዮ መገናኛ ያልነበረው ትንሽ የአየር ኃይል አውሮፕላን የመጀመሪያ ገጠመኛቸው መሆኑ ነው ። አቪዬሽንን በተመለከተ ። የዚያን ቀን ገጠመኝ የፈጠረባቸው ሰሜት ግን አብሮአቸው እስከ መጨረሻው ዘለቀ።

የልጅነት ጓደኛቸው በፈቃዱ ታምራትም አንዱ ሌላው ምክንያት ነበር። ተወልደው ካደጉባትና አፍ ከፈቱባት ስሬ ከተማ አውጥቶ ወደ ሐረር ሜዳ ደብረዘይት ወስዶ ላስቀራቸው ጉዳይ ። ስለ አውሮፕላን በረራ መሰረታዊ ሕጎች ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ገልጦ ያሳያቸው እሱ ነው ። በስዕል የተደገፈው ትንሽ መጽሐፍ ሰለ አውሮፕላን በረራ አእምሮአቸው ውስጥ ለዘላለሙ አትሞት ያስቀረው ነገር አለ። ይህ የሆነው ነቀምቴ አንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳሉ ነው ።

ስሬ ከነቀምቴ በግምት አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ትልቅ ሰው ያበረከተች ትንሽ መንደር ናት። እሳቸውም ከተማዋም የተወለዱት በአንድ ዓመት በ1937 ዓመት ምሕረት ላይ ነው ። አባታቸው አቶ ከበደ እና እናታቸው ወ/ሮ አማረች ከሸዋ ክፍለ ሃገር የመጡ የጉራጌ ብሐረሰብ አባላት ናቸው ። እህል-ውሃ የሚሉት ነገር አለ አይደል?

ወይዘሮ አማረች ሁለተኛ ሚስት መሆናቸው ነው ለአቶ ከበደ። ቀደም ብለው ከሌላ ሶስት ወልደዋል። ልጃቸው ፣ የወደፊቱ የአየር ኃይል አብራሪ አፍ የፈቱት በኦሮምኛ ቋንቋ ነው ። አየር ኃይል ከገቡ በኋላ አብረዋቸው ከመጡት የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ጋር በኦሮምኛ ሲያወሩ የሰሙ የዛን ጊዜ የኮርስ ባልደረባዎቻቸው ግን የኦሮሞ ተወላጅ አድርገው ይወስዷቸው ነበር።

ገና በለጋ ዕድሜያቸው የተጠናወታቸው የማወቅ ጉጉት አለ። አብሮአቸው ሸምግሏል። አባታቸው እንኮኮ እያሉ ትምህርት ቤት ይወስዷቸዋል። "ተማር ልጄ…"፣ ከሚል መልዕክት ጋር። ስሬ ከሶስተኛ ክፍል በላይ ማስተማር አትችልም ነበርና አራተኛ ክፍል

ኰ/ል ብርሃኑ ከበደ

ገብተው ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ነቀምቴ ቤተሰባቸውን ጥለው ለመሄድ ይገደዳሉ። ያን ጊዜ ገና አስር አልደፈኑም ።

አባታቸው ነቀምቴ ወስደው ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በደባልነት የሚኖሩበትን ሁኔታ አመቻችተው ወደ ስሬ ይመለሳሉ ። በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰው ናቸውና ሰነባብተው ልጃቸውን ለማላመድ አልቻሉም ። እሳቸውም ሃላፊነት ወስደው እራሳቸውን ማስተዳደር የጀመሩት ያን ጊዜ ነው ።

ኮሎኔል ብርሃኑ ከበደ ይባላሉ ።አብዛኛዎቻችሁ አታውቋቸውም የሚል ግምት የለንም ። እሳቸው የሚያውቁትን ያህል ግን ብዙዎቻችን ስለ ኢትዮጲያ አየር ኃይል አናውቅም ። በዚህ ላይ ሰውዬው እራሳቸው ያልተነገረ ታሪክ አላቸው ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ታዲያ ሰለ አየር ኃይልም ስለራሳቸውም ኮሎኔሉ እራሳቸው እንዲነግሩን ነው ።

የአየር ኃይል አባል ሆኖ ለመመልመል የተሻለ ዕድል የነበረው አዲስ አበባ ውስጥ ነበርና ኮሎኔል ብርሃኑ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ኮከበጽባሕ ትምህርት ቤት ገብተው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን መከታተል ይጀምራሉ ። እንዳሰቡትም ይሆንና በፈረንጆቹ አቆጣጠር 1961 የመግቢያ ፈተናውን አልፈው ከሌሎች ሁለት መቶ ከሚሆኑ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር ለሕክምና ምርመራ ደብረዘይት ሐረር ሜዳ አየር ኃይል ጣቢያ ይገባሉ ። በምርመራው አርባ ስምንት ተማሪዎች ብቻ ብቁ ሆነው ሲገኙ ሌሎቹ ወደ መጡበት ይመለሳሉ። ኮሎኔል ብርሃኑ ከአርባ ስምንቶቹ ውስጥ አንዱ ሆነው የ12ኛ አብራሪዎች ኮርስ ተካፋይ ለመሆን የአዲስ ምልምል ትምህርት ቤት ውስጥ ይገባሉ ።

መሰረታዊ የውትድርና ትምህርትን ከበረራ ስልጠና ጋር ያዛመዱ የቀለም ትምህርቶችን ወስደው ከአራት ወራት በኋላ የአየር

ወለድ ስልጠና እንዲወስዱ ይደረጋል ። ይህ ስልጠና በኢትዮጲያ አየር ኃይል የአብራሪዎች ስልጠና ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው መሆኑ ነው ። የቅደመ ዝግጅቱ ስልጠና ተጠናቆ በጃንጥላ መሬት ከታረፈ በኋላ በፍጥነት ከጃንጥላው የመላቀቅና ጃንጥላውን የመጠቅለል የሙከራ ትምህርት ጠንከራ ነፋስ ባለበት በዱከም ሜዳ ላይ እንዲደረግ ይወሰናል። እንደአጋጣሚ ሆኖ ግን አንድ ከፍተኛ መኮንን በዚያው ሰሞን በዚህ ልምምድ ላይ እንዳሉ በንፋስ ለረዥም ርቀት ተጎትተው የአካል ጉዳት ሰለደረሰባቸው ፕሮግራሙ ተሰርዞ የአየር ወለድ ስልጠናው ከአውሮፕላን መዝለልን ሳይጨምር ይጠናቀቃል ።

ከዚህ በኋላ ነበር የበረራ ትምህርቱ ለአርባ ስምንቱ ተማሪዎች መሰጠት የተጀመረው ። በ1961 ዓመት ምህርት ሐምሌ ወር ላይ ።

ተማሪዎቹ በሁለት ቡድን ተከፍለው አንዱ ቡድን ጥዋት በረራ ሲማር ሌላኛው የቀለም ትምህርት ክፍል ውስጥ ይወስዳል። በፈረቃ ማለት ነው ።



ከ1950ዎቹ ጀምሮ አየር ኃይሉ ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያውያኖች ሲካሄድ

በ1961 ዓ.ም አየር ኃይል በተቋቋመ በ17 ዓመት ሙሉ በሙሉ ይመራ የነበረው በኢትዮጵያውያን ነው ። አብራሪዎችም ሆኑ የልዩልዩ ሙያ ዘርፍ ባለሞያዎች በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያኖች ነበሩ ። ይልቁንም በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ በአሜሪካን አየር ኃይል የሰለጠኑ ጄት አብራሪዎች ወደ ሃገር ቤት ስለተመለሱ የ12ኛው ኮርስ ተማሪዎች ስልጠና በሐምሌ ወር ላይ ሲጀመር እነ ጄኔራል አምሐ ደስታ ፣ ጄነራል ኃይለሚካኤል ብሩና ሌሎችም በበረራ መምህርነት ተመድበው አዲስ በተዘጋጀ ካሪኩለም መሰረት ስልጠናው መካሄድ ጀመረ።

አርባ ስምንት ዕጩ መኮንኖች በሳብ ሳፊር የማሰልጠኛ አውሮፕላን ላይ የበረራ ትምህርት ጀምረው ሃያዎቹ ለመመረቅ ሲደርሱ በሚቀጥለው አውሮፕላን ላይ በቂ ቦታ የለም ተብሎ ሶስቱ ሲሰናበቱ ሁለቱ ወደ ምድር ጦር አቪዬሽን ይላካሉ። የቀሩት አስራ አምስት በራሪዎች በቲ-25ኤ ላይ ተከታታይ ስልጠና ለማግኘት ልሰድስት ወር (100 ሰዓት) 2ኛው አጥቂ ክንፍ አስመራ አየር ኃይል ጣቢያ ይላካሉ። በዚህ ሰልጠና ወቅት ሶስት አብራሪዎች በችሎታ ማነስ ሲሰናበቱ አስራ ሁለቱ ኮርሱን በሚገባ አጠናቀዋል።

ኮሎኔል ብርሃኑ ከሌላ ሁለት አብራሪዎች ማለትም ከፈቃዱ ታምራትና ኮሎኔል ብርሃኑ ውቤነህ ጋር ተመርጠው የበረራ ኮርስ አስተማሪነት ኮርስ ሲጀምሩ የተቀሩት ዘጠኙ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በተገኙ ቲ-28 ዲ ካውንተር ኢንሰርጀንሲ አውሮፕላኖች ላይ ተመድበው ስልጠና እንዲወስዱ ተደረገ።

የአስተማሪነት ኮርሱ ከተጠናቀቀ በኋላ ኮሎኔል ብርሃኑ ከበደና ብርሃኑ ውቤነህ እዚያው በተመረቁበት ትምህርት ቤት አስተማሪ ሆነው ሰርተዋል። በዚህ ጊዜ የአየር ኃይል የበረራ ትምህርት

ቤት በአዲስ መልክ ተዋቅሮ የመጀመሪያው ሰልጣኞች በሳፊር መቶ ሰዓት፣ በቲ-28ኤ መቶ ሰዓት በአጠቃላይ ከሁለት መቶ የስልጠና ሰዓት በኋላ የበረራ ክንፍና ዲፕሎማ አግኝተው እንዲመረቁ ሆኗል።

ኮሎኔል ብርሃኑ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በአስተማሪዎች አስተማሪነት ላይ ለዓመታት ከሰሩ በኋላ የጄት ስልጠና በቲ-33 ላይ ወስደው በ1969 5ኛ ተዋጊ (ኤፍ-5) ስኳድሮን ተመድበው በአብራሪነት፣በአስተማሪነት፣በትምህርትና የዘመቻ መኮንንነት ካገለገሉ በኋላ የትምህርት ዕድል አግኝተው የሕዝብ አስተዳደር ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይገባሉ ።

በ1974 ከትምህርት ቤት ተመልሰው የኢንስትሩመንት በረራ በኤፍ5-ቢ ላይ አድርገው ለማረፍ ሲቃረቡ ማረፊያ ሜዳው ላይ በአጋጠማቸው አደጋ እግራቸው ላይ ጉዳት ደርሶ በሕይወት ሲተርፉ ከፊት መቀመጫ ላይ ሆነው አብረዋቸው ይበሩ የነበሩት ሻለቃ እስጢፋኖስ መኮንን ግን የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል። ካንድ ዓመት ሕክምና በኋላ በአየር ኃይል ዘመቻ መምሪያ የትምህርት ዋና ክፍል ውስጥ የጄኔራል አምሐ ደስታ ምክትል ሆነው ሲሰሩ በተጨማሪም የኤፍ-5 አስተማሪ ሆነው አገልግለዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ እንዳሉ በ1976 አሜሪካ ተልከው በአሜሪካን አየር ኃይል ዩኒቨርስቲ ዕዝና ስታፍ ኮሌጅ ተምረው ተመርቀዋል።

በዚሁ ጊዜ ነበር ሶስት ጉልቻ የመሰረቱት ። ዛሬም በትዳር አብረዋቸው ያሉትን ወይዘሮ አማረች ታፈሰን ቀድሞም ኢትዮጲያ ያውቋቸው ነበር ። እሳቸውም ለትምህርት አሜሪካ ሄደው ይገናኛሉ። ከዚያ በኋላ ሌላ ጊዜ ማባከን አልፈለጉም። ያን ጊዜ የመሰረቱት ትዳር ተባርኮ ይኸውና ዛሬ ከአርባ ዓመት

ጋብቻ በኋላ ለአምስት ልጆችና ለአራት የልጅ ልጆች በርከት በቅተዋል።

ኮሎኔሉ ወደ ሃገር ቤት ተመልሰው የገቡት በ1977 አጋማሽ ላይ ነው። እዚያው ቆይተው ትምህርታቸውን የመቀጠል ዕድልና ፍላጎቱ ቢኖርም ሁኔታዎች አልፈቀዱም ።

ሃገር ቤት እንደተመለሱ 5ኛው ተዋጊ ስኳድሮን 7ኛ ተዋጊ ተብሎ አስመራ 2ኛው አየር ምድብ ስር ተዋቅሮ ስለነበር የዚህ ስኳድሮን አዛዥ ሆነው ይመደባሉ ። እንደሚያስታውሱት ከሆነ ጊዜው ጥሩ አልነበረም ። ብዙ ከተሞች በጠላት እጅ ወድቀዋል ። ጦሩም ተስፋ የቆረጠና የተበታተና ሆኖ ነበር ያገኙት ። አስመራ ለሊቱን በጥይት ተኩስ ስትናጥ ታድራለች ። ማን እንደሚተኩስ፣ ከየት እንደሚተኮስ እንኳን በቅጡ የማይታወቅበት ግዜ ነበር ። በዚህ ምስቅልቅል ውስጥ ግን አየር ኃይል የሚቻለውን ለማድረግ ጥሯል።

ሌላው ኮሎኔሉ በዚሁ አካባቢ የሚያስታውሱት ነገር ደርግ ከአሜሪካ ገዝቷቸው ነበር ሰለተባሉት አውሮፕላኖች ነው ። የሆነው እንዲህ ነው ።

ጊዚያዊ ወታደራዊው መንግስት የጦር መሳሪያ ከአሜሪካ እንዲገዛ ሲፈቅድ አየር ኃይል 130 ሚሊዮን ዶላር ከመንግስት ይመደብለታል። ከዚህ ገንዘብ ውስጥ 100 ሚሊዮን ዶላር ለ16 ኤፍ-5 ኤ፣ 2 ቲፒሲ 43ዲ እና ለአምስት ኤፍ 5 አብራሪዎች እንዲሁም በዛ ያለ ቁጥር ላላቸው ትምህርት ላይ ለነበሩ አብራሪዎች በቲ-38 ላይ በአሜሪካ አየር ኃይል ለማሰልጠን ይከፈላል። የቀረው ገንዘብ ሳይላክ ይቅር እንጂ ለ2 ሲ-130 ይመደባል። ቀሪዎቹ 8ኤፍ-5ኢ ተዋጊ አውሮፕላኖች ይመጣሉ ተብሎ ሲጠበቅ የአሜሪካን መንግስት ግዢውን እንዲቋረጥ ያደርጋል። ይህ ውሳኔ ከአሜሪካን መንግስት ጋር ያለንን ግንኙነት ስለአበላሸው የጦር መሳሪያዎቻችን የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያጡ ሆነ።

የሱማሌ ጦርነት መጀመሩ እንደማይቀር በመንግስት ደረጃ ሰለታመነ መንግስት መሳሪያ ፍለጋ ፊቱን ወደ ሶቪዬት ሕብረት ለመመለስ ይገደዳል። በዚሁ ምክንያት ሰኔ 1977 ላይ የኢትዮጲያ መንግስት ከሶቪዬት መንግስት ጋር የወዳጅነት ስምምነት ይፈራረምና የጦር መሳሪያዎችን ከሶቪዬት ሕብረት የሚገኝበት መንገድ ይቀየሳል። በዚሁ መሰረት ግዳጅ ላይና ውጭ ሃገር በትምህርት ላይ የነበሩትን የአየር ኃይል አብራሪዎች አሰባስቦ ለስልጠና ወደ ሶቪዬት ሕብረት መላክ አስፈላጊ ሆነ።

በሐምሌ ወር የሶማሌ ጦር ድንበር ሰብሮ ወደ ኢትዮጲያ ሲገባ አየር ኃይል ከ7ኛው ስኳድሮን ሶስት ቋሚ አብራሪዎችን ይዞ ከአስመራ ወደ ደብረዘይት ይገባና ቢሮ ውስጥ ያገለግሉ የነበሩ ከፍተኛ መኮንኖችን ጨምሮ ለጦርነት ይሰለፋል።



ኰ/ል ብርሃኑ ከF-5 አውሮፕላናቸው ጋር

ኮሎኔል ብርሃኑ በዚህ ጦርነት ሁለት ጊዜ አደጋ ደርሶባቸዋል። የመጀመሪያው ጎዴ ላይ ነበር ። በጃንጥላ ከዘለሉ በኋላ ጠላት እጅ እንዳይወድቁ በላንድሮቨር በሮ የደረሰላቸውን ሰው አሁንም ያስታውሳሉ። ሻለቃ አክሊሉ የሚባል የጎዴ ጣቢያ አዛዥ ነው ። ሁለተኛው አደጋ የደረሰው ከድሬደዋ በሰተምስራቅ ላይ ነው ። የሶማሌ ጦር ከፍተኛ ክምችት ድንገት ተገኘ ተብሎ ድሬደዋ የነበሩ አውሮፕላኖች በሙሉ ለማጥቃት አየር ላይ ውለዋል። ያ አልበቃ ብሎ ግን እሳቸውና ጄኔራል ተስፉ ደስታ ከደበረዘይት ተነስተው ለተጨማሪ ዕርዳታ ወደ ድሬደዋ ይበራሉ ።

ኢላማው ላይ ቀድመው የደረሱት አውሮፕላኖች ብዙ ስለነበሩ ከሩቅ ከፍ ብለው እየዞሩ ወደ ኢላማው ውስጥ ለመግባት ሲጠባበቁ አውሮፕላናቸው በ37 ሚሜ የመድፍ ጥይት አፍንጫው ላይ ይመታል። በጥቃቱ የአውሮፕላኑ የፊት እግር ተገንጥሎ ሲወድቅ ስብርባሪው የግራ ሞተር ውስጥ ገብቶ ሞተሩን ያጠፋዋል። በአንድ ሞተር ለማረፍ ወደ ድሬደዋ ሲቃረቡ ከሶስቱ እግሮች አንዱ ብቻ ይዘረጋል። ሰለዚህም በዣንጥላ መወረዱ ግድ ይሆንና ቁልቋልና ሰንሰል ላይ ያርፋሉ። ከዚያ ሰንሰል ላይ ባንድ እጃ አንስቶ ሄሊኮፕተር ውስጥ ያስገባቸውን ወታደር ጥንካሬ ዛሬም ያደንቃሉ።

የሶማሌ ጦርነት በድል ከጠናቀቀ በኋላ ትራንስፖርት ስኳድሮን ውስጥ በራሪ ለመሆን አንቶኖቭ 12 ላይ ለመሰልጠን ለስድስት ወራት ራሺያ ተልከዋል። ሰልጥነው ከተመለሱ በኋላ ለአጭር ጊዜ እንደተደራቢ ስራ ቢበሩም መደበኛ ስራቸው የአየር ኃይል የዕቅድና ፕሮግራም ኃላፊ መሆን ነበር። እዚያ በቆዩበት የአራት ዓመት የአገልግሎት ዘመን የፈጸሙት ብዙ ነው። ከባልደረቦቻቸው ከኮሎኔል ተሾመ አበበ፣ ከሻለቃ ወልደየስ ሞላ፣ ከማስተር ቴክኒሻን ሙሉጌታና ከሌሎች ጋር ሆነው የሰሩት ስራና ያስገኙት ውጤት ያስደስታቸዋል።

ኤፍ-86 ተዋጊ ጀት አውሮፕላን

በታው ብዙ ጥናቶችና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች የሚቀርቡበት ክፍል በመሆኑ ጥሩ ጸሐፊ ያስፈልገው ነበር። ለዚህ ተመርጠው ይሰሩ የነበሩት ወይዘሮ እሰከዳር ከበደ ነበሩ። ወይዘሮ እስከዳር ለስራቸው ይሰጡት በነበረው ቅድሚያ የኮሎኔሉን አድናቆት አትርፈዋል። አንድ ጊዜ በወሊድ ምክንያት ፈቃድ ከመውሰዳቸው ሌላ የዓመት ዕረፍታቸውን ተጠቅመው እንደማያዋቁ ነበር ኮሎኔሉ የሚያስታውሱት።

ኮሎኔል ብርሃኑ ክፍላቸው በዚህ ወቅት ከሰራቸው ስራዎች መሃከል አንዳንዶቹ በአየር ኃይል ውስጥ መሰረታዊ ለውጦችን አምጥተዋል። የሶቪዬት ሕብረት መልዕክተኞችን ወደ ኢትዮጲያ እንዲመጡ በማድረግ የከፍተኛ አውሮፕላን ጥገና ማዕከል እንዲቋቋም አሳምነው፣ ድርድርም ተደርጎ 400 ሚሊዮን ሩብል (በዚያን ጊዜ ምንዛሪ 500 ዶላር) ወጪ ተደርጎ ስራው እንዲጀመር አድርገዋል። ይሄ በመከላከያ ደረጃ ሊፈጸም ያልቻለ ጉዳይ ነበር። ዛሬም ይሄ ደጀን ተብሎ በአየር ኃይል ውስጥ ትልቅ ስራ የሚሰራበት ድርጅት ሆኗል። ሕንድ ሃገርም በመሄድ የሰፕላይ ስራአቱ እኛ ቀደም ሲል በምንጠቀምበት መንገድ ሆኖ እንዲዘረጋ አድርገዋል።

አየር መከላከያ በአጣዳፊ እንዲቋቋም የተደርገ ድርጅት ሰለነበር አሰራሩ ከአየር ኃይል ጋር እንዲጣጣም 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁና መልቀቂያ ፈተናውን ያለፉትን ዩኒቨርስቲ እንዲገቡ፣ ከ10ኛ ክፍል በላይ የሆኑ ወታደሮችን ደግሞ አየር ኃይል የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች የኤሌክትሮ ሜካኒክስ ኮርስ ውስጥ ገብተው እንዲሰለጥኑና ሲመረቁ በሕንድ አየር ኃይል መንገድ ቴክኒሻን ሆነው እንዲያገለግሉ መንገድ አመቻችተዋል።

በሶቪዬት ሕብረት የበረራ ትምህርት ችግር ያለበት መሆኑ ሲታወቅ እዚያ ሰልጥነው የሚመለሱትን ሃገር ውስጥ ለማስተማርና በተለይም የራሳችንን የበረራ ትምህርት ቤቶች እንደገና ማዋቀር ስላስፈለገ ተገቢውን ጥናት በማድረግ ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ደረጃ ስልጠና የሚሆን፣ ዋጋውም ተመጣጣኝ የሆነ አውሮፕላን ለመግዛት የረዥም ጊዜ ብድር የሚገኝበትን መንገድ አጥንተው አየር ኃይል እስከዛሬም የሚጠቀምበትን ኤስ ኤፍ -260 ከጣሊያን ኩባንያ ተገዝተው እንዲገቡ አድርገዋል።

አየር ኃይልን እንደገና ለማቋቋም ከሶቪዬት የተረከብነውን የጦር መሳሪያ ኢንቬንቶሪ በማስደረግ ለመረጃ አግልግሎት የሚውል የቅኝት ቪዲዮ በረል ታይም የሚያሳይ ካሜራ ገዝቶ አውሮፕላን ላይ በመግጠምና ሌላም በገንዝብ ዕጦት ሳይፈጸሙ የቀሩ ጥናቶችን ፈጽመዋል።

ሌላው የአየር ኃይልን የገንዘብ ፍላጎት ለማሟላት ያለጥቅም የቆሙ ኤፍ- 5ችን ከኢራን መንግስት ጋር ተደራድረው ገንዘቡ እንደታሰበው ለአየር ኃይል ባይሰጥም በ15ሚሊዮን ዶላር ሸጠው ለመንግስት ገቢ አስገኝተዋል።

ኮሎኔል ብርሃኑ ወደ አየር መንገድ የተዛወሩት በፍላጎታቸው ነው። በቃኝ ብለው። መጨረሻ ላይ አየር ኃይልን ያገለገሉት ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ሆነው ነው። ለአየር ኃይሉ የሰጡት አገለግሎት እጅግ ብዙ ነው። ከበረራው ውጪ። አየር ኃይልን ወክለው ከውጭ ድርጅቶች ጋር በብዙ ጉዳዮች ላይ ተደራድረዋል።

አየር መንገድ እያሉ ጦርነቱ መጨረሻ ላይ ኤል-100 ይዘው ለስራ ወደ አስመራ ሄደው እንዳረፉ አውሮፕላናቸው ተመቶ ከሞት ይተርፋሉ። ይሁን እንጂ ስብርባሪው ሰውነታቸው ውስጥ ገብቶ ሰለነበረ ጉዳት ይደርስባቸዋል። እናም ለሕክምና አየር መንገዱ ጀርመን ይልካቸዋል። ሕክምና ላይ እንዳሉ ኢሕአድግ አዲስ አበባ ይገባል። እዚያው የአሜሪካ ኤምባሲ ቪዛ አሰውጥተው ወደ አሜሪካ ያቀናሉ። ለማንኛውም በሚል። ሁኔታዎች ሲረጋጉ ግን ወደ ኢትዮጲያ ተመልሰው ስራቸውን ይቀጥላሉ። ስራቸው ላይ ትንሽ እንደቆዩ ነው የታሰሩት። አያማርሩም። ሽንፈት ያመጣብን ዕዳ ነው የሚሉት።

አየር ኃይል ከሚያውቃቸው በላይ እሳቸው አየር ኃይልን ያውቁታል። ለድርጅቱ ያላቸው ፍቅርና አክብሮትም የመጣው ከዚሁ ነው። ተማሪ ሆነው ለሕይወታቸው አስተማሪዎቻቸውን ተማምነው በረዋል። አስተማሪ ሆነው ለተማሪዎቻቸው

ሕይወት ሃላፊነት ወስደው በረዋል። ዊንግ ማን ሆነው እሳቸውን ተከትለው ደመና ውስጥ ለሚገቡ ሁሉ ዋስትና ሆነዋል። እሳቸውም ዊንግ ማን የሆኑትን ተከትለው ያለስጋት ሰማይ ላይ ውለዋል። ይህ ሁሉ የሚናገረው ዕምነት በሠራዊቱ ውስጥ እንደነበረ ነው። ፈረንጆቹ ኤስፕሪት ዴ ኮር እንደሚሉት ማለት ነው። በአዛዥና በታዛዥ መሃከል የጓደኛና የወንድም አይነት ግንኙነት ነበር አየር ኃይል ውስጥ ።

ከፊትህም፣ ከጀርባህም፣ ከጎንህም አለሁልህ በሚል ሠራዊት ውስጥ ተምረዋል። አስተምረዋል። ሰልጥነዋል። አሰልጥነዋል። እርስ በርሱ በሚተማመን፣ አንተ ማን ነህ? ከየትስ መጣህ? በማይል፣ ችሎታ ብቻ በሚፈለግበት ቤት ውስጥ አድገው ለቁምነገር በቅተዋል። በዚህም የሚሰማቸው ኩራት አለ። ይህንን ባሕል ለቀጠለው ትውልድ ማስተላለፍ አለመቻላችን ግን የእግር እሳት ሆኖባቸዋል። በእጅጉ ይቆጫሉ። መሸነፋችን ያንገበግባቸዋል። ዛሬ በያለንበት ለምናማርረው ነገር ሁሉ ምክንያቱ መሸነፋችን መሆኑንም ያምናሉ። በቅጡ አለመሸነፋችንም ያናድዳቸዋል። የመሩን ሰዎች በየትም ዓለም እንደተደረገው ሁሉ በወጉ እጃቸውን ለመስጠት እንኳን አልተደራደሩም። ያን አድርገው ቢሆን ኖሮ ያ በዕዛቸው ስር የነበረ ሠራዊት እንደአልባሌ የትም ተበትኖ አይቀርም ነበር ባይ ናቸው።

እሳቸው የሚያውቁት አየር ኃይል ዘመናዊና የሰለጠነ ነበር። በዘፈቀደ ሳይሆን በሬጉሌሽንና በማንዋል የሚተዳደር ተቋም። የማሰልጠኛ ተቋሞቹ ከሰለጠነው ዓለም ጋር ዕኩያ እንደነበሩ ነው የሚያውቁት። ለበረራ ስልጠና ከገቡ ተማሪዎች መሃከል በአማካይ የሚያስመረቀው ከ10 እስከ 15 በመቶ ያህሉን በቻ ነበር። መርሆው ብዛት ሳይሆን ጥራት ሰለነበረ። በሌላው የሰለጠነ ዓለም ያ ቁጥር 20 በመቶ ነው።

የቀድሞው የኢትዮጲያ አየር ኃይል ያለማቋረጥ አስራ ሰባት ዓመት ተዋግቷል። በእሳቸው ግምት ይሄ የዓለም ሪኮርድ ነው። ያ ታዲያ በእርግጥ በተለመደው መንገድ የማያቋርጥ ተከታታይ ስልጠናዎችን እንዳያከናውን እንቅፋት ሆኖበታል። ይህም ሆኖ ግን ለኮሎኔል ብርሃኑ፣ ብዙ የሃገር ውስጥም ይሁን የውጬ ሃገር ተቋሞችን የማወቅ ዕድል ለገጠማቸው ሰው የቀደሞው የኢትዮጲያ አየር ኃይል ተወዳዳሪ የሌለው ብርቅና ድንቅ ነው። በሌላ የሃገሪቱ ሲቪል ተቋማት ውስጥ የዘመናዊ አሰራርን መሰረት የጣሉ ብዙ ሙያተኞችን ያፈራ የሃገራችን ትልቅ ሃብት።

እንደ እሳቸው ዛሬ በውጬ ለመኖር ለተገደዱ የአየር ኃይል አባላት የሚሉትን ማወቅ ፈልገን ጠየቅናቸው። መገናኘቱን፣ መጠያየቁን፣ መረዳዳቱን ምን ያህል እንደሚወዱት ነው የነገሩን። አሁን በሚያዩት እንቅስቃሴ በጣም ደስተኛ ናቸው። ከመሰነባበታችን በፊት እሳቸውም ጥያቄ አቀረቡልን።

"መቼና የት ነው የምትሰባሰቡት በዚህ ዓመት?"

"ሲያትል"፣ አልናቸው።

"እመጣለሁ"፣ አሉን። ቁርጥ ያለ ቃል ነበር። እስከዚያው እግዛብሔር በሰላምና በጤና ያቆይልን ዘንድ ጸሎታችን ነው ።

--------------///-------------

የአየር ኃይል ሙዚቃኛና

ሻምበል ብሩ

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

መቼም የአየር ኃይል ታሪክ ብዙ ነው ። ከተጻፈው ደግሞ ያልተጻፈው ይበዛል ። ይህ ታሪክ ካልተጻፈው ወገን ነው ።

አንቶኖቭ 12 የማጓጓዣ አውሮፕላን

ጥር ወር 1979 ከአስመራ ሁለተኛው አየር ምድብ ተነስቶ ወደ ደብረዘይት ያቀናው የማጓጓዣ አንቶኖቭ 12 አውሮፕላን አየር ላይ የተጓዘው አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ብቻ ነበር ። አውሮፕላኑ ውስጥ ተሳፍረው ከነበሩት መሃከል አብዛኛዎቹ ወጣቶች ነበሩ ። ሮጠው ያልጠገቡ ። ሕይወታቸው ገና ወደፊት የሆነ ። አዛዣቸው ኮሎኔል ብሩክና አሰልጣኛቸው ማስተር መላከም አብረው አሉ ። ብዙዎቻችንን ያስተማሩ አንድ ምሁርም ከታሳፋሪዎቹ መካከል አንዱ ነበሩ ። አቶ/ዶር/ፕሮፌሰር ግርማ ሃይለሥላሴ ። ሁሉም ሰው በአመቻው የማዕረግ ስያሜ የሚጠራቸው የተከበሩና የታወቁ የአየር ኃይል ሲቪል ሰራተኛ ነበሩ።

ሻምበል ብሩ ጋሻው ከዚሁ ቡድን ጋር መሆን ነበረባቸው ። ኮሎኔል ብሩክ የሰጧቸውን ትዕዛዝ ግን አልተቀበሉም ። አለቅዬውም ክስ እንደሚመሰረቱባቸው ዝተው ወደ አስመራ ለመሄድ ይዘጋጃሉ ። ሻምበል ብሩ እንደሚሉት ላለመሄድ ምክንያት ነበራቸው ። አውሮፕላኑ ቡድኑን ይዞ ወደ አስመራ ከመሄዱ በፊት ወዳጃቸው ዶክተር አደፍርስ ጋ ሄደው ዕረፍት እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ ። ወደ አስመራ ላለመሄድ ምክንያት ለማቅረብ ያህል ። ዶክተሩም ለምን ወደ አስመራ አብረህ አትሄድም? ዕረፍት ምን ያደርግልሃል? ብለው ለማግባባት ይሞክራሉ ።

“የለም እነዚህ ልጆች በደህና የሚመለሱ አይመስለኝም ። ይሞታሉ ። መሄድም አልነበረባቸውም ” ፣ ብለው ይናገሩና እፊታቸው ያለቅሳሉ ። ዕረፍቱንም ያገኛሉ ። አስቀድሞ ክፉ ነገር ታይቶኛል ነበር ነው የሚሉት ።

በዚያ አውሮፕላን ላይ የተሳፋሩትን ይዘው ወደ ሰማይ የወጡት አብራሪ ሻለቃ ደጀኔ ነበሩ ። እሳቸውም ሆኑ የአውሮፕላኑ ክሩዎች እዚያ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ደክመዋል ። ብዙ ላብ አፍሰዋል ። ብዙም ተጉዝዋል ። ያን ዕለት ግን የመጨረሻቸው ሆነ ። አየር ላይ ከወጡ በኋላ ከአስራአምስት ኪሎ ሜትር ባላይ መጓዝ አልቻሉም ። ሻምበል ብሩ ጋሻው ግን ይኸውና ብዙ ዳገት ወጥተው ፣ ብዙ ቁልቁለት ወርደው እነሆ ዛሬ እዚህ ሰሜን አሜሪካ ይገኛሉ ። ታሪካቸውንም ያወጉናል ።

የአየር ኃይል ሙዚቀኛ ሻለቃ

የአየር ኃይል ባንድ (ፋን ፌር) ስልጠና የተጀመረው በ1976 ገደማ ነው ። ባንዱ ከአስራ ስምንት ወራት ስልጠና በኋላ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ1978/79 ላይ ነበር ። ኦርኬስትራው የተወጣጣው ከዚሁ ባንድ ውስጥ ነው ። ኅበዝ ኅበዙ ተመርጦ ።

በኢትዮጲያ አቆጣጠር 1979 በአየር ኃይል ታሪክ ውስጥ የደረሰውን አሳዛኝ ነገር የአየር ኃይል ሠራዊትና የደብረ ዘይት ነዋሪ በምሬት ያስታውሱታል ። ከዚህ ቀደም ደርሶ ከነበረው በተለየ አደጋው መላ ሠራዊቱን ታላቅ ሐዘን ላይ ጥሏል ። ሃያ ሁለት ሰዎች በአንድ የአውሮፕላን አደጋ

ሕይወታቸውን አጥተዋል ። ገና ባንድ እግሩ መቆም እየጀመረ የነበረ ኦርኬስትራም እንዳለ ወድሟል ። እሳት የላሱ ፣ ሁሉም በስስት ያያቸው የነበሩ ሙዚቀኛ ወጣቶች አብረው አለቁ ። መጥፎ ዕድል ። ጎዶሎ ቀን ነበር ለመላ ሠራዊቱ ። ለሀገሪቱም እንዲሁ ።

ይህ ባንድ ከመቋቋሙ አስቀድሞ "ተነሳ ተራመድን" ለጆሮ ያበቃ አማተር ባንድ ነበር ። እኔ አልደረስኩበትም ። የ"ተነሳ ተራመድ" ግጥም በደቦ እንደተሰራ የነገረኝ አስተዋጾ ካድረጉት ሰዎች መካከል አንዱ የነበረው ማስተር ቴክኒሺያን ጌታቸው መኮንን ነው ። በኋላ ላይ እኔም ሰለዚህ ባንድ የማወቅ ዕድሉ ገጥሞኛል ። እነደገና ተሰባስቦ ከስራ መልስ ሐረር ሜዳ ሲኒማ ቤት ውስጥ እየተገናኝ ሲለማመድ ። ማስተር አስራት ፒያኖ ፣ ማስተር መላከ ሳክስፎን ፣ ኃይሌ (እንጥሎ) ና መኮንን ጊታር ፣ የኄላእሸት (ዶርዜው) ከበሮ ይጫወቱ ነበር ። አምታትቼው ከሆነ ይቅርታ ። በአጠቃላይ የባንዱ አባላት ግን እነዚህ ይመስሉኛል ።

ታድያ አልፎ አልፎ እኔም ግጥም በመወርወር ተሳትፎ አድራጊ ነበርኩ ። ለሃገር አቀፉ የመሰረተ-ትምህርት ዘመቻ ያዘጋጀነው መዝሙር ለኢትዮጲያ ሬዲዮ በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንደመክፈቻ ሆኖ ያገለግል እንደነበር አስታውሳለሁ ። ስሙ ጠፋኝ እንጂ አንድ ድምጻዊም ልጅ ነበር ። ያው እንደምታውቁት በዚያን ጊዜ ዘፈኑ ሁሉ የአብዮት ፣ የጦርነት ጠረን እንዲኖረው ይፈለጋል ። የዘመቻና የጦርነት ዘመን ነበራ። የሃገር ፍቅር ስሜቱም እንደዚያው የዛኑ ያህል የቡዙዎችን ቀልብ ገዝቷል ።

ታዲይ ይህ አማተር ባንድ ሲወድቅ ሲነሳ ቆይቶ በኋላ ላይ አዲሱ ባንድ ተመሰረተ ። ከመስራቾቹ መካከል አንዱ የነበሩት ሻምበል ብሩ የመጡት ረዥም መንገድ ተጉዘው ነው ። ለሙዚቃው ዓለም የተፈጠርኩ ሰው ነኝ ባይ ናቸው ። ከደብረብርሃን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡና ክቡር ዘበኛ ኦርኬስተራ ውስጥ እንዲቀጠሩ ጥላሁን ገሰሰ ምክንያት ሆኗል ። የሙዚቃ ችሎታቸውን ያደንቅ ነበርና ።

ሻ/ል ብሩ በጓደኞቻቸው ሰርግ ላይ

ሰውዬው ገና በለጋ ዕድሜያቸው ይዘፍናሉ ። ይገጥማሉ ። ያፏጫሉ ። በፉጨት ዛሬም የሚገጠምኝ ካለ ይሞክረኝ ባይ ናቸው ። ክቡር ዘበኛ የመቀጠር ዕድሉን ያጨናገፉባቸው አባታቸውን የሚያውቁ አንድ ጄኔራል ነበሩ ። የዕገሌ ልጅ ሆንህ ዘፋኝ አትሆንም ብለው ወደ መጡበት እንዲመለሱ አድርገዋቸዋል ። ሰውዬው ግን የታያቸው ነገር አለና ወደ ደብረብርሃን ከመመለስ ይልቅ ወደ ሐረር ነው ያቀኑት ። ወደ ሶስተኛ ክፍል ጦር ሙዚቀኛ ። ብዙም ሳይቆዩ ግን ለዕጩ መኮንንነት ተመልምለው ሆለታ ይገባሉ ። ከዚያ በኋላ ነው የወደፊት ሕይወታቸው ከአየር ኃይል ጋር የተገመደው ።

አየር መከላከያ ሲቋቋም ለዚህ ክፍል ከሆለታ ከተመለመሉት ሰዎች መሃከል አንዱ ሆኑ ። መልማያቸውን ማስተር ዜና አሰማኸኝን አሁንም ያስታውሳሉ ። ወዲያው ለሚሳይል ስልጠና ወደ ሩሲያ ቢላኩም ኮርሱን ሳይጨርሱ በስምንት ወራቸው ወደ ኢትዮጲያ ይመለሱና አሰብ ይላካሉ ። የሶማልያ ጦርነት የተጀመረበት ወቅት መሆኑ ነው ። አሰብ ላይ የሚሳይል ስልጠናቸውን እንዲያጠናቅቁ የረዷቸው ኩባዎች ነበሩ ።

ለሙዚቃ የተፈጠሩት ሰው ታዲያ የአየር ኃይል አዛዦች ዓይን የገቡት ወዲያው ነበር ። ሰውዬው ሚሳይል ላይ ቢሰለጥኑም መዝፈንም ፣ መግጠምም ፣ ማፏጨትም አላቆሙማ ። በጀቱ ተፈቀዶ ፣ ምልመላው ተጠናቅቆ ስልጠናው ሲጀመር እዚያው ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው አብረው ነበሩ ።

አየር ኃይል ባንድ የመመልመልም ሆነ የማሰልጠን ልምድ ስላልነበረው ምድር ጦር በአደራ መቶ ሃያ ሰዎችን ለአየር ኃይል ባንድ ይመለምላል ። ለማሰልጠን ግን ድርጅታዊ አቅርቦቱን ማሟላት ስላልቻለ ፖሊስ ሠራዊት ምልምሎቹን ተረክቦ ሰልጠናውን አዲስ አበባ ኮልፌ ላይ አካሄደ ።

ከባንዱ (ፋን ፌር) ውስጥ ተመርጦ የወጣውን ኦርኬስትራ በኋላ አቶ ሙላቱ አስታጥቄ ደብረዘይት እየተመላለሰ ኢቫንጄሊካን ግቢ ውስጥ ማሰልጠን ጀመረ ። ሻለቃ አሸኔም ኦርኬስትራውን በማሰልጠን ረገድ ትልቅ አስተዋጾ አድርገዋል ። ኦርኬስትራው ታዲያ የመጨረሻ ዕጣውን እስከተቀበለበት ቀን ድርስ የተሟላ አልነበርም ባይ ናቸው ሻምበል ብሩ ። የሰለጠኑ ተወዛዋዥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች አልነበሩትም ። ምልመላው ተካሄዶ ገና ስልጠና ላይ ነበሩ ።

በዚህ ምክንያት ነበር ኦርኬስትራው ወደ አስመራ እንዲላክ ሲወሰን የተቃወሙት ። አብሮ ለመሄድም ፈቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩት ። አስገራሚ የሕይወት ገጠመኝ ። እንደ እሳቸው አባባል ኦርኬስትራው ወደ አስመራ እንዲሄድ የገፋፉ ሰዎች ያቀረቡት ምክንያት ሠራዊቱን ለማዝናናት ቢሆንም እግረ-መንግዳቸውንም በጓደኛቸው ሠርግ ላይ ለመታደምና ሠርጉን ለማድመቅ ነበር ። ለደግ የታሰበ ቢሆንም መጨረሻው ሳያምር ቀረ ። ለአየር ኃይሉም ጎዶሎ ቀንን አስከተለ ።

ክፉው ወሬ የተሰማ ዕለት የደብረዘይት ሕዝብ ነቅሎ ነበር የወጣው ። ከተማው የነዚያ በአጭር የቀሩ ወጣቶች ከተማ ነበር ። ለሶስት ጉልቻ ያሰቧቸውና የጠበቋቸው ኮረዳዎች ነበሩ ። ከተማው ላይ ገና መውጣት የጀመሩ ኮከቦች ነበሩና እነሱን በአደጋ ለተነጠቀችው ከተማ ቀኑ ጨለማ ሆነ ።

የአዛዡ የጄኔራል ፋንታ በላይ ሕልምም ነበሩ ። የመላው ሰራዊቱም እንዲሁ ። ሳይፈቱ የቀሩ ሕልሞች ። ብቅ ብላ ወዲያው እንደተሰወረች ጸሐይ አይነት ሆኑ ። ከዚያ ወዲህ ባንዱ ከደረሰበት አደጋ አላንሰራራም ። አንዴ በፖለቲካ መምሪያው ፣ ሌላ ጊዜ በስፖርት ክፍሉ ፣ በመጨረሻም በ101ኛው ትምህርት ምድብ ዕዝ ስር ቢቆይም ከደረስበት ጉዳት ማገገም አልቻለም ። እነደገና በእግሩ ለማቆም ጥረቱ ቢቀጥልም የጎደለው ሳይሟላ ፤ የተሰበረውም ሳይጠገን ሌላ ሁሉኑም ከናካቴው የሚያፍርስ ኃይል ደረሰና መጨረሻው ሆነ ። ሻምበል ብሩ ይህ ሁሉ ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ የአየር ኃይል ክበቦች ሃላፊ ሆነው መስራት ጀምረው ነበር ። የአየር ኃይል ሙዚቃኛ ሻለቃ ጉዳይ ግን እስከ አሁን ከሆዳቸው አልወጣም ።

ኢሕአድግ የቀረውን የሙዚቃ መሳሪያ ነጥቆ ለምድር ጦር ሰጠ ። የተረፈውም በየቤቱ የጌጥ ዕቃ ሆኖ ቀረ ። ሻምበል ብሩ ጋሻው ወደ ሆለታ ፣ ከዚያም ወደ ጦላይ ተግዘው መከራ አይተዋል ። ያ ሁሉ አልፎ ግን ዛሬ በዲቪ ሎተሪ አሜሪካ ገብተው ታሪካቸውን ለመተረክ በቅተዋል ። የሁለት ጨፍ ስሜቶች ዛሬም አእምሮአቸውን ይፈትነዋል ። በአንድ ወገን ሞት ከደገሰላቸው ጥሪ በማምለጣቸው ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚያን ዛሬም ልጆቼ የሚሏቸውን ወጣት ልጆች በሞት በመነጠቃቸው ያዝናሉ ። ሃገራቸውም ዛሬ የሚደርስባት ፍዳ እጅግ ያሳስባቸዋል ።

---------------////----------------

ሚግ አብራሪውና

የቤላሩሱ ሕይወት አድን ድራማ

ፋሲል ማሞ - ሚግ 23 ስኳድሮን

ከአውሮፕላን ጋር የቆየ የድብቅ ፍቅር እንደነበረኝ አስታውሳለሁ ። ገና ጨቅላ ታዳጊ ሆኜ ከኲተቤ አፋፍ ላይ አሻግሬ ቦሌ አለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ ግዙፍ አውሮፕላኖች ሲነሱና ሲያርፉ በርቀት ስመለከት ልቤም አብሯቸው ይነሳና ያርፍ ነበር ። ታድያ አንድ ቀን አምላክ ቢረዳኝ እኔም እንደ አንደኞቹ እሆናለሁ እያልኩ እመኝ ነበር .. በልቤ ።

አየር ኃይልን ከመቀላቀሌ በፊት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበርኩ ። ወጣትነት ብዙ የሚታሰብበትና የሚታቀድበት እንዲሁም የሚመረጥበት ወቅት በመሆኑ እኔም ውስጤ ያለውንና የሚያስደስተኝን ሙያ መምረጥ እንዳለብኝ የሚያስጨንቀኝ ዕድሜ ላይ ነበርኩ ። አውሮፕላን በራሪ መሆንን ደግሞ ከኲተቤ አፋፍ ላይ ጀምሮ የልጅነት ሕልሜ ሆኗል ።

2000 ዓም የኢትዮጵያ አየር መንገድና የኢትዮጵያ አየር ኃይል ምልመላ በተመሳሳይ ጊዜ ነበርና መ/ቤቶቹ የጠየቁትን መስፈርት በማሟላት ሁለቱም ጋ ተመዘገብኩ ። በመጨረሻ ግን የተዋጊ ጀት በራሪነቱ የወጣትነት ልቤን ገዝቶት ኖር አየር ኃይልን መረጥኩ ።

አየር ኃይል የተዋጊ አውሮፕላን በራሪ የሚኰንበት መ/ቤት እንደሆነ ከማሰብ ያለፈ ጠለቅ ያለ ዕውቀት አልነበረኝም ። በእርግጥ የመከላከያ አንዱ ክንፍ መሆኑ ቢገባኝም ከኲተቤ አፋፍ ላይ ዘወትር አሻግሬ ከምመለከተው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ብዙም ልዩነት ይኖረዋል ብዬ አላሰብኩም ። ይሁን እንጂ የልጅነት ህልሜ ውስጥ በራሪ መሆን በቅቷልና አየር ኃይልን በፍቅር ወድቄለት ተቀላቅዬው አረፍኩት ።

እንዳለመታደል ሆኖ አየር ኃይልን ከተቀላቀልኩ በኋላ የገጠመኝ የጠበቅኩት አልነበረም ። በዚህ ተቋም ውስጥ ካለው ፈታኝ የወታደራዊና የበረራ ስልጠና በላይ ከሙያው መስፈርት ወጣ ያለው (Unprofessional) የአስተዳደር ስልት ገና በጠዋቱ ውስጤን ይቆጠቁጠው ጀመር ። አየር ኃይሉ ሙሉ በሙሉ በገዢው ፓርቲ አባላቶችና የስርዓቱ ታማኝ አገልጋዮች ቁጥጥር ስር ውሏል ። ይህ ወታደራዊ ተቋም ዋነኛ የስርዓቱ ክንድ እንዲሆን ይፈለግ ነበርና ትምህርቱና ብቃቱ ከነበራቸው ሙያተኞች ይልቅ የፖለቲካ ታማኞችን የሚያበረታታ አሰራር ጠንክሮ ይታያል ። ይህ ከሙያ ብቃት ይልቅ ፖለቲካዊ ወገንተኝነትን መሰረት ያደረገን አካሄድ ልቀበለው እንደማልችል ውስጤ እየነገረኝ ቢሆንም የበረራ ስልጠናውን በትጋት በመከታተልና ጥቂቶችና ብቃት ያላቸው በራሪዎች ብቻ በሚመደቡበት ተዋጊ ስኳድሮን በሚግ 23 ቦምብ ጣይ አውሮፕላን ላይ በመመደብ አገሬን በቅንነትና በጀግንነት ለማገልገል ከመጀመሪያው ረድፍ ተሰለፍኩ ።

ተወልጄ ያደግኩት በመዲናችን አዲስ አበባ ነው ። እንደሚታወቀው አዲስ አበባ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች በአንድነት ተቀላቅለው የሚኖሩባት ከተማ በመሆኗ የእኔ የዘር ሃረግ እንደ ጥያቄ ወደ ጭንቅላቴ መጥቶ አያውቅም ። እናም የኢህአዴግ የአገዛዝ ስልት ሊመቸኝ ባይችል አያስገርምም ። ይህ ዘርን መሰረት ያደረገው የፖለቲካ አካሄድ ያለመተማመንን ፣ ከዚያም መለያየትን ያበረታታል ከሚሉት ወገን ነኝ ። የእኔ ፍላጐት ደግሞ መለያየት ሳይሆን አንድነት ነው ። ያለመተማመንን አጥብቄ እጠላለሁ ። በዚህ አስተሳሰቤም ዳጐቼለት ምርጫዬ ያደረኩት የአየር ኃይል ሙያና የፖለቲካው መስመር ተለያይተውብኝ ምቾት ነሳኝ ።

ዛሬ ላይ ሆኜ ያለፈን ታሪክ ሳወሳ ቀላልና የዋዛ ሊመስል ይችላል ። እዚህ ለመድረስ ግን ብዙ ውጣ ውረድን አሳልፌያለሁ ። በተለይ ግፍና በደል እየበዛ ሲሄድና ህሊና በቃኝ ሲል ፣ ውስጥህ አሻፈረኝን ማንጐራጐር ይጀምራል ። ያኔ ነገሮች ሁሉ ይቀያየራሉ ። እኔም ጋ የሆነው ይኸው ነው ።

2005 ዓም ድንገት በአገራችን የፖለቲካ አካሄድ ላይ ለውጥ የሚያመጡ እንቅስቃሴዎች መታየት ጀመሩ ። የአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ በመንግስት ሚዲያ በይፋ በአገራችን ጉዳዮች ላይ ሲከራከሩ እንዲታዩ ሆነ ። የተቃዋሚዎች በይፋ ወጥተው ሃሳባቸውን የመግለፃቸው ክስተትና የገዢው ፓርቲም ሆደ ሰፊ መሆን በአገራችን የዴሞክራሲ ጭላንጭል የታየበት መድረክ ሆኖ ተስተውሏል ።

በዚህ የክርክር መድረክ የኢሕአዴግ ድክመትና ያሉበት ስህተቶች ጐልተው የወጡበትና ሚዛኑንም ስቶ ሲውተረተር

ማየት በእጅጉ የሚያስደምም ትዕይንት ሆነ ። እንዲዚህ አይነት ግልፅ የፖለቲካ አካሄድ በአገራችን የተለመደ አልነበረምና ሁኔታው የሕዝቡን ትኩረት ሳበ ። እኔም እንደ አብዛኛው የአገሬ ሕዝብ ክስተቱን በመመልከት በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ለውጥ እየመጣ ነው በማለት ደስ ብሎኛል ።

በዚህ የለውጥ ሞቅታ ውስጥ እያለሁ ድንገት ከነበርኩበት የሚግ-23 በምብ ጣይ ተዋጊ ስኳድሮን ተነስቼ ለሱ-27 ተዋጊ አውሮፕላን ስልጠና ወደ ውጪ መሄድ እንዳለብኝ ተነገረኝ ። ትዕዛዙ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ዓይነት ነበር ።

በወቅቱ የሚግ 23 በምብ ጣይ ስኳድሮን የአብራሪ አቅሙ እጅግ ውሱን ነው ። እኔና 4 የበረራ ባልደረቦቼ በስኳድሮኑ የበረራ ዝግጁነትና ከኤርትራ ጋር በማንኛውም ሰዓት ወደ ውጊያ ሊገባ ይችላል በሚል ሰበብ ከዋናው ቤዛችን ባህር ዳር ተነስተን መቀሌ ከትመናል ። በዚህ ቀውጢ ሰዓትና የአብራሪ እጥረት ካጠቃው ሚግ 23 ስኳድሮን ተነስቶ ለሱ 27 ስልጠና በሚል ሰበብ ከአገር ውጪ የመሄዱ ጉዳይ አነጋጋሪ ነበር ። ይሁን እንጂ ከፖለቲካው ትኩሳት መራቄ ቅር እያለኝም ቢሆን የመጣውን ወታደራዊ ትዕዛዝ ያለ አንዳች ማመንታት መቀበል ነበረብኝ ።

የስልጠናው ዕድል እንዴት እንደተሰጠኝ ፣ ማንስ እንደመረጠኝና በምንስ መስፈርት እንደተመረጥኩ የማውቀው ነገር ባይኖርም ፤ ሱ-27 አውሮፕላን በዘመናዊነቱና በውጊያ ብቃቱ ብዙ የተባለለት መሆኑ እያስደሰተኝና በአገራችን እየተነቃቃ ያለው የፖለቲካ ለውጥ ውስጤን እያሞቀው ወደ ቀድሞዋ የሶቭየት ሕብረት አካል ቤላሩስ ተጓዝኩኝ ።

በአካል ከቤተሰቦቼና ከአገሬ ብርቅም ከአገር ስወጣ የነበረው የአገራችን የፖለቲካ ምስቅልቅል እያሳሰበኝ ነበር ። በአገኘሁት መንገድ ሁሉ ሁኔታዎችን በቅርበት ለመከታተል መረጃዎችን ከድሕረ ገፆችና ከተለያዩ ሚዲያዎች እቃርም ጀመር ። ያ አዎንታዊ የሆነው የአገራችን ዴሞክራሲያዊ የምርጫ አካሄድ ለአገራችን ሰላም መስፈን በእጅጉ ተስፋ እንደሚሰጥ እያሰብኩ ነበር ። ግና ብዙም አልቆየም ። ኢህአዴግ ለሕዝብ የገባውን ቃል አጠፈ ።

ከምርጫው ውጤት በኋላ እየተደረገ ያለውና እየተሰማ የነበረው ውዝግብ ሰላሜን ነሳው ። ተስፋ እንድቆርጥና ለምን ? የሚል ጥያቄ እንዳነሳም አደረገኝ ።

መከላከያ ሰራዊቱ አገርን እንጂ አንድን ፓርቲ አገልጋይ አይደለም የሚለውን ዴሞክራሲያዊ መርህ ውስጤ ይቀበላል ።

ሰራዊት አገር የመጠበቅ እንጂ ዜጋውን በጭካኔ የመግደል ስልጣን እንደሌለው በሚገባ የማውቅ ሰው ነኝ ። በውስጤም ለምንድነው ሕዝብ የሚጨፈጭፍ ስርዓት የማገለግለው ? የሚል ጥያቄ ፈጠረ ። እስከመቼ ነው ሕዝብ መብቱን ሲጠይቅ መሳሪያ የሚደገንበት ? ይህ ለእኔ ከባድ ወንጀልና ግፍም ጭምር ነበር ። የዚህ ወንጀል አካል ፣ ተሳታፊና መሳሪያ መሆን ደግሞ ፈፅሞ አልፈለግም ። ወያኔ እየገባበት ካለው የወንጀል ማጥ በራሱ ይውጣ እንጂ አጋር ልሆነው አይገባም አልኩ ። **በታሪክ ተጠያቂ ከመሆንና ወልዶ ያሳደገህ ሕዝብ ላይ እንደ መተኮስ የሚያሳፍር የወንጀል ጫፍ የለምና** ከዚህ ስርዓት ፈፅሞ መለያየት እንዳለብኝ ወሰንኩ ።

ሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እንደሚያደርጉት በገሃድ በአደባባይ መቃወም አለብኝ ብዬም ለራሴ ቃል ገባሁ ። ይህንን ለማድረግ ስልጠናውን ማቋረጥ የመጀመሪያው እርምጃ መሆን ነበረበት ። ሕይወት ውሳኔ ከሌለበት ስኬታማ አይሆንምና እኔም ተቋውሞዬን "ሀ " ብዬ ለመጀመር ውሳኔ ላይ ደረስኩ ።

በውጪም ሆነ በአገር ውስጥ ያሉት ኢትዮጵያውያን በያሉበት ለተቃውሞ በመውጣት የዓለም መንግስታት በሕውሃት አገዛዝ ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርጉ የዜግነት ግዴታቸውን እየተወጡ ነበር ። የተቀሩት የስራ ባልደረባዎቼም እንደ እኔው ያስቡ ነበርና ይህ አስተሳሰብ የእኔ ብቻ እንዳልሆነ ሳይ ተበረታታሁ ። በሚገርም ሁኔታ ከአስር የስራ ባልደረቦቼ መካከል ስምንታችን በአንድ ዓላማ ስር መሆናችንን አረጋገጥኩ ።

መ/አ ፋሲል ማሞ ከሚ-23 ተዋጊ አውሮፕላኑ ጋር

እንቅስቃሴያችን በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት ስምንታችንም ተስማምተናል ። በምንም መልኩ ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ እንቅስቃሴ ማድረግ የለብንም ። እንዴት ፣ ለማንና መቼ እጃችንን መስጠት እንዳለብንና አጋርነታችንን ለሕዝቡ በምን መልኩ መግለፅ እንዳለብን አጠናን ።

እጃችንን ለመስጠት ያሰብንበት ቦታ ዋና ከተማዋ ሚኒስክ ውስጥ ሲሆን ከመኖሪያ ከተማችን ራቅ ያለ ነበር ።

የምንፈልጋቸው በታዎችም የሚገኙት ሚኒስክ ውስጥ ነው ። ስለዚህም ወደ ከተማዋ ተጉዞ መረጃ መሰብሰብ የግድ ነበር ።

ሚንስክን መጐብኘት የሚል ሰበብ ሰጥተን በመጓዝ የምንፍልጋቸውን በታዎች ሁሉ አጠናን ። ይህ የሆነው እጅ ከመስጠታችን ጥቂት ቀናት በፊት ነበር ። እንደ አጋጣሚ እኛ እጃችንን ልንሰጥ ስናስብና በአገር ቤት ደግሞ ከስራ ባልደረቦቻችን መካከል መ/አ በኃይሉ ገብሬና መ/አ አብዮት ማንጉዳይ በታጠቁት ሚ-35 ሔሊኮፕተር አዲስ አበባ ሰላማዊ ሕዝብ አናት ላይ እንዲበሩ የተሰጣቸውን ግዳጅ ተቃውመው ወደ ጅቡቲ የኰበለሉበት ወቅት አንድ ሆኖ ነበር ። በዚህም የተነሳ የኢሕአዴግ ባለስልጣናት ከኢትዮጵያ እየደወሉ እንቅስቃሴያችንን መከታተል በመጀመራቸው እጅግ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ገባን ።

Fotoscanner från Google Foto

በነፍስ አድኑ ዘመቻ ነፃ ከወጣን በኋላ

አወጣጣችንን ከባድ የሚያደርገው ደግሞ የምንኖርበት ቤት በጥበቃ ስር መሆኑ ነው ። የከተማዋ ፖሊሶችም ያውቁናል ። በተጨማሪም እኛ እጃችንን ለመስጠትና ከለላ እስከምናገኝ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ አገር ቤት ቢሰማና ያለንበት ቦታም ቢታወቅ ሊደርስብን የሚችለው ነገር ከባድ መሆኑ እሙን ነበር ። ቢሆንም ይህ ሁሉ አደጋ ያሰብነውን ከማድረግ ወደ ኋላ የሚያደርገን ባለመሆኑ ዕቅዳችንን ለማሳካት በቁርጠኝነት ቀጠልን ።

እጅ ከመስጠታችን አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሁለት ባልደረቦቻችንን አስቀድመን ወደ ሚኒስክ በመላክ ሆቴል እንዲይዙና በተቻላቸው መጠን ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲሰበስቡ አደረግን ። የላክናቸው ጓደኞቻችንም በቀለጠፈ አኳኋን ነገሮችን አስተካክለውና የሆቴላችንን አድራሻ ደውለው አሳወቁን ። እኛም በከፍተኛ ጥንቃቄ መኖሪያ ከተማችንን በመልቀቅ ሊገጥመን የሚችለውን ማንኛውንም ፈተና በፀጋ ለመቀበል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አካባቢውን ለቀን በመውጣት ሚንስክ ገብተን አደርን ።

በማግስቱ ማልደን በመነሳት በቀጥታ ወደ አሜሪካን ኤምባሲ በማቅናት አምባሳደሩን ለማነጋገር እንዲፈቀድልን ጠየቅን ። ይሁን እንጂ አምባሳደሩን ለማግኘት ያደረግነው ጥረት ባይሳካም ምክትላቸውን ለማነጋገር ተፈቀደልን ። ለአምባሳደሩ ተወካይ ተገቢውን ሰላምታ ከአቀረብን በኋላ አገራችን ውስጥ እየተፈፀመ ያለውን ግድያና ያለመረጋጋት ፣ በተጨማሪም እኛ እየወሰድን ያለውን ዕርምጃ ዘርዝረን በማስረዳት የአሜሪካ መንግስት የፖለቲካ ጥግኝነት እንዲሰጠን አበክረን ጠየቅን ።

ተወካዩም ኤምባሲው ጥገኝነት መስጠት እንደማይችልና በተባበሩት መንግስታታ የስደተኞች ፅ/ቤት (UNHCR) በኩል ማመልከት እንደሚገባን አሰራሩን ጭምር በታላቅ ትህትና በማስረዳትና የጉዳያችንንም ከባድነት በመገንዘብ በኤምባሲው ወጪ ታክሲ ተከራይተው ወደ ስደተኞቹ ፅ/ቤት እንድንሸኝ አደረጉ ። በኤምባሲው ለተደረገልን መልካም መስተንግዶ በማመስገን በታክሲ ወደ UNHCR (አለም ዓቀፉ የስደተኞች ጉዳይ ፅ/ቤት) አመራን ።

ዕለቱ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ጁን 20 ነበር ። ይህ ቀን ደግሞ የዓለም የስደተኞች ቀን እንደሆነ ይታወቃል ። እንደ ዕድል ሆኖም በዕለቱ ፅ/ቤቱ ክፍት ነበርና የስደተኞቹ ፅ/ቤት ሰራተኞች በትህትናና በአክብሮት ተቀብለው አነጋገሩን ። ስለ እኛም ከአሜሪካ ኤምባሲ ተደውሎ እንደተነገራቸው አሳወቁን ። የጉዳያችንን ከባድነት በመረዳታቸው ብዙ አላጉላሉንም ። እንዲያውም የUNHCR ዋና ዳይሬክተር የነበርንበት ከተማ ድረስ መጥቶ በመጐብኘት ለጉዳያችን ልዩ ትኩረት ሰጥቶት የሚችለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ቃል ገባልን ።

ከUNHCR ጋር ያለንን ጉዳይ በቀላሉ እንደጨረስን ወዲያው በጀርመን ድምፅ በኩል እርምጃችንን ለዓለም ሕብረተሰብ ለማሳወቅ ከሬዲዮ ጣቢያው ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ ተስማማን ። የኢሕአዴግ አገዛዝ በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ግድያ በመቃወምና ለወገናችን ያለንን አጋርነት በመላው ዓለም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖችና ለዓለም ሕዝብ ከጓደኞቼ ጋር በመሆን ግልፅ አደረግን ። ከዚያም ጉዳያችንን በቅርበት ሆነን ወደምንከታተልበት ከተማ ተላክን ።

ከሰከነ የሕይወት መስመር በአንድ ጊዜ ወደ አደገኛና መጨረሻው ምን ሊሆን መገመት ወደማይቻልበት የሕይወት መስመር ወረድን ። የስደት ሕይወትም "ሀ" ብሎ ተጀመረ ።

ስደት ቤላሩስ ውስጥ እጅግ አደገኛ ነው ። በማንኛውም ደቂቃ አደጋ ሊደርስብህ ይችላል ። ለደህንነትህም ምንም ዋስትና አይኖርህም ። ስለዚህ በዚህ አደገኛ አኗኗር ውስጥ እያለን ወደ ቤላሩስ የኢሚግሬሽን ፅ/ቤት በመሄድ የጥገኝነት ጥያቄ አቀረብን ። ጥያቄያችን ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ከአንድ ወር

በላይ እንደሚፈጅና ለደህነታችንም የ24 ሰዓታት ጥበቃ እንደሚደረግልን በመግለፅ ትንሽ እፎይ እንድንል አደረጉን ። ቀን ቀን ሁለት በደምብ የታጠቁ ፖሊሶች ፣ ማታ ደግሞ ሁለት ሲኒየር መኰንኖች ተጨምረው መኖሪያችንን በመጠበቃቸው ሰላማችን መለስ ቢልም በዓይነ ቁራኛ ስለሚከታተሉን እንቅስቃሴያችን ፈፅሞ የተገታ ሆነ ።

የስደት ኑሯዋችንን ከጀመርን ማግስት አንስቶ በሞስኰ የኢሕአዴግ አገዛዝ አምባሳደር የነበረው ጄ/ል አሳምነው በዳኔ እኛን ለማግኘትና ለማነጋገር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ጀመረ ። በፍፁም ልናገኘው እንደማንፈልግ ብንገልፅለትም ጉትጉታውን ማቆም ባለመቻሉ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ባለስልጣን ጋር አንዳችም ድርደር ለማድረግ ፈቃደኛ ያለመሆናችንን በፅሁፍ ለአምባሳደሩ አሳወቅን ። ጐን ለጐንም ተቃውሟችንን በተለያዩ ሚዲያዎች ደጋግመን ማሰማታችንን ቀጠልን ።

የእኛ ቁርጠኛ ተቃውሞ ለአየር ኃይሉም ሆነ ለገዢው ስርዓት ታላቅ ውድቀት ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ደስታንና ብርታትን የፈጠረ ነበር ።

በወቅቱ የቤላሩስ ፕሬዝዳንት የነበሩት አሌክሳንደር ሉካሼንኰ ለስደተኞቹ ኰሚሽን ኃላፊ እኛ ቤለሩስ ውስጥ እስከአለን ድረስ ምንም ዓይነት አደጋ እንደማይደርስብን ቃል እንደገቡላቸው ተነግሮናል ። በተቃራኒው ግን የቤላሩስ ወታደራዊ አዛዦችና ኃላፊዎች በድርጊታችን ደስተኛ ባለመሆናቸውና ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖራቸው የሚችለው ወታደራዊ የንግድ ግንኙነት አደጋ ላይ በመውደቁ ሊበቀሉንም እንደሚፈልጉ በሚያደርጉት ድርጊትና በንግግራቸው ለመረዳት ችለን ነበር ።

አንድ ወር በታጠቁ ጠባቂዎች ቁጥጥር ስር መዋልና ውሉ ባልታወቀ ሁኔታ ነፃነትን እንደማጣት አስከፊና አስጨናቂ ወቅት አይኖርም ። ስንወጣም ሆነ ስንገባ የምናደርገውን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ለእነርሱ የማሳወቅ ግዴታ ተጥሎብን ሳለ አንድ ወር ሞላንና የቤላሩስ ኢሚግሬሽን ባለስልጣናት በሚያሳዝን ሁኔታ ጉዳያችን ተቀባይነት ባለማግኘቱ ወደ አገራችን እንድንመለስ የሚያዝ ውሳኔያቸውን አሳወቁን ። እንደ እነርሱ ገለፃ በአገራችን ውስጥ ሰላም እንደሰፈነና መንግስትም በደል እያደረሰ አይደለም የሚል ድምዳሜ ጨምረውበታል ። ከዚሁ ውሳኔ ጋር ተያይዞም መኖሪያችን አካባቢ የነበረው ጥበቃ በዚሁ ቀን ተነሳ ። ይህ የቤላሩስ ባለስልጣናት ውሳኔ እጅግ ከፍተኛ ጥርጣሬ ላይ ስለጣለን ለ UNHCR ጉዳዩን በዝርዝር ስናስረዳቸው እነርሱም ድንጋጤ ላይ ወደቁ ።

የቤላሩስ መንግስትን ውሳኔ ተከትሎ ሊደርስብን የሚችለውን አደጋ መገመት ቀላል ነበር ። በላያችን ላይ አደጋ እያንዣበበ እንደሆነ ተረድተናል ። በወቅቱ የሕውሃት አገዛዝ ያደረገውን የምርጫ ውጤት ማጭበርበር በመቃወም ከአገር ወጥተን መቅረታችን እንዲሁም በታወቁ የውጪ ሚዲያ ተቃውሞዋችንን መግለፃችን ምን ያክል ገዢውን ፓርቲ እንደጐዳው ግልፅ ነበር ። ከዚያም በላይ አየር ኃይሉ በአንድ ጊዜ 8 ተዋጊ በራሪዎችን ማጣቱ ምን ያክል እንደሚጐዳው መገመት አያዳግድትም ። በአገር ውስጥ ያሉ የግል ፕሬሶች በእኛ ጉዳይ ላይ በሰፊው ይዘግቡ ስለነበር ስርዓቱን በእጅጉ እየጐዳው ነበር ። በመሆኑም የሕውሃት አገዛዝ የከፈለውን መስዋዕትነት ከፍሎ እኛን በእጁ ቢያስገባ እንደ ከፍተኛ ድል ይቆጠርለታል ። ይህንን ዕቅዱን ለማስፈፀም ደግሞ በጐን ከቤላሩስ ከፍተኛ ወታደራዊ ባለስልጣናት ጋር በድብቅ እየተዋዋለ መሆኑ ይሰማል ። የቤላሩስ መንግስት የጥገኝነት ጥያቄያችንን ውድቅ ማድረጉና የተመደበልን ጥበቃም በአስቸኳይ መነሳቱ ለኢሕአዴግ ባለስልጣናት ዕቅዳቸውን ለማሳካት አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው ።

ምንም እንኳ ይግባኝ መጠየቅ እንደምንችል ቢገለፅልንም ጥበቃ አልባ የሆነውን የመኖሪያ ቤት ለቀን በፍፁም መንቀሳቀስ እንደማንችል መነገሩ ጥርጣሬያችንን ከፍ አደረገው ። በዓይነ ቁራኛ መከታተላቸውንም ተረድተናል ።

ወጣቱ ካዴት ፋሲል ከበረራ አስተማሪው ጋር

የመጣውን አደጋ በፀጋ ከመቀበል ውጭ በኢሕአዴግ ሴራ ላለመውደቅ ለራሴ ቃል ገባሁ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአራትና አምስት ቀናት ውስጥ ከቤለሩስ አስገድደው ሊወስዱን ዝግጅታቸውን ማጠናቀቃቸውን ጉዳያችንን በቅርበት የሚከታተሉ በመላው ዓለማት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖች አሳወቁን ። መረጃውም ሞስኰ ውስጥ ከሚኖሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች አማካኝነት እንደተገኘም ተነገረን ።

ዝርዝር ዕቅዱም ኢሕአዴግ አንቶኖቭ -12 ተብሎ የሚጠራውን ግዙፍ የዕቃ ማመላለሻ የአየር ኃይል አውሮፕላን በጥገና ስም

ወደ ቤለሩስ ሊያመጣና እኛን በማሳፈን አስገድዶ በዚሁ ወታደራዊ አውሮፕላን ከቤለሩስ ይዞ መውጣት ነበር ። ለዚህ ግዳጅ የሚተባበሩ የቤላሩስ ወታደራዊ ጄነራሎች ዳጐስ ያለ የአሜሪካ ዶላርና ውድ ገፀ በረከት እንደሚቀርብላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል ።

በወቅቱ ይህንን መረጃ የሚያቀርብልን ሰው ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆኑና ምን ማድረግ እንደሚገባን ሲያማክረን ጭንቀቱን በድምፁ መቆራረጥ መረዳት ቀላል ነበር ። በተቻለ ፍጥነት አሁን ካለንበት አካባቢ እንድንሰወርና ወደ ጐረቤት አገር መሻገር እንዳለብን አሳሰበን ። ይሁን እንጂ ከአካባቢያችን ለመሰወርም ሆነ ወደ ጐረቤት አገር ለመሻገር የሚያስችለን ምንም የሚያፈናፍን ሁኔታ አልነበረም ። በራሳችን ለመደበቅም ሆነ ለመንቀሳቀስ አልቻልንም ። አማካሪያችን ግን ወደ ሩስያ ብንሻገር እዚያ ያሉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች ነፍሳችንን ሊታደጉንና ማናቸውንም መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀታቸው ሲነገረን ልባችን ትንሽ ተስፋን አጫረ ። ብርታትም አገኘን ። ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ደጐች ናቸው ። የእኛን ጉዳይ እንደራሳቸው አድርገው እየተከታተሉ ነው ። ይህ ሕብረትና ቁርጠኝነት እንደሚያድነን ተስፋ አደረግን ። ይህ ከየአቅጣጫው የሚመጣልን እገዛ ብርታት ሆኖን የእኛም እልህና ቁጣ የዚያኑ ያክል ሆነ ። የመጣው ይመጣታል እንጂ ሕውሃት እጅ በመግባት የሕዝባችን የትግል ወኔ ላይ ውሃ አንቸልስም ። መስዋዕትነት ከጠየቀ መስዋዕት ለመሆን ዝግጁ ነን ብለን ለራሳችን ደጋግመን ቃል ገባን ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከተጋረጠብን አደጋ ክብደት አንፃር የተነገረንን ሁሉ ለማመን እየተቸገርን ነበር ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ሊረዱን ቁርጠኝነቱ እንዳላቸው ብናምንም ከምንሰማቸው መረጃዎችና ግርግሮች ጀርባ የሕውሃት እጅ ቢኖርበትስ የሚለውን አስፈሪ ጥያቄ ማናችንም መመለስ አልቻልንም ። ከሚያናግሩን ውስጥ አንዳቸውንም በአካል የምናውቃቸው አልነበሩምና ክፉ ብናስብ የሚፈረድብን አይደለም ።

ኢሕአዴግ ባለ በሌለ ኃይሉ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ከመረጃዎቹና በአካባቢያችን ከሚታዩት እንቅስቃሴዎች መረዳት ቀላል ነበር ። እኛን እየተከታተሉ ወሬ የሚያቀብሉት ሰዎች እንዳሉ በሁኔታዎች እየተረዳን ነው ።

በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ እያለን ሊረዱን የተዘጋጁትን ኢትዮጵያውያኖች ማንነት ሊያጣራልንና ልናምነው የምንችለውን በአካልም የምናውቀውን የመጨረሻ ሰው የውስጥ ጥርጣሬና ፍርሃታችንን በድፍረት ማማከር ነበረብን ። በምላሹም ከነማን ጋር በቅርበት መስራት እንዳለብን አቅጣጫ በማግኘታችን እፎይታን አገኘን ። ከሞስኮም ሆነ ከሰሜን አሜሪካ ሰብዓዊነትን መመሪያቸው ካደረጉ ወገኖቻችንንም ጋር በግልፅ ልባችንን ከፍተን መነጋገር ጀመርን ።

በወቅቱ አገራችን ውስጥ ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰዎች ላይ እየተደረገ ያለውን ግድያና እስር በይፋ ወጥተን በመቃወማችን የበርካታ ኢትዮጵያኖችን ልብ በመግዛት ከፍተኛ አክብሮትን ለግሰውናል ። ከመላው ዓለም በተለይም ሰሜን አሜሪካ ያሉ ወገኖቻችን በሃሳብም በገንዘብም ለአንዷት ደቂቃ እርዳታቸውን ሳያቋርጡ አብረውን የጭንቀቱን ጊዜ እየገፉ ነበር ። ወደ ሕውሃት እጅ መውደቁን ሁሉም በአንድነት ለማስቆም ደፋ ቀና ብለዋል ። ለዓለም ህብረተሰብ አቤት ለማለትና በሕውሃት አስተዳደር ላይ ጫና ለመፍጠር በሰላማዊ ሰልፍም ሆነ አስፈላጊ ናቸው ይሏቸውን ቢሮዎች እያንኳኩ ጉዳያችንን እንደጉዳያቸው አድርገው አከናውነዋል ። ለእነዚህ ብርቅዬ ኢትዮጵያውያን ዜጐቻችን የምንከፍለውና የምናመሰግንበት ቃላቶች ዛሬ ድረስ ያጥሩናል ።

እነዚሁ ወገኖቻችን ለየዕለቱ መኖሪያችን የሚያስፈልገውን የመጠለያና የምግብ ወጪ ከመደጐማቸው ስራ ጐን ለጐን ከቤላሩስ በሰላም በመውጣት ወደ ሌላ ሁለተኛ አገር ለማሸጋገር የሕይወት አድን ግብረሃይል በማቋቋም ሌት ተቀን እየሰሩ ነበር ። ይህ ግብረሃል ሁኔታዎችን በከፍተኛ ሚስጢር በመያዝ ፣ በሚቻለው ፍጥነት ከአለንበት አደጋ በአስቸኳይ እንድናመልጥ የሚያደርግ ዕቅድ ዘረጋ ።

አሁን በፍፁም የሚባክን ጊዜ የለም ። እኛም ሆንን ወገኖቻችን ሌት ተቀን እየተዘጋጀንና ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ በሙሉ ተጠንቀቅ ላይ ሆንን ። የምናመልጥበት መንገድም አማራጩ እጅግ የጠበበ ፣ ቁርጠኝነትና በፅናት መቆምን የሚጠይቅ እንደሆነ ብንረዳም ያለ መጠራጠር ዝግጅታችንን ቀጠልን ። ከሁሉም በላይ የነበረን ጥበቃ በይፋ ተነስቷል ይበሉን እንጂ በተለያዩ ሁኔታዎች በድብቅ እንቅስቃሴያችንን ይቆጣጠሩ ነበር ።

ሞስኮ ካሉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በአንድ ነገር ተስማምተናል ፤ ይኸውም መኖሪያ ቤታችን መጠናት ነበረበት ። ይህንንም ጉዳይ የሚያከናውን ሰው ተልኰ ካሜራ መኖሩን ፣ መኖሪያ ቤታችን ምን እንደሚመስል ወጣ ገባውን አጥንቷል ። ምክንያቱም ከቤታችን መውጣት ባንችል እንኳ እቤት ድረስ ገብቶ ማዳን የሚል የመጨረሻ አማራጭ ስለነበረውም ጭምር ነበር ።

የሞስኮ አገር ወዳዶች ከሞስኮ ባለስልጣናት ጋር ጥሩ ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን የተቀሩትም በሞስኮ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ የሚደረገውን በቅርበት መከታተል የሚችሉ ነበሩ ።

የኢትዮጵያ ገዢዎችና የቤላሩስ ጄነራሎች እኛን ለመበቀል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በእነዚህ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጥብቅ ክትትል ስር ወድቋል ። እነዚህ አገር ወዳዶች ደግሞ እኛን ሊረዱን ይችላሉ ለተባሉት አካላት በአስቸኳይ እየተደረገ ያለውን ያሳውቃሉ ። መልዕክቱን የሚቀበሉት ክፍሎች ደግሞ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ከፍለው እኛን ለማዳን ቅድመ ዝግጅታቸውን እየነደፉ ነበር ።

ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ነገር ግን ተከፍሏቸው መረጃዎችን የሚያጠናቅሩት ሰዎች ዱካችን በሚገባ እየተጠበቀ እንደሆነና መኖሪያችንም ዙሪያውን በካሜራ እንደሚጠበቅ አረጋገጡ ። ይህ መረጃ ለእኛ መድረሱ እጅግ ጠቃሚ ነበር ። በተቻለ መጠን ትኩረት ሳንስብ ተራ በተራ መኖሪያችንን መልቀቅ እንዳለብን ረድቶናል ።

አወጣጣችን ምን መምሰል እንዳለበት ፣ ከመኖሪያ ቤታችን ስንወጣ የምንሰጠው ምክንያት ፣ ስንት ስንት ሆነን እንደምንወጣ ፣ አለባበሳችን ምን መምሰል እንዳለበትና በመጨረሻም የመገናኛ ፣ የመሰባሰቢያ ቦታችን የት ሊሆን እንደሚገባውና የተቀሩትንም ጥቃቅን ነገሮች እንዴት መፈጸም እንዳለብን በጋራ ተመካክረን አፀደቅን ።

መኖሪያ ቤታችን በብረት ፍርግርግ የታጠረ ነው ። በይበልጥ ማታ ማታ በሩ ስለሚዘጋ መክፈት አይቻልም ። ጨለማን ተገን አድርጎ መንቀሳቀስ እንደ አማራጭ ሊወሰድ ቢችልም በሩ ምሽት ላይ በመዘጋቱ ምክንያት የተሻለው ሰዓት በቀን የምናደርገው እንቅስቃሴ ነበር ። ስለዚህ እንቅስቃሴው መጀመር ያለበት በጠዋት እንዲሆን በመወሰናችን አንድ ሁለት እያልን የተለያየ ምክንያት በመስጠት በጠዋት መኖሪያ ቤታችንን ለቀን ወጣን ።

የሰው ኃይላችን በሶስት እንዲከፈል ተወስኗል ። የተለያዩ ሶስት መኪናዎች እያንዳንዱን ግሩፕ እንደሚወስዱ አስቀድሞ ፕላን ተደርጓል ።

በእኔ በኩል ሃሳቤ ተከፋፍሏል ። እያንዳንዷ ን እንቅስቃሴያችንን በጥርጣሬ ነው የምመለከተው ። የመታፈን ዕድል ሊኖር ይችላል የሚለው ሃሳብ ነፍሴ አስጨንቋታል ። መታፈናችን ለእኛም ፣ ለሌሎች ኢትዮጵያውያኖችም ሆነ ለአጠቃላይ ለትግሉ የሚያመጣው አሉታዊ ጐን ያሳስበኛል ። በሌላ መልኩም ደግሞ እኛን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ኋላ ኋላችን የሚክለፈለፈው ሕውሃት እኛን እጁ በማስገባት ሊፈጥረው የሚችለውን የሞራል የበላይነት በፍፁም አዕምሮዬ ሊቀበለው ፈቃደኛ ሊሆን አይችልም ። በፍፁም ከነነፍሳችን እጃቸው ሊያስገቡን አይገባም እያልኩ በውስጤ ደጋግሜ ቃል እገባለሁ ። በወቅቱ አዕምሮዬ በምን ያህል ፍጥነት ነገሮችን ያወጣና ያወርድ እንደነበረ ፣ የአካባቢያችንን እንቅስቃሴ የማስተውልበት ቅፅበት አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ይገርመኛል ። ነገሮችን ሁሉ በጥርጣሬ እያስተዋልኩ ቢሆንም አማራጭ አልነበረኝምና ማድረግ ያለብኝን ዝም ብዬ ማድረጌን አላቋረጥኩም ።

የግዜ ዑደት አያቆምምና የፍፃሜዋ ሰዓት ደረሰች ። እኔንና አንደኛውን ባልደረባዬን እንዲወስደን የተመደበው መኪና ወደ እኛ እየተቃረበ ሲመጣ ፍጥነቱን አቀዘቀዘ እንጂ ፈፅሞ አልቆመም ። በፍጥነት አንድ ነጭ ሰው ከመኪናው ዘሎ በመውረድና በዚያው ፍጥነት ሁለታችንም ወደ መኪናው እንድንገባ አደረገን ። ሌሎች መኪኖችም በተመሳሳይ ሁኔታ እየመጡ የተቀሩትን ጓደኞቼን በመኪና እያነሱ ተፈተለኩ ።

የጫነን መኪና በፍጥነት ይከንፋል ። መኪናው የሩስያና ቤላሩስ ድንበር ድረስ ለ45 ደቂቃ ሲጓዝ ከጓደኛዬ ጋር አንዲትም ቃል አልተለዋወጥንም ። ይህ ጉዞ ወደ የትኛው የዕድል መስመር እንደሚመራን እርግጠኞች አይደለንም ። ወደ ሕውሃት ቀለበት አይውሰደን እንጂ የትም ብንገባ ግድ አልነበረንም ።

ራሺያና ቤላሩስ ድንበር ስንደርስ መኪናዎቹ በቅፅበት ዋናውን መንገድ በመልቀቅ ወደ መንደሮች ውስጥ በመግባት ጥቂት እንደተጓዝን እንድንወርድ ተነገረን ። ለሚስጢራዊነቱ ተብሎ ስለሚደረገው ነገር አንዳችም መረጃ ስለማይነገረን የሚሉትን ከመፈፀም ውጪ ምንም አይነት ጥያቄ ማቅረብ አልተፈቀደልንም ። በኋላ ግን ከሞስኮ ድረስ ተልኮ እኛን እንዲታደገን አንድ አበሻ በአንደኛው መኪና ውስጥ እንደነበር አስተዋልኩ ። ምንም ጊዜ ሳናባክን አንደኛው ራሺያዊ የለበሰውን ልብስ ሙሉ ለሙሉ አውልቆ ወገቡ ድረስ የሚደርስ የፕላስቲክ ሱሪና ቦቲ ጫማ እየተጣደፈ ሲያጠልቅ ምን ሊከተል ነው በሚል እንደ ተዓምር አፍጥጠን እየተመለከትነው ነበር ። ወዲያውም በሌላ ፍጥነት ገጀራውን አውጥቶ እንድንከተለው በምልክት መመሪያ ሰጠን ። በዚህን ሰዓት ሁላችንም ምን እየተደረገ ይሆን በሚል እርስ በርሳችን ተያየን ። ሁኔታችንን የተረዳው ከሞስኮ እኛን ለመርዳት የመጣው አበሻ የቤላሩስን ድንበር አቋርጠን ለመውጣት የተሻለው መንገድ ይህ በመሆኑ ሰውየው የሚለንን ያለ አንዳች ማመንታት በተገቢው ፍጥነት ተግባራዊ እንድናደርግ አስረዳን ። ድንበሩን በሰላም እንዳቋረጥንና ወደ ራሺያ ድንበር ከተሻገር ሌላ መኪና እንደሚጠብቀንም ጨምሮ አሳወቀን ። ሁኔታው ግልፅ ሲሆንልን መሪያችንን በልበ ሙሉነት መከተል ያዝን ። መንገዳችን ምን ሊመስል እንደሚችል ከሚመራን ሰው አለባበስና ከያዘው ገጀራ መገመት ችያለሁ ። ሰውዬው እኛን በመምራት በፍጥነት እየተጓዘ ከፊት ለፊቱ ያለውን ጥቅጥቅ ያለ ጥሻ በገጀራው እየቆራረጠ ያፀዳልናል ። እንዲህ እየተከተልነው እያለን ጢሻው ገለል ሲል እስከ ደረታችን

የሚያሰጥመን የረጋ ውሃ ውስጥ መሪያችንን ተከትለን ገባን ። መሪያችን ለምን የፕላስቲክ ሱሪ እንደለበሰና ቦቲ ጫማ እንዳጠለቀ አሁን ግልፅ ሆነልን ። አማራጭ የለም እስከ ደረታችን የሚያሰጥመን ውሃ ውስጥ በመግባት የቻልነውን ያክል አካላችንን መጐተት ጀመርን ። ወደ ውስጥ እየዘለቅን ስንሄድ የረጋው ውሃ መጥፎ ሽታና ክርፋት አላስተነፍሰን አለ ። ነፍሳችንን ለማዳን የምናደርገው ጥረት ነውና የመሪያችንን ዱካ ይዘን በብርታት ተከተልነው ። በዚህ ዓይነት ለአንድ ሰዓት ያክል በእግር እንደተጓዝን የቤላሩስን ግዛት ተሻግረን የሩስያ ምድር ላይ አረፍን ። መሪያችን ይህ የቆምንበት መሬት የሩስያ ግዛት በመሆኑና ጉዞው ስላደከመን ተረጋግተን እንድናርፍ አደረገን ።

ሱ-27 ተዋጊ ጀት አውሮፕላን

ከቤላሩስ ለቀን ሌላ አማራጭና የተሻለ ይሆናል በተባለው የሩስያ ግዛት መገኘታችን የተሻለ ተስፋ አለው ብዬ ባምንም መጨረሻችን ምን ሊሆን እንደሚችል ሳላውቅ ልረጋጋ አልቻልኩም ። እረፍት አድርጉ ብንባልም ለአካላችን ካልሆነ በስተቀር አእምሯችንን ከጭንቀት ሊያሳርፍ የሚችል ምዕራፍ ላይ ገና አልደረስንም ።

ትንሽ ከድካማችን ስናገግም ይጠብቃቹሃል የተባልነው መኪና እየቀረበን ሲመጣ አስተዋልኩ ። አንድ ሌላ ሁለተኛ አበሻ አብሮ መጥቷል ። በሶስት መኪና መሆናችን ቀርቶ ሁላችንም በአንድ መኪና ውስጥ እንድንገባ አደረገን ። አበሾቹ ወንድሞቻችን ሕይወታችንን ለማዳን የሚያደርጉልን ጥረት ፣ እየወሰዱት ያሉት አደገኛ ግዳጅ ውስጤን በእጅጉ አበረታኝ ። ኢትዮጵያ መቼም ቢሆን የሚታደጋትና ክፉዋን መስማት የማይፈልጉ ዜጐች በዓለም ዙርያ መኖራቸው በኢትዮጵያዊነቴ ኰራሁ ። ይህ ወንድማችን እየደጋገመ አይዟችሁ ይለናል ። ያበረታታናል ። ቅንነቱና እያደረገ ያለው ከልቡ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻል ነበር ። እናም ጥርጣሬዬ ቀስ በቀስ ከውስጤ እየበነነ ሲሄድና ያ ተለጉም የነበረው አንደበታችን ሲከፈት አንድ ሆነ ። በደስታ ማውካካት ጀመርን ። በጉዟችን አቋርጠን የመጣነው መንገድ አስከፊነትና አሁን ያለንበት ሰላማዊ መሬት ላይ እንድንደርስ የረዱንን ሁሉ በአድናቆት ከበሬታ ሰጠናቸው ።

ሞስኰ እንደገባን ለአንድ ወር ከሆቴል ሳንወጣ ተደብቀን ቆየን ። ***ኢትዮጵያውያኑ ሕይወታችንን ከመታደጋቸውም በላይ እያደረጉልን ያለው እንክብካቤ በቃላት ለመግለፅ ያስቸግራል ። ገንዘባቸውን ፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን እንዲሁም ደህንነታቸውን ጭምር ነበር መስዋዕት እያደረጉልን የነበሩት ። ለእኔ የዕድሜ ልክ ባለውለታዎቼ ናቸው ። ይህንን ሁሉ መስዋዕትነት ከፍለው አሁን ለአለንበት ሰላማዊ አየር ያደረሱን ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ያሉት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን የዕድሜ ልክ ዕዳ ተሸክሚያለሁ ። በተግባር እነሱ ለሰብዓዊነት የከፈሉት መስዋዕትነት እኔ ተራ ደርሶኝ እስካልከፈልኩ ድረስ በቃላት የምገልፀው ምስጋና ይበቃቸዋል ብዬ አላምንም ። እግዚአብሄር በያሉበት ሰላማቸውን እንዲያበዛ የዘወትር ፀሎቴ ነው ። ወገን ምን ማለት እንደሆነ ፣ የኢትዮጵያዊነት ጥልቅ ሚስጢር ፣ የወገን አለኝታነትን በአንድ ላይ በመስዋዕትነታቸው አስተምረውኛልና ።***

ከአንድ ወር በኋላ ሞስኰ ወዳለው የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኰሚሽን (UNHCR) ቢሮ በመሄድ ማመልከት ነበረብን ። ኬላ ሰብረን በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ራሺያ በመግባታችን ምክንያት ጉዳያችንን ላይቀበሉ ይችላሉ ብዬ ሰግቻለሁ ። ይሁን እንጂ እንደፈራሁት ሳይሆን የስደተኛው ኰሚሽን አቤቱታችንን ወዲያ ተቀበለው ። ወዲያውም ወደ ሌላ ሶስተኛ አገር በማሸጋገር በሰላም መኖር የምንችልበት ሁኔታ በአፋጣኝ እንደሚያመቻቹና ረዥም ጊዜም እንደማይፈጅ ሲነግሩን ለአምላኬ ምስጋናዬን አቀረብኩ ።

ሞስኰ ያሳለፍኩት ግዜ በግሌ አስቸጋሪና ብዙ ውጣ ውረዶች የበዙበት ቢሆንም ሕይወት እንዲህ ናትና በቀና ተቀብዬዋለሁ ። እራሳችንን ሙሉ ለሙሉ ለመርዳት ያልደረስን ጥገኞች ነበርንና የሞስኰ ወገኖቻችን እንዲሁም ከአሜሪካ ግዛት የሚደረግልን ድጋፍ ውስጤን ይከብደው ነበር ። እኛን ተከትሎ አየር ኃይሉ በሙያተኞች ያልተቋረጠ የስደት ወጀብ ውስጥ ነበርና እነዚህ ወገኖቻችን እነዚህን ሁሉ ስደተኞች የሚረዱበት አቅም ውስጤን ይበላዋል ። እኛ በቶሎ ነፃ ልናደርጋቸው ይገባል እያልኩ እጨነቃለሁ ። በመሆኑም ከስደተኞቹ ቢሮ ጋር በቅርበት እየተገናኘን ጉዳያችንን መከታተል ጀመርን ። እግዚአብሄር ደግ ነው ። ጉዳያችን በአፋጣኝ ተከናውኖ ወደ ሶስተኛና ነፃ አገር ያለ አንዳች ችግር መዛወር ቻልን ።

ዛሬ ፈተናው ሁሉ አልፏል ፣ አምላክ በሶስት ልጆች ባርኰኝ ኑሮዬን እየገፋሁ ነው ። ት/ቤት በመግባትም በጤናው ዘርፍ አንድ የመጀመሪያ ዲግሪና ሁለት የማስተርስ ዲግሪ በመያዝ

ሙያ ቀይሬ በጥሩ ኑሮ ላይ እገኛለሁ ። አገሬ ግን በልቤ ውስጥ ትልቅ ስፍራ እንደያዘች አለች ። ሁሌም ሰላሟንና ደህንነቷን እመኛለሁ ። ሕዝቧም ሳይለያይ አንድነቱን ጠብቆ እንዲኖር ፀሎቴ ነው ።

የመጀመሪያ ደረጃ በረራ ስኳድሮን ውስጥ

አየር ኃይልን ሳስብ በእጅጉ እተክዛለሁ ። በዚህ አካሄድ የትም መድረስ እንደማይቻል ሳስብ ለአገሬ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ አምርሬ አዝናለሁ ። እንደዚያ በልጅነት የማልመውን ሙያ አግኝቼ ሳልጠግበው ተገድጄ ማቋረጤ የውስጥ ሕመሜ እንደሆነ አለ ።

አገራችን የተወሰኑ ሰዎች ብቻ አይደለችም ። እናድርጋትም ቢባል ሊሆን የሚችል ጉዳይ አይደለም ። ይልቁንስ የአገራችን እጣ ፋንታ በመዳፋቸው ውስጥ የወደቀ አካላት አበክረው ሊያስቡበት የሚገባው ጉዳይ በስልጣን ከሚገኘው ደስታና ሃሴት ባሻገር የሕዝብና የአገር ኃላፊነት ሊከብዳቸው ይገባል ።

በመጨረሻም አሁን ላለንበት ሕይወት እንድንደርስ ለረዱንና ለታደጉን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ሁሉ በቃላት መግለፅ የማልችለውን ምስጋና በድጋሚ ለማቅረብ እወዳለሁ ። ጊዚያቸውን ፣ ገንዘባቸውንና ዕውቀታቸውን መስዋዕት አድርገውልናልና ፈጣሪ ውለታቸውን ይክፈላቸው ።

ከአክብሮት ጋር

ፋሲል ማሞ

Fotoscanner från Google Foto

ሚግ-23 ከሶሎ በረራ በኋላ

Fotoscanner från Google Foto

የእናት ባለ አዳራ

ኖላዊት

እንደ ሰባሰገል በላይ በሰማያት ኮከብ የቆጠረው ፣

በአቬየሽን ታሪክ የቀስተደመናን ጮራን የፈጠረው ፣

ከፍ ዝቅ እያለ ጠላት አስረግዶ ከድባቅ ያኖረው ።

ከቤተሰቡ ጋር ደምቆና አሸብርቆ ፣

ለዚህ ላደረሰው ምስጋናን ሰንቆ ፣

ጀግናው ሲያትል ላይ ፣ ይኸው ተገናኘ አመቱን ጠብቆ ።

በረጅሙ ጉዞ የህይወት መርከብ ላይ ፣

ማዕበል ቢያናውጠው ቢንሳፈፍም ከላይ ።

ያንተ ትብስነት የሃገር ልጅ ወዙን ጣዕሙን ያላጣ ፣

ታሪክ ማ'ያዛናፍ ከቀዬው ቢርቅም ካገሩ ቢወጣ ፣

የቀድሞው አየርኃይል ኩራት ማቴቤ ነው ነፍሴ እስክትወጣ ።

እንደው ለትውስታ ለዕለቱ ጨዋታ ፣

እስኪ ልነካካው ያንን ቤት በሩቁ ፣

የተኙት ጀግኖቼ ሰምተው እንዳይነቁ ።

ከላይ ከአርያም ከትልቁ ማማ ፣

ዛሬም የነገሱ በልባችን አርማ ፣

***አሰፋ አየነ** እውቀትን አፍላቂ ፣*

***አበራ ወ\ማርያም** ጨዋታን አዋቂ ።*

***ታዬ ጥላሁንም** ልዩነው ፍቅራቸው ፣*

***ዮሃንስ** ሲወሳ የእነአለማየሁ ይበራል ፊታቸው ።*

እናንት ውድ አዛዦች ብርቱ ጀነራሎች ፣

አልፋ ናችሁና ፈርቀዳጅ አሻራ ፣ የእናት ባላዳራ ፣

ነፍሳችሁ ትሰለፍ ከአብረሃም ከይሳቅ ከነ ያዕቆብ ጋራ ። (2)

እንደው ግና ግና እናንት ውድ አንበሶች

የአገሬ መከታ ጋሻዋ ጦሯና ህያው ምስክሮች ።

አንድ ህመም ነበረኝ እኔን ያሰቃየኝ ፣

እናንት የጥንቶቹን ባገኝሁ ያስባለኝ ፣

*እነ **አምሃ ደስታን ገናናው መንግሱቱን** ፤*

የቁርጥ ቀን ልጆች ሽንፈት ያላሳዩን ።

*ምንስ ብሎ ይሆን እንደው **ተስፉ ደስታ** ፣*

*ወኔው ያልበረደ **የበላይ ልጅ ፋንታ** ፣*

ቆራጥ ልበሙሉ የወገን አለኝታ ።

*ምናል ቀና ብትል **ለገሰ ተፈራ** ፣*

ዶጋ አመድ ያረከው የጠላትን ጎራ ።

*ጦሩን የመከተው **ሰለሞን በጋሻው** ፣*

*ምን መሬት ቻለቸው **ንጉስዬ ዘርጋው** ።*

መቼም ጎዶሎ ነው በስደት ካለፉ ፣

ሆዱ የማይራራ ካገር ለተገፉ ፣

ቀንን ለማሳለፍ ቢገቡ መዳፉ ፣

ሞት ፅዋን ደገሰ እርመ በላው ክፉ ።

***አሰፋና ከበደን ታከለን** እንዳ'ናይ*

***በነጥግነህ** ላይ፣*

***በነአለማየሁ** ላይ፤*

***በነዘበነ** ላይ*

ምን'ዳስ ጣለባቸው በምድር በሰማይ ።

ግዳጅ ዓይኑ ይጥፉ ካልገበው ውለታ ፣

*ሁለት **ጥላሁንን** ከቀማን ባንዳፍታ ።*

ይኸው ደስ ይበልህ እኔ አላውቅም ስቄ ፣

*ሁሌ ትዝ ይለኛል ደጉ **አብርሃም ስንቄ** ።*

***አበበ አቤቤና ጌታቸው ምህርቴ** ፣*

ሰማይ ቤት ምናለ? ንገሩኝ በሞቴ ።

*ታማኝ አገልጋዩ ባጫና መንግስቱ **ባህሩና ካሳዬ** ፣*

*የነ**ጌታሁንን መርዕድና አማኑኤል** እንዲሁም **ተስፋዬ** ።*

ቤታቸው ሲጨቀይ በነፍረደ ገምድል ፣

አደራው ሲበላ በአድርባዮች ጠብደል ።

ታሪክ ሲቀለበስ ማድጋው ሲናወጥ ፣

አቧራው ባህሩ በደም ሲበጠበጥ ።

ኧረ'ናንተ ጀግኖች በስደት ያላችሁ ፣

እንደምን አንደምን ምንአለ ሆዳችሁ ?

ማን በጠየቀየልኝ እኒያን እንቁ ጌጦች ፣

የአቬየሽኑ ድምቀት የህዝብ መከታዎች ።

ሰላም በማስቀደም የተሰደዳችሁ ፣

የምዬ አንጡራ ይጠበቅ ያላችሁ ።

እውነት በመናገር ፣

የእገረሙቅ ሰለባ ካቴና ያጌጣችሁ ፣

እንደነ ***ግርማ አስፋው*** *ወህኒ የጣሏችሁ ።*

ብርሃነ መስቀል ሰለሞን ከበደ *፣*

ፍስሃ *ና* ***ክፍሌ****ን በአንድ ያዋሃደ ።*

ይመስክር ዘብጥያው ፣

ምን እየሸለመ እንዳስተናገደ ።

ቢሆንም እምዬ .... ፣

ሰማይሽ ጠቋቁሮ መከፋትን ቢያዝልም ፣

አምናለሁ ሀገሬ እኔ ተስፋ አልቆርጥም

ታሪክ ይደገማል ትንሳኤሽ አይርቅም ።

ታዲያ ኢትዮጵያዬ !

ዳግማዊ ትንሳኤሽ እውን የሚሆነው ፣

በግፍ ተገፍትሮ ተበትኖ ያለው ።

እትብት ልጆችሽ በአህጉራት ዳርቻ ፣

በናፍቆት ተጠብሰው በቁጭት ያረሩ ሚ'ኖሩ ለብቻ ፣

ጉያሽ እንዲገቡ ያለዘር ሐይማኖት የጎሳ ሸኩቻ ፣

ከስሩ መንቀል ነው መርዞ የያዘሽን እሾህ አራሙቻ ።

<u>የጄት ኢንጂኑ ሰው</u>

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

አዉሮፕላንን ያለ ሞተሩ ማሰብ አይቻልም ። ሞተሩንም እንዲሁ ያለጠጋኙ። አየር ኃይል ዉስጥ ሞተር ጠጋኝ ከነበሩት ሰዎች መሃከል ማስተር አለማየሁ ዘዉዴ አንዱ ናቸው። የአየር ኃይል አዉሮፕላኖች ሰማይ ላይ እንዲውሉ እሳቸው ከሌሎች የስራ ባልደረባዎቻቸው ጋር ኤንጂን ሾፕ ውስጥ ላብ አፍሰዋል። ሞቱ የተባሉ የአውሮፕላን ሞተሮችን ነብስ የሚዘሩት ኢንጂን ሾፕ ውስጥ ነበርና በታው "ትንሳኤ ሙታን" ተብሎ ይጠራ ነበር ነው ያሉን ማስተሩ።

ማስተር አለማየሁ በትውልድ ሐረርጌ ናቸው። ሀብሮ አውራጃ ወብቻ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከክርስቲያን ቤተሰብ በ 1936 ዓም ተወለዱ። መሪ ጌታ ዘውዴ በየነና እማሆይ ሙሉነሽ በየነ በሕይወት ዘመናቸው ካፈሯቸው ሁለት ልጆች መሃከል አንዱ ናቸው። ሌላዋ ሴት ልጃቸው ዛሬ በትዳር አዲስ አበባ ትኖራለች። ማስተር አለማየሁ አሁን በስደት የሚኖሩት አሜሪካ፣ ሚኔሶታ ውስጥ ነው። ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ወበራ አውራጃ ደደር ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሐረር ከተማ መድሐኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል እያሉ ነው በአየር ኃይል የተመለመሉት። በፈረንጆቹ 1961 ላይ።

ዘጠኝ ሆነው ከሐረር ወደ ደብረ ዘይት የመጡት ወጣቶች ከሌላ ክፍለ ሃገራት ከተመለመሉት ጋር ተቀላቀሉና ኢ-11 የሚል የኮርስ ስም ተሰጣቸው። ኮርሱን ሲጀምሩ 120 ነበሩ። አዲስ ምልምል ስልጠናው ላይ 20 የሚሆኑት ሳይቀናቸው ቀረና 100 ያህሉ የሚሰጠውን የሁለት ዓመት ኮርስ ሥልጠና አጠናቀው ተመረቁ።

አንድ በወሬ ደረጃ የሰማነው ነገር ግን ያላረጋገጥነውን ጉዳይ በተመለከተ ማስተሩን መጠየቅ ነበረብን። በወሬ ደረጃ ሰምታችሁ ከሆነ ዱሮዱሮ አየር ኃይል ምግብ ቤት ውስጥ ወተት በቧንቧ ይቀርብ ነበር ይባላል። ታዲያ ይህ ዕውነት ከሆነ ማስተር አለማየሁ ለዚህ ምስክር መሆን አለባቸው በሚል ይሄ ዕውነት ነው? ብለን ጠየቅናቸው። እንደ ውሃ ከቧንቧም ባይሆን በትልቅ ኮንቴነር ውስጥ ሆኖ እንደ ሻይና ቡና በብርጭቆ እየተቀዳ ይጠጣ ነበር አሉን። ያ ታዲያ እያንዳንዱ እንደፍላጎቱ የሚሉት አይነት ነበር። በእኛ ዘመን በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የሰማነውን ኮምኒዝም የሚመስል ነገር አያስታውሳችሁም?

ጃንሆይ አርብአርብ አየር ኃይል እየመጡ አባላቱ የሚበሉትን እራሳቸው በግል ይከታተሉ ነበር። ሠንጋም ይታረዳል። አንዳንዴም ከቤተመንግስት ጠጅና ቁርጥ እንዲሁ ለሠራዊቱ ይላክ እንደነበር ነው ማስተር አለማየሁ ያጫወቱን። ያ "የትፍስህተ - ገነት ዘመን"በአየር ኃይል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ። የሚገረመው ነገር አየር ኃይል በዚህ ተደልሎ የኖረበት ዘመን አልነበረም። ምንጊዜም ለፍትህ፣ ለዕኩልነትና ለለውጥ እንደባተ ነው የኖረው።

ማስተር አለማየሁ መሰረታዊውን የአውሮፕላን ሞተር ጥገና ትምህርት አጠናቀው እንደተመረቁ ኤንጂን ሾፕ በመመስረት ላይ ነበር። እሳቸውም ወዲያው ለትምህርት ወደ አሜሪካ መላካቸውን ነግረውናል። በአሜሪካንም ስዩም ከሚባል ጓደኛቸው ጋር ቱልሳ ኦክላሆማ ኤሮናቲክ ትምህርት ቤት ሲማሩ ቆይተው ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ወደ ሃገራቸው ይመለሳሉ። ማስተር አለማየሁ ለረዥም ዘመን የተለያዩ የረሲፕ ኢንጂኖች ጥገና ላይ ከሰሩ በኋላ ወደ ትሬኒግ ተዛውረው ለ17 ዓመት አስተምረዋል። ከ 800 በላይ የሆኑ ተማሪዎችንም በቴክኒክና በኦኖቲክ ሙያ አሰልጥነው አስመርቀዋል። በዚህ ሁሉ መሃከልም በጊዜያዊ የስራ ምደባ (ቲዲ ዋይ) በሁሉም አየር ኃይል ዋና እና ንኡስ ጣቢያዎች ሁሉ በመሄድ አገልግሎት ሰጥተዋል። በ1974 አየር ኃይሉ ወደ ሶቪዬት ሲስተም እንደገባም ለሰባት ወር ወደ ሶቪዬት ሕብረት ተልከው ከሞስኮ 175 ማይልስ ርቀት ላይ በምትገኘው ኢቫኖቭ ከተማ በአንቶኖቭ 12 ላይ ሰልጥነው ተመልሰዋል።

አየር ኃይል በወግ በማዕረግ ከዳራቸው ሰዎች ማሃከል ማስተር አለማየሁ አንዱ ናቸው። በእሳቸው ዘመን ሚስት ለማግባት የተዘጋጀ የአየር ኃይል አባል በቅድሚያ ለመሬጅ ኮሚቴ ማመልከቻ ማስገባት ይጠበቅበታል። በጠቅላይ መምሪያ ስር የሚተዳደር ኮሚቴ ነበር። እርግጠኛ ነኝ ይህንን እንደ እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማችሁ መደነቃችሁ አይቀርም። ታዲያ ማስተሩ ቤተሰብ ያጨላቸውን ኮረዳ የሕይወት ታሪክ ለኮሚቴው ያቀርቡና ኮሚቴውም ኮረዳዋንና ቤተሰቧን አነጋግሮ ለትዳር ብቁ መሆኗን ያረጋግጣል። ከዚያም እሳቸውም እንዲሁ ትዳር ለመመስረት ዝግጁ መሆናቸው ተጠናና መጨረሻ ላይ የኮሚቴውን አወንታ ያገኛሉ ። ከዚህ በኋላ ነው ሠርጉ በ1962 ላይ ተደግሶ ጉሮ ወሸባዬ የተባለው ። ጥሩ ባሕል ነበር አትሉም? ለዚህ ይሆን የእዛ ዘመን ትዳር በረከት የሞላበት። አየር ኃይል ቤታችን፣ አባት እናታችን እያልን የምንለው አለምክንያት አለመሆኑን በዚህ መገንዘብ ይቻላል።

ማስተሩ እስካሁን ከትዳር ጓደኛው ጋር በደስታ ሲኖሩ 48ኛ ዓመታቸውን ይዘዋል። በነገራችን ላይ የትዳር ኮሚቴው ላፀደቀው ጋብቻ የትዳር አልዋንስም ይሰጥ ነበር።በዚያን ዘመን ከሁለት እስከ ሶስት መቶ ብር ይደርስ እንደነበረ ማስተር አለማየሁ አጫውተውናል። ይህን አለዋንስ በሕጋዊ ደረጃ የፈጸመ የአየር ኃይል አባል ሁሉ ያገኝ ነበር። በዚህ መልክ ከማስተር አለማየሁ ጋር ሶስት ጉልቻ የመሰረቱት ወይዘሮ መንደሪን ገብረጻዲቅ ከባለቤታቸው ጋር አንድ ሴትና አራት ወንድ ልጆች አፍርተዋል። ማስተር አለማየሁ ቀደም ብለው ከትዳር በፊት የወለዱት ሌላ አንድ ወንድ ልጅም አላቸው። በነገራችን ላይ ወይዘሮ መንደሪን አየር ኃይል ውስጥ በኮንትራት ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበረ የተረዳነው በዚሁ ቃለ-መጠይቅ ጊዜ ነበር።

ማሰተር አለማየሁ ዘውዴ አየር ኃይልን ለሰላሳ ዓመታት ያህል ሲያገለግሉ አንድም ቀን አየር ኃይል በመሆናቸው የተጸጸቱበት ቀን የለም። እንዲያውም በአየር ኃይል አባልነታቸው ይኮራሉ። በአዛዦችና በሠራዊቱ መሃከል የነበረውን ፍቅርና መከባበር አሁንም ያስታውሳሉ። እንደ አብዛኛው አባላት ሁሉም የተሰጠውን ስራ ከላይ እስከታች በፍቅር በመከባበር ከመስራት በስተቀር አንዳችም ቅሬታ አልነበረም። ከጄኔራል ፋንታና አምሃ ጋር ቅርጫት ኳስ ወይንም እግር ኳስ የመጫወት አጋጣሚውንም አግኝተው ይሆናል።

አንድ መጥፎ ቀን ያስታዉሱ እንደሆን ጠይቀናቸው። ባለፈው ዕትማችን ላይ "ሐረር ሜዳ ከዕለታት አንድ ቀን" በሚል ርዕስ ባወጣነው ጽሑፍ ላይ የተረከነውን ቀን ጠቀሱልን። ቀውጢ ሊሆን የሚችል ቀን እንደነበር ያስታውሳሉ።

የአየር ኃይል ሠራዊት በሶማሌ ጦርነት ጊዜ በሃገር የማዳን ግብግብ ውስጥ ያሳየው ተጋድሎና የከፈለው መስዋትነት በማስተሩ ልብ ውስጥ የተለየ ቦታ አለው። የአየር ኃይል ማሕበራዊ ሕይወትን በተመለከተም ዛሬም የማይዘነጉት አጋጣሚ አለ። በአንድ ወቅት በጄኔራል አበበ ወልደ ማርያም አዛዥነት ዘመን በተዘጋጀው የጫካ ውስጥ ግብዣ ላይ በጥሪ የተገኙት የተለያየ የጦር ክፍል ታዳሚዎች የአየር ኃይል ሠራዊት አንድነት፣ ፍቅርና መከባበር ምን ያህል እንደሆነ አይተው አዛዦችን ከታዛዥ መለየት ያልተቻላቸው ወቅት ነበር።

ማስተር አለማየሁ በአሁኑ ወቅት በሚኒሶታ አስር ቤተሰብ አባላት ያሉበት የቀድሞው አየር ኃይል አባላት ማሕበር ከሌሎች ጋር መስርተው መንቀሳቀስ ከጀመሩ አስር ዓመታት ሆኗል። ወደፊት ይህንን ማሕበር በይበልጥ የማጠናከር ዕቅድም አላቸው። በቃለ መጠይቃችን መገባደጃ ላይ ከጎናቸው እንደምንቆም ቃል ገብተናል። እሳቸውም ለዓለም አቀፉ

የቀድሞው አየር ኃይል አባላት ሕብረት ያላቸውን በጎ ምኞትና ምስጋና ከመናገር አልተቆጠቡም። ወደ ሚኒሶታ ብቅ የምትሉ ሰዎች ፋሲካ ምግብ ቤት ብትሄዱ እሳቸዉንና ባለቤታቸውን ልታገኙ ትችላላችሁ። በባለሙያ እጅ የተሰናዳ ምግብ የመመገብ ዕድሉም ይኖራችኋል ።

------------///------------

ቴክኒሻኖች በዕለት ተዕለት ስራቸው ላይ

ያልተሳካው መፈንቅለ መንግስት

ሳምሶን ብዙወርቅ

ግንቦት ፰ ቀን ሺህ ፱፻፹፩ ዓ/ም

፪ኛው አየር ምድብ

ዮሐንሥ ፬ኛ አየር ማረፊያ

አሥመራ

አስመራ አየር ማረፍያ የግንቦት ጸሐይ ክርር ብላ ወጥታ አናት መነጥረቁን ተያይዛዋለች ። እያለፈ የሚነፍሰው ነፋስ ሊያቀዘቅዘው ቢሞክርም የመሬቱ ንዳድ መልሶ ወላፈን እየፈጠረ ወደ ላይ ይጋረፋል ።

የሁለተኛው አየር ምድብ አባላት ወታደራዊ የስራ ልብሶቻቸውን ለብሰው ዕለታዊ ተግባራቸውን ለመከወን ከወዲያ ከወዲህ ይጣደፋሉ ። ከተለያዩ አውሮፕላኖች የሚወጣው የሞተር ድምጽ አካባቢውን ያናጋዋል ። በየመሃሉ እንደ ነጎድጓድ የጆሮ ታምቡር እስኪቀደድ የሚሰማው የሚግ ሃያ አንድ እና ሃያ ሶስት ተዋጊ አውሮፕላኖች የሞተር ድምጽ ግን ከሁሉም በላይ ጎልቶ እኔን ካልሰማችሁኝ የሚል ይመስላል።

ልብ ብሎ ላስተዋለው የሙዚቃ ጠበብት የተቀኙበት የኦፕራ ሜሎዲ ይመስል አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ እያለ የታዳሚን ቀልብ ለመሳብ እንጂ በዘፈቀደ የሚጮህ የአሮፕላን ሞተር ድምፅ አይመስልም ።

ሞቃታማው አየር በውስጡ የሚናኘውን የጄት ሞተር ጭስ ለመበተን በአራቱም ማዕዘናት መንፈሱን ቀጥሏል ። በዚህ በተለመደው የዕለት ተዕለት ተውኔት ታጅቦ በነጭ መደብ ላይ ደማቅ ሰማያዊ ቀለም አግድም የተሰመረበት ፣ በጭራው ላይ በትልቁ የአገሪቱን ሰንደቅ ዓላማ (አረንጓዴ ቢጫና ቀይ) የተሸከመው ሽንጠ ረዥሙ የቀድሞዋ ሶቪየት ሰራሽ ቱዩ 154 የመንገደኞች አውሮፕላን በርካታ መንገደኞችንና ወታደራዊ ቁሳቁሶችን ጭኖ ከደብረ ዘይት ሐረር ሜዳ በመነሳት አስመራ አየር ማረፊያ ከተፍ አለ ።

ይህ የመጓጓዣ አውሮፕላን ከቀድሞዋ የሶቪየት ሕብረት መሪ ከጓድ ሊዮኒዮድ ብሬዥኔቭ ለጓድ መንግስቱ ኃ/ማሪያም በስጦታ የተበረከተላቸው ነበር ። ይሁን እንጂ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ይህንን አውሮፕላን ከመጎብኘት ባለፈ አንድም ቀን ሲገለገሉበት አልታዩም ። በተመሳሳይ ሁኔታ የሞዛምቢክ መሪ የነበሩት ጓድ ሳሞራ ማሼል ከሶቭዬት ሕብረት በተበረከተላቸው አውሮፕላን ሕይወታቸው በማለፉና አደጋውም በኬጂቢ እንደተቀነባበረ ከሃሜት የዘለለ ጥርጣሬ ይናፈስ ስለነበር የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በሞዛምቢኩ መሪ ላይ የደረሰውን አደጋ በመሸሽ ይመስላል በአውሮፕላኑ ለመገልገል ፈቃደኛ አልሆኑም ። እንደ አማራጭም ለኢትዮጵያ አየር ኃይል በስጦታ ተበርክቶ በየሳምንቱ ማክሰኞ ወደ አስመራ ፣ ሐሙስ ደግሞ ወደ ድሬዳዋ የአየር ኃይልን ሰራዊት እና ቤተሰብ እንዲያጓጉዝ ተደርጓል ። እነሆ ዛሬም በመደበኛ ፕሮግራሙ ዕለት ማክሰኞን ጠብቆ ከደብረዘይት በመነሳት አስመራ ሁለተኛው አየር ምድብ በሰዓቱ አርፎ በውስጡ የነበሩትን መንገደኞች እያራገፈ ነው ።

በወታደራዊው ደንብ መሰረት ከፍተኛ መኮንኖች ቅድሚያ በማግኘት ከአውሮፕላኑ ይወርዱና ሌላው የሰራዊቱ አባል በተዋረድ ከአውሮፕላኑ ይወጣል ። በዘፈቀደ እየተጋፉ መውረድና ስርዓቱን ማዛነፍ ወታደራዊው ስነምግባር አይፈቅድም ። ዛሬም በዚህ በረራ ውስጥ ካሉት ከፍተኛ መኮንኖች መካከል የሁለተኛው አየር ምድብ አዛዥ ብርጋዴር ጄነራል ንጉሴ ዘርጋውና ሌሎች ከአንደኛው አየር ምድብ ለአጭር ጊዜ የስራ ቆይታ ወደ አስመራ የመጡ ሁለት የአየር ኃይል ጄኔራሎች ከሁሉም ቀድመው በመወጣጫው መሰላል በኩል ብቅ አሉ ። ጄነራል ንጉሴ

ዘለግ ያለ ቁመናና ግርማ ሞገስ ያላቸው ፤ በሰራዊቱ እጅግ የተወደዱና እንደ አባት የሚታዩ አዛዥ መኰንን ናቸው ።

ከመንገደኞች መውረድ በኋላ ደብዳቤ የመጣለትና ጓደኛውን ያገኘ ፣ እንዲሁም የመሃል አገር ወሬ ለመስማት የጓጓ ሁሉ ወደየ ካፊቴሪያውና ወደየ ክበቡ ሲበተን እኔም በዕለቱ ሊካሄድ ወደ ታሰበው ስብሰባ አመራሁ ። ስብሰባው በየዓመቱ ስለሚከበረው የአየር ምድቡ ቀን በዝግጅት ኮሚቴነት የተመረጥን አባላት ከአየር ምድቡ አዛዥ ጋር ለመወያየት ነበር ። ሆኖም ባልታወቀ ምክንያት አዛዡ ሊገኙ አልቻሉምና ስብሰባው ለሌላ ጊዜ እንደ ተዛወረ ተነግሮን ወደ የስራ ክፍላችን ተመለስን ።

ወደ በረራ መስመር ስመለስ ወታደራዊ ተርሚናል አካባቢ ከወትሮው ለየት ያለ እንቅስቃሴና ግርግር አስተዋልኩኝ ። በዚህ ያልተለመደ ሁኔታም ቀልቤ በመሳቡ ሁኔታዎችን በጥርጣሬ መከታተል ጀመርኩ ።

አስመራ በቅፅበት ውስጥ ምን ሊያጋጥምህ እንደሚችል አታውቅም ። አትኩሮት ፣ ጥርጣሬና ጥንቃቄ የዘወትር መመሪያህ ሊሆኑ ይገባል ። ድንገት ኃይለኛ ፍንዳታ አካባቢህን ሊያሸብረው ይችላል ። የረዥም ርቀት ሮኬት ፍንጣሪም አካባቢህን ሲደረምሰው ልትመለከት ትችላለህ ። በአንድነት ተቀላቅለን እንኑር እንጂ ማን ማንንና መቼ እንደሚከዳ ማወቅ አዳጋች ከሆነ ሰነባብቷል ። እናም ይህ ወታደራዊ ተርሚናል አካባቢ የሚታየው ለየት ያለ እንቅስቃሴ ጤና ስለነሳኝ ነገሮችን በአንክሮ ማስተዋል ቀጠልኩ ።

ለወትሮው ከምሳ በፊት አስመራ የመጣው አውሮፕላን ወደ ደብረዘይት ተጓዥ መንገደኞችን ይዞ መመለስ ነበረበት ። ዛሬ ግን በጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ (የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት ም/አዛዥ) የሚመራ ልዩ ኮማንዶ ጦር ከነሙሉ ትጥቁ በጥድፊያ ሲጫን አስተዋልኩ ። በዚህ ለየት ያለ እንቅስቃሴ የራሴን መላምት ከመስጠት ያለፈ ምንም አይነት መረጃ አልነበረኝም ። ከቲዩ-154 (TU-154) ተከትሎም አንድ ተጨማሪ አንቶኖቭ-12 ወታደራዊ ማጓጓዣም በተመሳሳይ መልኩ ልዩ ኮማንዶዎችን በጥድፍያ ሲጫን በመመልከቴ በጥብቅ ምስጢር የተያዘ ዘመቻ እየተከናወነ እንደሆነ ልቤ ጠረጠረ ።

የጊዜ ዑደት ሆኖ ጀምበር ወደ ምእራብ አቅጣጫ ጉዞዋን ስታፋጥን የቀኑ ሙቀትም አብሯት ጉዞ የጀመረ ይመስል አየሩ መቀዝቀዝ ጀምሯል ። ሁለቱም ግዙፋን የማጓጓዣ አውሮፕላኖች ኰማንዶዎቹን ጭነው እንደአበቁ ጨለማው ከመንገሱ በፊት አስመራ "ዮሃንስ አራተኛ" አየር ማረፊያን ለቀው ተነሱ ። የሞተራቸው ድምፅ ከጆሮዬ እስኪርቅና ከዓይኔ ዕይታ እስኪጠፉ ድረስ በስስት ተመለከትኳቸው ። ይህ ምስጢራዊ በረራ ወዴት ይሆን የሚለውን ጥያቄ እንደያዝኩ አቅጣጫዬን ወደ ኤርሜን ክበብ አደረኩ ።

በአየር ኃይል ውስጥ የክፍል አወቃቀርን (status) መሰረት አድርገው የተቋቋሙ የሰራዊቱ መገልገያ ክበቦች አሉ ። እነዚህም

***የመኰንኖች ክበብ** - በዚህ ክበብ ውስጥ ከምክትል መቶ አለቃ እስከ ጄነራል ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች የሚገለገሉበት ነው*

***ቴክኒሽያን ክበብ** - ባለ ሌላ ማዕረግተኛ የቴክኒክ ሙያተኞችን ያካተተ ሲሆን ከጁኒየር ቴክኒሽያን እስከ ማስተር ቴክኒሻን ያሉ የሰራዊቱ አባላት ይገለገሉበታል ።*

***ኤርሜን ክበብ** - ወጣቶች (ጁንየር) ባለ ሌላ ማዕረግተኛ የቴክኒክ ሙያተኞች ከጁኒየር ኤርክራፍት ማን እስከ ሊዲንግ ኤርክራፍት ማን ድረስ የሚገለገሉበት*

***የካዴት ከበብ** - በመኰንነት ለመመረቅ ገና በስልጠና (በትምህርት) ላይ ያሉ ካዴቶች (ዕጩ መኰንኖች) የሚገለገሉበት ነው ።*

***ተማሪዎች ክበብ** - በትምህርት ላይ ያሉ አፕሬንቲስ ወጣት ተማሪዎች የሚገለገሉበት ሲሆን*

***የኤር ፖሊስ ክበብ** - በአየር ኃይሉ ውስጥ በጥበቃና በተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ላይ ያሉ የአየር ኃይል ፖሊስ ክፍል የሚገለገልበት ክበብ ነው ።*

በአንድ ዓይነት ስታተስ ስር ያሉ የሰራዊቱ አባላት ካልሆኑ በስተቀር አንደኛው ወደ ሌላኛው ክበብ ገብቶ መገልገል አይችልም ። ሁሉም በየራሱ ካታጐሪ እየተሰባሰበ አብሮ

ይውላል ። ይህ አሰራር የአየር ኃይሉን ወታደራዊ የአዛዥነት የዕዝ ጠገግና አሰራር በሚገባ ሚዛኑን ጠብቆ እንዲሄድ ይረዳል ተብሎ ይታሰባል ። ለረዥም ዓመታትም በሰራዊቱ ውስጥ ተግባራዊ ሆኖ ኖሯል ። ጨዋታን ጨዋታ ያነሳዋልና ስለአየር ኃይል ክበብ ካነሳሁ አይቀር አንዲት አጋጣሚን አንስቼ ልለፍ ።

ቲዩ-154 የመንገደኞች አውሮፕላን

አስመራ ሁለተኛው አየር ምድብ አካባቢ በስራ አጋጣሚ በተደጋጋሚ የሚመላለስ በስም የማላስታውሰው አንድ የምድር ጦር ሻምበል አየር ኃይል መኮንኖች ክበብ በመሄድ ከአንዴም ሁለቴ ግልጋሎት እንዲያገኝ በኰሚቴዎች ይፈቀድለታል ። ከዚያ በላይ በእንግድነት መገልገል የሚያስችል ሕግ ባለመኖሩ ግልጋሎቱ በኰሚቴዎች እንዲቋረጥ ተደረገ ። በዚህም ሳቢያ ውስጥ ገብቶ ግልጋሎት ማግኘት ያልቻለው መኰንን ሲጋራና ቡና በውጪ ሲጠቀም የአየር ምድቡ አዛዥ ብ/ጄ ንጉሴ ዘርጋው ይመለከታሉ ። ጠጋ ብለውም ለምን ውጭ ሆኖ እንደሚገለገል ሲጠይቁት ክበቡን በኮሚቴነት የሚመሩት መኮንኖች እንዳስቆሙት ይነግራቸዋል ። ቅኑ አዛዥ ሕጉን ትንሽ ገፋ አድርገው መኰንኑ ለተወሰነ ጊዜ በክበቡ እንዲገለገል ኰሚቴዎችን በማግባባታቸው ሻምበሉ ከዚያን ዕለት ጀምሮ እንደ ልቡ እንዲጠቀም ፈቃድ ያገኛል ። ይህ ደግነት ውዱን ጄነራል ዋጋ ሳያስከፍላቸው አልቀረም ። እንደነዚህ አይነት ፀጉረ ልውጥ ሰዎች አንዳች ድብቅ ግዳጅ እየተሰጣቸው በአካባቢው ወዲያና ወዲህ እንደሚሉ የደህንነት ሙያተኞች አጥብቀው ይኰንናሉ ። ጄነራሉ በደግነት የፈቀዱለት መኰንን መልሶ አጥፊያቸው ሆኖ ብቅ እንደሚል ፈፅሞ አልገመቱም ።

ምሽት ላይ እራት ከተበላ በኋላ መደበኛ የሆነውን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ለመከታተል ብንታደምም ከአንድ ቀን በፊት የተላለፈውን ፕሮግራም እንዳለ በድጋሚ ከማሰራጨትና በመሳሪያ የተቀነባበረ ሙዚቃ ከማሰማት ውጪ ትኩስ የዕለቱን ፕሮግራም ሳያስተላልፍ ይቀራል ። በዚህም ምክንያት መሃል አገር አንድ የተፈጠረ ከባድ ችግር ስለመኖሩ ከጥርጣሬ የዘለለ ዕምነት ያዘኩኝ ።

እንደሚታወቀው ሚስጢራዊ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ወደ መሃል አገር የሚደረገው ፣ በተጨማሪም የቴሌቪዥንና ራዲዮ ስርጭት የሚስተጉዋጐለው በመንግስት አካባቢ የፀጥታ ችግር ሲነሳ ብቻ ነው ። በዚህም ምክንያት አብዛኛው የሰራዊቱ አባል በራሱ መንገድ አንዳንድ ጉዳዮችን ሲያጣራ ማምሻውን ከደብረዘይት የተነሱ ተዋጊ ጄቶች በአዲስ አበባ አናት ላይ ሲበሩ እንደነበርና ሔሊኰፐተሮች ደግሞ የመንግስት ለውጥ መደረጉን የሚያበስር በራሪ ወረቀቶች መበተናቸውን ስንሰማ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ገባን ። የሚወራው ዕውነት ከሆነ አስመራ ላለነው የሰራዊቱ አባላት እጅግ አደገኛ ይሆናል ። ምክንያቱም ከአስመራ ወደ መሃል አገር የሚደረገው ጉዞ በአየር አገልግሎት ብቻ ነው ። በየብስ ወደ የትኛውም አቅጣጫ መንቀሳቀስ አይቻልም ። የሻብያ አማፅያን ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በመመሳሰል አደጋ እያደረሱ የነበሩበት ወቅት ላይ ነበርን ። በምድር የሚጓጓዙ የሰራዊቱ ቀለብም ሆነ ትጥቅ በኰንቮይ በመታጀብ ካልሆነ የሚሞከር አልነበረም ።

ረቡዕ ግንቦት ፱ ቀን

በነጋታው ማለዳ ወፎች ወደ የዕለት ተግባራችን እንድንሰማራ ይመስላል ዝማሪያቸው በመስኰቱ በኩል ጐልተው አሰሙን ። ፀሃይ ከወደ ምስራቅ በጥቂቱ የፈነጠቀችው ብርሃን አካባቢውን ሁሉ ወርቅማ ቀለም አልብሶት ድንቅ ሰአሊ የተጠበበት ሸራ መስሏል ። አውሮፕላኖቹን ለበረራ ዝግጁ ለማድረግ የቴክኒክና ድጋፍ ሰጪ ሙያተኞች ማልደን በረራ መስመር መገኘት የዕለት ተዕለት ተግባራችን ቢሆንም ዛሬ ግን ያለወትሮው ጭር ብሏል ። ቀድሜ ያገኘሁት ሲኒየር ቴክኒሺያን " ምንልታደርግ መጣህ " ? በሚል የምጸት ፈገግታ ተቀበለኝ ። እንዳልገባኝ የተረዳው ቴክኒሻን "የመንግስት ግልበጣ መካሄዱን በለሆሳስ ጆሮዬ ስር ቀርቦ በሹክሹክታ አረዳኝ" ። "ርዕሰ ብሔሩም ከአገር ወጥተዋል" ብሎ ደገመልኝ ። የሰማሁትን ማመን አቃተኝ ። ውስጤን ድንጋጤ ቢጤ ሲወረኝ ቢሰማኝም የትናንቱ ኰማንዶዎቹን የማጓጓዝ ትዕይንትና ምሽት ላይ ከቃረምኳቸው ቅንጥብጣቢ ወሬዎች በአንድ ጊዜ በአዕምሮዬ ተመላለሱ ።

አዲስ አበባ ላይ የተሞከረው መፈንቅለ መንግስት መክሸፋና በርካታ ወታደራዊ ጄነራሎች መገደላቸው በሰፊው መነገር ጀምሯል ። ምሽት ላይ ብሔራዊውን የቴሌቪዥን ስርጭት ለመመልከት መዝናኛ ክፍል በጊዜ ገብተን ታጨቅን ። በአዲስ አበባ ስለ ተካሄደው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ልዩ ዝግጅት በመመልከት ላይ እንዳለን ከበስተ ኋላ የሚገኘው በር ድንገት በኃይል ተበርግዶ አንድ ሰው በከፍተኛ ድምፅ የሚግ ሃያ ሶስት ሙያተኞች ለአጣዳፊ ስራ ስለሚፈለጉ ወደ በረራ መስመር በአስቸኳይ እንዲንቀሳቀሱ በማዘዝ አንባረቀ ። ከመቅፀበት ከኤርሜን ክበብ በር ላይ አንዷት ግልጽ ላንድሮቨር መኪና የቻለችውን ያህል ሙያተኛ ይዛ በፍጥነት ወደ በረራ መስመር ተፈተለከች ። የተቀረነውም በሩጫ ወደዚያው አመራን ።

በዚህ ምሽት መብረር ለምን አስፈለገ ? የሚለው ጥያቄ በውስጤ በፍጥነት ይመላለሳል ። ኰሎኔል መንግስቱ ለስራ ጉብኝት ከሄዱበት ጀርመን ወደ አዲስ አበባ እየተመለሱ እንደሆነ መረጃ ደረሶ እርሳቸውን የያዘውን አውሮፕላን ጠልፎ ለማስቀረት ይሆን ? ሊሆን እንደሚችል ውስጤ ጠረጠረ ። መፈንቅለ መንግስቱ አዲስ አበባ ላይ ከከሸፈ ርዕሰ ብሔሩን ጠልፎ ማስቀረቱ ለመደራደሪያነትና አዲስ አበባ በቁጥጥር ስር የዋሉትን መፈንቅለ መንግስት አድራጊ ከፍተኛ መኰንኖችን ለመታደግ አማራጭ የሌለው ፍቱን መድሐኒት እንደሚሆን አመንኩ ። በእርግጥ እንዲህ አይነቱን ሃሳብ በግል አፍኖ ከመያዝ በስተቀር ከማንም ጋር የሚማከሩት ያለመሆኑ እያስጨነቀኝ አውሮፕላኑ ቶሎ ዝግጁ ሆኖ ኢላማውን አስገድዶ እንዲያወርድ እያፀለይኩ ስራዬን በፍጥነት እከውን ጀመር ።

አዲስ አበባ ላይ በቁጥጥር ስር የዋሉት አዛዦቻችን ደህንነት ያሳሰበኝን ያክል ሁለቱ የሚግ ሃያ ሶስት በራሪዎች ቀድመው በረራ መስመር መድረሳቸውን ስመለከት ልቤ በተስፋ ተሞላ ። በራሪዎቹ እንደ ተቆጣ ግስላ ወዲያ ወዲህ ይንጐራደዳሉ ። ቶሎ ወደ አየር ተመንጥቀው ግዳያቸውን ለመጣል የቸኰሉ ይመስላል ። በመንግስት አካባቢ እየተካሄደ ያለውን ጉዳይ ጠልቀው ባያውቁትም እነ ጄነራል ፋንታ በላይ አዲስ አበባ ላይ ደህንነታቸው አስጊ ሁኔታ ላይ በመውደቁ እነሱን ከአደጋ ለመታደግ እንደተጣደፉ አምኜ እጅግ ደስ አለኝ ።

ለመብረር በዝግጅት ላይ ያለችው ሚግ ሃያ ሶስት ተዋጊ ጀት ዙሪያ በርካታ ድጋፍ ሰጪ ተሽከርካሪዎች ይተራመሳሉ ። መብራታቸውን አብርተው ጭለማውን በብርሃን አጥለቅልቀውታል ። ሙያተኞች በየተራ ተገቢውን ፍተሻ ካደረግን በኋላ ሁለቱም ፓይለቶች እንደ ነብር እየዘለሉ ወደ አውሮፕላኗ ገብተው ዝግጁ በመሆን የአውሮፕላኑን ሞተር ማስነሳት ጀመሩ ።

ሚግ-23 ኢንተርሴፕተር ስኳድሮን ለበረራ ዝግጅት ላይ

ከዋናው ሞተር በፊት መነሳት የሚገባት መለስተኛ አስነሺ መዘውር ለመነሳት በማስገምገም ቀጭን ድምጿን እያሰማች እያለች ብዙም ሳትቆይ ጠፋች ። ዋና አብራሪው ሻለቃ "ኢጂቲ አባቭ ዘ ሊሚት" (የሞተሩ ሙቀት ከሚገባው በላይ ሆኗል) በማለት ችግሩን በአቅራቢያው ለቆመው የጥገና ሃላፊ ድምፁን ከፍ አድርጐ አሳወቀ ። ችግሩ ከአስነሺዋ ሞተር የሚወጣው የተቃጠለ አየር ከሚገባው በላይ በመሞቁ የሚከሰት በመሆኑ በአቅራቢያው ከቆሙት ድጋፍ ሰጪ ተሽከርካሪዎች በአንዱ ላይ የነበረውን የታመቀ አየር በመጠቀም የአስነሸውን ሞተር በማቀዝቀዝ በድጋሚ የሞተሯ ድምጽ ተሰማ ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ በተመሳሳይ ሁኔታ የሞተሯ ድምፅ ጠፋና ዋናው አብራሪ ቀድሞ ከአውሮፕላኗ በመውረድ ለጥገና ሃላፊው ሻምበል ችግሩን በቃል በማስረዳት ቀጥሎም በአውሮፕላኗ ጠቅላላ ሁኔታ መመዝገቢያ ማህደር ላይ የገጠመውን ዕክል አስፍሮ ወደሚጠብቃቸው ተሽከርካሪ በመግባት አካባቢውን ለቀው ሄዱ ።

በአንድ ጊዜ ቀዝቃዛ ላብ በጀርባዬ ሲወርድ ተሰማኝ ። ታሪጌቱን (ዒላማውን) አንቆ ይመለሳል ብዬ የተማመንኩበት በረራ በዕክል ምክንያት ባለመሳካቱ አዘንኩ ። ሁኔታዎች እንዳሰብኩት ባለመከናወናቸው ሊደርስ የሚችለው ጥፋት አሳሰበኝ ።

መፈንቅለ መንግስት በዘፈቀደ የሚሰራ ተራ ስራ እንዳልሆነ ይገባኛል ። መሞከር የለበትም ፣ ከተሞከረ ደግሞ ቆራጥና

ፈጣን እርምጃ መውሰድ ይፈልጋል ። ትንሽ ስህተት የህይወት መስዋዕትነት ታስከፍላለች ። በቁጥጥር ስር ለዋሉትም ሆነ አስመራ ለምንገኘው መልካሙን ከመመኘት ውጪ ሌላ አቅም አልነበረኝም ።

ነገሮች ግራ ያጋቡት ሙያተኛ የበረራ መስመሩን ለቆ ሲወጣና በተሽከርካሪዎቹ ብርሃን ፏ ብሎ የደመቀው ስፍራ በአንድ ጊዜ ወደነበረበት አስፈሪ ድቅድቅ ጨለማና ጸጥታው ተመለሰ ። ብዙም ሳይቆይ ሊቀ-መንበሩን የያዘው የመንገደኛ አውሮፕላን የበረራ መስመሩን በመቀየር በሚስጢር አዲስ አበባ መግባቱን ሰማን ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮም አስመራ ያለው ግዙፉ የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊትና የአየር ኃይል ሁለተኛው አየር ምድብ ከቀሪው የአገር መከላከያ ሚኒስትር ጋር ያለው ግንኙነቱ መቋረጡ ግልፅ ሆነ ።

ሐሙስ ግንቦት ፲ ቀን

እንደ ወትሮው ሁሉ ዛሬም ማልደን በመነሳት ወደየስራ ክፍላችን ብንሄድም ሁለትና ሶስት እየሆንን ስለ ሁኔታው ከማውጋት ውጭ ስራ አልነበረም ። የግቢው ፀጥታ እጅግ ያስፈራል ። በየሰዉ ፊት ላይ አንዳች የከበደ ነገር እንዳለ ይነበባል ።

ረፋዱ ላይ አንዲት ትዕዛዝ ከጠቅላይ መምሪያው መጣችና በባዶነት የተንጠለጠለው ልባችን በተስፋ እፎይ አለ ። ከምሳ በኋላ ጠቅላላ የሰራዊቱ አባል በሚግ ሃያ አንድ የጥገና ሃንጋር ውስጥ እንዲገኝ የሚል ጥሪ ነበር ። ጥሪው የመፈንቅለ መንግስቱን ጉዳይ ለመወያየት ሊሆን እንደሚችል አላጣነውም ። ያበጠው መፈንዳቱ ላይቀር በፀጥታ ድባብ ከምንንገላታ ግልፅ ያለ መረጃ ማግኘቱ በራሱ የእፎይታ ያክል ሆኖ ተሰማኝ ።

በተባለው ሰዓት ከስብሰባው ስፍራ ስደርስ ሰፊው የጥገና ሃንጋር በሰው ብዛት ተጣቧል ። እስከ ዛሬ ካየኋቸው ስብሰባዎች ሁሉ በሰው ብዛት የዛሬውን የሚስተካከል መኖሩን እጠረጥራለሁ ። እንደሚታወቀው የአየር ኃይል ማሕበረሰብ ለስብሰባ እጅግም እንደሆነ ባውቅም የዛሬው ከወትሮው ለየት ያለ ጉዳይ የያዘ በመሆኑ ሁሉም በነቂስ ወጥቶ በጊዜ ቦታ ቦታውን ይዟል ።

የአየር ምድቡ አዛዥ ብርጋዴር ጄነራል ንጉሴ ዘርጋው ፣ ኃላፊው መ/አ ፣ እንዲሁም በተለያየ የሃላፊነት ደረጃ የነበሩ ከፍተኛ መኮንኖችን በማስከተል ወደ ስብሰባው ሲገቡ በማናቸውም ፊት ላይ በጐ ስሜት አይነበብም ነበር ። ሁላችንም ከተቀመጥንበት በመነሳት ከተቀበልናቸው በኋላ አዛዡ ጊዜ ሳያባክኑ ጉሮሯቸውን በመጠራረግ ንግግራቸውን ሲጀምሩ አካባቢው በፀጥታ ተዋጠ ።

"እንደምን ውላችኋል?"፣ ጄነራል ንጉሴ ዘርጋው ንግግራቸውን በከፍተኛ እርጋታና በራስ መተማመን መንፈስ ጠንከር አድርገው ጀመሩ። "እንደምታውቁትና እንደሰማችሁት መሃል አገር ጦር ሜዳ ሆኗል ! አዛዦቻችን ተገድለዋል ! ከእንግዲህ በኋላ በመንግስቱ ኃ/ማሪያም መገዛት ሞት ነው" አሉ … ። ጄነራሉ ለአፍታ ቀና በማለት በዝምታ ከፊት ለፊታቸው ተሰብስቦ በአንክሮ የሚያዳምጣቸውን የአየር ኃይል ሰራዊት ትክ ብለው ሲያስተውሉ ቆዩና ወደ ንግግራቸው በመመለስ "በአሁኑ ሰዓት አስመራ የምንገኘው የሰራዊቱ አባላት ከሌላው ሰራዊት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ባይኖረንም ከተለያዩ ኃይሎች ጋር በመነጋገር ሁኔታዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል ሰፊ ዕድል አለ"፣ ብለው በመግለፅ መድረኩን ለፖለቲካ ኃላፊው አስተላለፉ ።

ቀጭን የሰውነት ቁመና ያለው የፖለቲካ ኃላፊ ፈጥኖ መድረኩን በመረከብ ለንግግር ተመቻቸ ። ዞማ ጸጉሩ ወደ ኋላ ሸሽቶ ወደ በራነት እየተቀየረ ሲሆን ግራና ቀኝ ያለው ፀጉሩ ጐፍሮ ይታያል ። በቀይ ዳማ ፊቱ ላይ ችፍፍ ብሎ የሚፈሰውን ላብ አሁንምአሁንም በመሃረብ ይጠርጋል ። እልህና ቁጣ ይነበብበታል ። ምን ሊነግረን እንደሚችል ከውስጤ ጋር እየተሟገትኩ ነበር ። የፖለቲካው አካል

ወገንተኛ ይሆን ? እያልኩ ውስጤ ተረብሿል ። መኰንኑ ግን ቁርጠኛ በሆነ ድምፅ ንግግሩን ሲቀጥል ውስጤ በደስታ ተሞላ። በሃገሪቱና በሰራዊቱ እንዲሁም በሕዝቡ ላይ እየደረሰ ያለውን የአስተዳደር በደል ፣ በሰፈራ ሰበብ አባትና ልጅ እንደተለያዩ ፣ ቤተሰብና ትዳር እየፈረሰ እንደሆነ ... በሰራዊቱ ውስጥም ከውጥረት እና ከጦርነት በስተቀር እረፍት የሚባል ያለመኖሩን በመዘርዘር ካስረዳ በኋላ " እኔ እስከማውቀው ድረስ ከስታንድ ባይ እና ከሬድነስ በስተቀር አንድ ቀን ከቤተሰቤ ጋር እፎይ ብዬ ያሳለፍኩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም "፣ በማለት የሰራዊቱን ስሜት የነካ ንግግር አደረገ ። እፎይ አልኩ ። የፖለቲካው መስመር ከተባበረ ሁኔታዎች ቀላል ሊሆኑ እንደሚችሉ ገመትኩ ። ከፖለቲካው ኃላፊ በኋላ ደልደል ያለ የሰውነት አካል ያለው ወዛም ራሰ በራ ጠይም ሰው መድረኩን ተቆጣጠረ ። ፈገግታ ሁሌም ከፊቱ ላይ አይጠፋም ። የሁለተኛው አየር ምድብ የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ መቶ አለቃ ነበር ። በእጁ ማስታወሻ ብጤ ይዟል ። በእጅጉ ዘና ያለ አቀራረብ ነበረው ። እንደ ወትሮው ዛሬም ፊቱ በፈገግታ የተሞላ ነው ። አማርኛን የራሱ በሆነ ቃና ሲናገረው የተለየ ለዛ አለው ። ግን ምንም ሲያስጨንቀው አይታይም ። ፈገግ እያለ ሰላምታ ካቀረበ በኋላ በእጁ የያዘውን ማስታወሻ ሳይመለከት በግዴለሽነት አጭር ንግግር አድረጐ ጨረሰ. " እኔ ብዙም የምናገረው የለኝም ..... ብቻ አንድ እንሁን .... አንድነት ኃይል ነው .... ሁሌም አንድ እንሁን"፣ በማለት እየተጣደፈ ንግግሩን ቋጨ ። መ/አለቃው ያለንበት አስፈሪ ሁኔታ ብዙም ያስጨነቀው እንዳልሆነ በማየቴ ተገርሜያለሁ ። ፈገግታና ነገሮችን በቀላሉ የማየት ባሕርይው የተለመደ ነበርና ወዲያው ትኩረቴን ከእሱ ላይ አነሳሁ ። በመጨረሻም አዛዡ አዳዲስ ለውጦች ሲኖሩ እንደሚያሳውቁን ቃል በመግባት አሰናበቱን ።

ስብሰባው አልቆ ወደየስራ ክፍላችን ስናመራ ከምእራብ አቅጣጫ ከበረራ መስመር ባሻገር ዥንጉርጉር የአየር ወለድ የደንብ ልብስና ቀይ መለዮ ያጠለቁ ወታደሮች በርቀት ወደ እኛ ሲጠጉ ተመለከትኩኝ ። እየቀረቡን ሲመጡ ክላሽንኮቭ ጠመንጃቸውን ወድረው በረድፍ በወታደራዊ ስልት የሚንቀሳቀሱ በርካታ ኮማንዶዎች መሆናቸውን አረጋገጥኩ ። ከመቅፅበት ዙሪያችንን ተከበብን ። እንደ አዲስ አበባው ሁሉ መፈንቅለ መንግስቱ እዚህም ሊከሽፍ ይሆን ? ወይስ ልምምድ እያደረጉ ነው በማለት ለማረጋጋት የሚሞክሩ ድምፆችን ብሰማም ከኮማንዶዎቹ ሁኔታ አንፃር ልምምድ ላይ ያሉ አልመስልህ አለኝ ። ብዙሃኑ ባለበት ተደናግጦ ግራ በመጋባት ማምለጫ አቅጣጫ እየፈለገ እያለ ከአየር ወለዶቹ አካባቢ ጐላ ባለ ድምጽ ቁም ! እንዳትነቃነቅ ! እያሉ በጩኸትና በአስፈሪ ሁኔታ ወደ እኛ ሲጠጉ በአንድ ጊዜ አካባቢው ተሸበረ ። ያልጠበቅነውና ያልጠረጠርነው ክስተት ነበርና ከፍተኛ ትርምስ ውስጥ ገባን ። ዙሪያችንን ስንመለከት የወታደሮቹ ቁጥር እየጨመረ መጥቶ በአየር ወለድ ሰራዊት ሙሉ ቁጥጥር ስር መውደቃችንን አስተዋልን ። ፈጥነውም ወደ አንድ ስፍራ ሰበሰቡን ።

ያ የተመረጠልን ቦታ አውሮፕላኖቹን ከዕይታ ለመከለል የምንጠቀምበት ከፍ ተደርጎ በብሎኬት የተገነባ ባለ ሶስት ግድግዳ ባንከር ነበር ። ባንከሩ ውስጥ እያጣደፉ እያስገቡን እያለ ያ ወደዚህ ባንከር እንድንገባና እንድንሰበሰብ ያዘዘው ድምፅ ሐሳቡን በመቀየርና በጥርጣሬ በመሞላት "በልበል በአስቸኳይ ከዚህ አስወጣልኝ ...."፣ በማለት ከባንከሩ ውስጥ ወጥተን ሜዳ ላይ እንድንፈስ በማድረግ የያዝነው መሳሪያ ካለ እንድናስረክብ ጠየቁን ። በመሰረቱ አየር ኃይል ውስጥ የበረራ ክሩዎችና ከስራ ባህሪያቸው ጋር በተያያዘ የሚሰጥ መሳሪያ ካልሆነ በስተቀር አብዛኛው ሰራዊት የታጠቀ አይደለምና ቅድሚያ ወስደው ጄነራል ንጉሴ የታጠቁትን አሜሪካ ሰራሽ ኮልት 38 ሽጉጥ አውጥተው አስረከቡ ። በመጨረሻም በአጠቃላይ ከሰራዊቱ የተገኘው መሳሪያ ብዛት በቁጥር ከሃያ አምስት የማይበልጥ ነበርና ትጥቅ እንድንፈታ ያዘዘን መኮንን ከሰራዊቱ የተሰበሰበውን የሽጉጥ ቁጥር ማነስ ተመልክቶ " ምንድነው ? የዩንቨርሲቲ ተማሪ ነው እንዴ የሰበሰብነው ? " በማለት ሁላችንም መሳሪያ እንዳልታጠቅን በመታዘቡ በአግራሞት እኛኑ መልሶ ጠየቀን ። እግረ መንገዱንም ያልታጠቀ ሰራዊት ማገታቸውን የተረዳው ይመስለኛል ።

በአንድ ሻምበል አማካኝነትም ጄነራል ንጉሴ ዘርጋውንና ሌሎች የሚፈልጓቸውን በስም በመጥራት ለይተው ወሰዷቸው ። ይህ ሻምበል ቀደም ሲል በአየር ኃይል መኮንኖች ክበብ ግልጋሎት እንዲሰጠው በጄነራል ንጉሴ የተፈቀደለት ሰው ነበር ። ያኔ ደግ ቢውሉለትም ውለታቸውን በክፉ እየመለሰላቸው መሆኑ አሳዛኝ ክስተት ነበር ። በዚያን ጊዜ መኮንኖች ክበብ እየተመላለሰ የሰማቸውን መረጃዎችና ምስጢር በመሰብሰብ አሉታዊ ተግባሮችን ሲፈፅም እንደነበረ ቆይቶ ተገልጿል ። ሻምበሉ የሚፈልገው ሰው እንዳለ ሁሉ እየተንጠራራ"የታሉ አዲሱ ጄነራል ? ሲል በአስፈሪ ድምፅ እየጮኸ ጠየቀ ። ጠይም ፣ ጸጉራቸው በሽበት የተወረረ ፣ ቀጭንና በቅርቡ የብርጋዴር ጄነራልነት ማዕረግ የተሰጣቸው ትሁት ሰው ወደፊት ቀረቡ ።

እኚህ ከፍተኛ መኮንን በቴክኒክና አስተዳደር ትምህርት ቤት የኤሌክትሮኒክስ ዴፓርትመት ውስጥ አዛዥ ሆነው አውቃቸዋለሁ ። በጣም የተከበሩ በኤሌክትሮኒክስ ሙያም በእጅጉ የተደነቁ ምሁር ናቸው ። ከዚህ በፊት አስመራ አይቻቸው ባላውቅም በዚህ ክፉ ቀን ምን እግር እንደጣላቸው እልህ እየተናነቀኝ እራሴን እጠይቃለሁ ።

ሻምበሉ የቀጮኑን ጄነራል ወደ ፊት መውጣት እያየ ሌላ ጄነራል መጣራቱን ቀጠለ ። ያ ቀዩስ ጄነራል የታለ ? … ሻምበሉ አምባረቀ ። ግራና ቀኝ እያማተረ ቢፈልጋቸውም ቀዩ ያላቸውን ጄነራል ሊያገኛቸው አልቻለም ። በአየር ኃይል ትምህርት ምድብ በአዛዥነት የሚታወቁትን መልከ መልካም መኰንን ነበር ሻምበሉ እየፈለገ የነበረው ። አስመራ እየተካሄደ የነበረውን የአዛዥነት ኰርስ ለማስተማር መጥተው እዚህ ክፉ ቀን ላይ ወድቀዋል ።

ረፋዱ ላይ በሹፌርነት የተመደበላቸው ሻለቃ ባሻ የራሱን ወታደራዊ ፊልድ ጃኬት በማልበስ ከሲኒማ ቤት ይዟቸው ሲወጣ አስተውያለሁ ። ዕድል በቀኛቸው የዋለችላቸው ጄነራል ከዛሬው የአየር ወለዶች ወረራና እገታ ለጊዜው ተርፈዋል ማለት ይቻላል ።

ሻምበሉ እየደጋገመ ስማቸውን ቢጣራም መልስ የሚሰጠው ባለማግኘቱ አንደማያመልጡት በዛቻ እያጉተመተመ በእጁ ያስገባቸውን ከፍተኛ መኰንኖች እየነዳ እዚያው የቆምንበት ትቶን ሄደ ። እነዚህ ሁለት ጄነራሎች ትናንት ረፋዱ ላይ ከደብረዘይት በመጣው ቲዩ - 154 አውሮፕላን ጄነራል ንጉሴ ዘርጋውን ተከትለው የወረዱት ነበሩ ።

ምሽት ላይ አለፍአለፍ እያለ የአውቶማቲክ መሳሪያ ድምጽ በርቀት እየተተኰሰ አስፈሪውን ፀጥታ ያደፈርሰዋል ። ከተኩሱ መድመቅ ጋር የጮፈራና የሆታ ደምጽ አብሮ ደምቆ መሰማቱ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለመገመትም ቸገረኝ ። ኋላ እንደ ተረዳሁት በሻምበል መስፍን (በኋላ በኮሎኔልነት ማእረግ የ102ኛው አየር ወለድ ብርጌድ አዛዥ የሆነ) እና ሻምበል ሲሳይ የተባለ የምድር ጦር መስመራዊ መኮንን አማካኝነት የሁለተኛ አብዮታዊ ሰራዊት አዛዥን ጨምሮ በሌሎች ከፍተኛ መኰንኖች ላይ አሰቃቂ የሆነ እርምጃ በመውሰድ ቀሪዎቹን ከፍተኛ መኮንኖች ደግሞ ወደ አየር ወለድ ቅጥር ግቢ በመውሰድ እንዳሰሯቸው ሰማሁ ። ዕውቁ የአቪየሽን ዶክተርም የዚሁ ሰለባ አካል መሆናቸው እጅግ የሚቆጭ ነበር ።

ጥፋት ተፈፅሟል እንኳ ቢባል መሳሪያ ያስፈቷቸውን የሰራዊቱን አዛዦችና የአገር ባለውለታ የጦር መኰንኖች በቁጥጥር ስር ማቆየት ሲቻል ከአውሬነት ባልተናነሰ በየጐዳና ላይ የተፈፀመውን ወንጀል ታሪክ መቼም ይቅር የማይለው ግልፅ ነበር ።

አርብ ግንቦት ፲፩ ቀን

ማልዶ መነሳት በሁላችንም ውስጥ ያለ ወታደራዊ ልምድ ነበርና ያለአንዳች ቀስቃሽ ሁላችንም በተመሳሳይ ሰዓት መመገቢያ ክፍል ተገናኘን ። ሁሉም የሰማውን መረጃ ይለዋወጣል ። የሞት መርዶ ከመስማት በሻገር ሰላማዊ ሁኔታ አልነበረም ። አስፈላጊ ከሆኑ ሙያተኞች በስተቀር ወደ ስራ ቦታ መሔድ ክልክል ሆኗል ። ጄነራል ንጉሤ በአየር ምድቡ አባላት የተወደዱና እጅግ የተከበሩ አዛዥ ነበሩና ሃዘኑ በሁላችንም ላይ ወደቀ ። ትናንት በሁላችንም ፊት ከነሙሉ ግርማ ሞገሳቸው ቆመው የነበሩት አዛዥ መኰንን ዛሬ በፍትህ አልባነት በጨካኝ አውሬዎች እጅ መውደቃቸው የሁላችንንም ልብ በሃዘን ሰበረው ።

አረፋፍጄ ቀስ እያልኩ ወደ አየር ወለድ ግቢ አቅጣጫ አዘገምኩኝ ። ቀና ብዬ ዙሪያ ገባውን ስማትር ከሽቦ አጥር ባሻገር በቁጥጥር ስር የዋሉ ከፍተኛ መኮንኖች ታዩኝ ። የሁለተኛው አየር ምድብ የዘመቻ መኰንን የበረራ ቱታቸውን እንደለበሱ ሲታዩ የአየር ምድቡ የአስተዳደር መኮንንም እንዲሁ በወታደራዊ ልብስቸው ሆነው አየኋቸው ። የኢትዮጵያን ጠላት ወደ ትቢያ ሲለውጡና ሲያርበደብዱ የነበሩ ምርጥ የሃገሪቱ ጀግኖች በአንድ ጀንበር ለእንደዚህ አይነት ጭካኔ በመዳረጋቸው ተጠቃሚው ጠላት እንጂ ማንም ሊሆን እንደማይችል ለመረዳት ብዙ ዕውቀት አይጠይቅም ።

<u>የስብሰባ ጥሪ</u> ፡

በተከታዩ ቀን በያለንበት ለሁላችንም የስብሰባ ጥሪ ደረሰን ። ደግሞ ምን ቀርቷቸው ይሆን ? ነበር የሁሉም ጥያቄ ። ቀትር ላይ በአየር ምድቡ ዘመቻ ጽሕፈት ቤት ደጃፍ ላይ ተሰበሰብን ። ማን ሊመጣ እንደሆነ ባናውቅም አንድ ከፍተኛ የሃገሪቱ ባለስልጣን ሊያነጋግረን እንደሚችል መገመት ይቻላል ።

ዙሪያውን ከወትሮው ለየት ያለ ከባድ ጥበቃ ተደርጓል ። ከቆይታ በኋል ከሲቪል ተርሚናል አቅጣጫ ከሶስት የማይበልጡ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ ፍጥነት የአውሮፕላን መንደርደሪያውን ተከትለው እኛ ወደምንገኝበት አቅጣጫ ሲከንፉ በማየቴ ምናልባት የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ኮሎኔል መንግስቱ እራሳቸው መጥተው ይሆናል የሚል ግምት አደረብኝ ። በኋላ ቀርበው ሳያቸው ግን ፕሬዝዳንቱ ሳይሆኑ የደርጉ ከፍተኛ ባለስልጣን ሌ/ጄነራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ነበሩ ። ጄነራሉ ከመኪናቸው ከመውረዳቸው በፊት በልዩ ፍጥነትና ስልት የወረዱት የቤተ መንግስቱ ልዩ ጥበቃዎች (በተለምዶ ቅልቦች የሚባሉት) ነበሩ ። የቁመታቸው ግዝፈት ፣ የሰውነታቸው መፈርጠም ፣ ያለዕረፍት የሚቅበዘበዙት አይኖቻቸው ከያዙት መሳሪያ ጋር እንኳን በቅርብ ርቀት ላለ ሰው በርቀት ለሚመለከት እጅግ ያስፈራሉ ። ሁሉንም በጥርጣሬ የሚያዩ ይመስላል ።

ጄኔራሉ በሃገሪቱ ካሉት ወታደራዊ መኮንኖች ውስጥ ብቸኛው ባለከፍተኛ ማዕረግ ናቸው ። የለበሱት የክብር ልብስ በማዕረግ እና በኮርዶን ተንቆጥቁጧል ። ከመኪና ወርደው በቀጥታ ወደ ተዘጋጀላቸው መናገሪያ ሰገነት አመሩ ። በሰላምታና በለሰለሰ አንደበት ጀምረው በአንድ ጊዜ ወደ ንዴት እና ቁጣ ተሸጋገሩ ። ቀጥለውም ዘለፋና ዛቻ አስከተሉ። "ይሔ ዛሬ መንግስት ልትገለብጥበት የነበረው አውሮፕላን ከደሃ ቤተሰቦችህ ቅማል ላይ በተሰበሰበ ገንዘብ የተገዛ ንብረት ነው ..."፣ የሚለው ንግግራቸው ምን ለማለትና ማንን ለመናገር እንደሆን ዛሬ ድረስ ሳይገባኝ አለሁ ።

ሰራዊቱን ይበልጥ የሚያስበረግግ እንጂ የሚያረጋጋ ወይም ኃላፊነት እንዲሰማው የሚያደርግ አንዲትም ቃል ሳያሰሙ የምሬት ንግግራቸውን ፈጽመው በመጡበት አኳኋን እየከነፉ ተመለሱ ። የሳቸው መምጣት መንግስት ሁሉንም በበላይነት እንደተቆጣጠረ ለማረጋገጥ ቢመስልም በንግግራቸው ግን ሰራዊቱን ከማስበርገግና ከማሸበር የተሻለ የማረጋጋት ስራ ሳይሰሩ ስብሰባውን ጨርሰዋል ።

በሌላ በኩልም የሃገሪቱ ርዕሰ-ብሔር ኰ/ል መንግስቱ ኃይለማሪያም በደብረዘይት ፭ኛው አየር ምድብ ተገኝተው ለሰራዊቱ ንግግር እንዳደረጉ ሰማን ። በኋላም በቴሌቪዥን እንደ ታዘብኩት በመጠኑም ቢሆን የሳቸው አቀራረብ የተሻለ ነበር ። ከሰራዊቱም ጥያቄዎችን ተቀብለዋል ። ባለው የፕሬዝዳንትነት ዘመናቸው ምንም የተሻለ ኑሮ እንደሌላቸውም ገልጸዋል "... እኔ መንግስቱ ኃይለማሪያም ከአንድ ተራ ወጥ ቤት የተሻለ ኑሮ አልኖርም ...ፋንታንም ከድሮ ጀምሮ አውቀዋለሁ ..... ከሻለቅነት ማዕረግ እስከ ጄነራል አሳድገነዋል ። ይህንን ሰራዊት ይዞ እንዳይጠፋ ከሰራዊቱ ገለል በማድረግ ወደ ኢንዱስትሪ ሚኒስትርነት ብናዛውረውም ከሰራዊቱ ግን አልተለየም ። የጄነራል ፋንታም ምክትል ቀኝ መንገደኛ እንደሆነ አውቃለሁ ... "። የፕሬዝዳንቱ ንግግር መቼውንም የሚረሳ አልነበረም ። እጅግ በለሰለሰ ቋንቋ አቋማቸውን ግልጽ በማድረግ ያስረዱ ሲሆን ሰራዊቱንም እንደ ጄነራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ሳያንጓጥጡ ተፈጠረ ስላሉት ሁሉ በዝርዝር አስረድተዋል ።

ማምሻውን በቴሊቪዥን መመልከቻ ታድመን ሳለ ዜናው ሁሉ ስለ ተሞከረው መፈንቅለ መንግስት ሲሆን እየተደጋገመ በጥቂት ጄነራሎች የተሞከረው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሳይሳካ መቅረቱንና ከመፈንቅለ መንግስቱ ጋር ንክኪ የነበራቸው በርካታ ግለሰቦች ላይ አብዮታዊ ርምጃ መወሰዱን ይዘረዝራል ። በሌሎች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ግለሰቦች ላይ ምርመራ መጀመሩና ጥፋተኞችም ለፍርድ እንደሚቀርቡ እየተደጋገመ ይገልፃል ።

በማግስቱ ማልደን በየስራ ቦታችን ተገኝተናል ። ግቢው እንደገና ሕይወት ለመዝራት ይመስላል አውሮፕላኖች ማስገምገም ጀምረዋል ። የቅኝት በረራ በማድረግ የአየር ኃይሉን ስነልቦና እንደገና ለመገንባት ጥረት እየተደረገ ነው ።

ረጅሙ እና አሰልቺው ጦርነት የበርካታ ዜጎችን ሕይወት ቀጥፏል ። ጦርነቱን ለማስቆም ይሆናል ተብሎ የተወሰደው መፍትሄ የአገሪቱን ርእሰ ብሄር ከስልጣናቸው በማስወገድ የተሻለ አመራር እንዲኖር ለማድረግ ነበር ። ሆኖም ምርጥ የሃገሪቱ ወታደራዊ ባለስልጣናት የተሳተፉበት ይሄ መፈንቅለ መንግስት እንዴት ሊከሽፍ እንደቻለ ወደ ፊት የሙያው ባለቤቶች ሰፊ ጥናት የሚያቀርቡበት እንደሚሆን እምናለሁ ።

በእርግጥ ሰራዊቱ አስርተ ዓመታት በፈጀው ጦርነት ከሚገባው በላይ ተሰላችቷል ። በአገሪቱ ከፍተኛ መኮንኖች ላይ በተወሰደው ግብታዊ ዕርምጃ አውራ እንደሌለው ንብ ተበትኗል። በጥቂት ጀብደኛ የሰራዊቱ አባላት ግብታዊነት የተወሰደው ዕርምጃ መተኪያ የሌላቸውን ወታደራዊ ጠበብቶችና የአገሪቱ ባለውለታዎችን ደም አፍሷል። ይህም ዛሬ ለምንገኝበት ትልቅ ውድቀት የመጨረሻው መጀመሪያ ለመሆኑ ሁላችንም ምስክር ነን ።

እነዚያ ጠላትን በየጦር ግንባሩ ሲያስጨንቁ የነበሩ ጀግኖች ያን ጊዜ በወገናቸው እጅ ያለፍርድ ታርደው ሬሳቸው በአደባባይ ተጎትቶ አይሞቱ ሞት ሞተዋል ። ሻእቢያና ሕወሃት አንድ ጥይት ሳይተኩሱ ያንን ድል ሲያገኙ ምንኛ ተደስተው ይሆን ? የቆሙበት መሬት የከዳቸው ፣ ያሳደጉት ውሻ የነከሳቸው እነዚያ የጦር መሪዎች ክብር ሲገባቸው ተዋረዱ ፤ በሕይወት የተረፉትም ለይስሙላ ፍርድ አደባባይ ቆሙ ።

የግቢው ሁኔታ ወደ ቀድሞው መልኩ እየተመለሰ ይመስላል ። በበረራ መስመር አካባቢ የስራ ልብሶቻቸውን የለበሱ መካኒኮች ወዲያ ወዲህ ይቻኰላሉ ። አልፎ አልፎም የአውሮፕላኖች ሞተር ሲያጓራ ይሰማል ፣ ነገር ግን አንድም አውሮፕላን ወደ አየር ላይ አልወጣም ።

አንድ ፓይለት ከ፪ኛው አየር ምድብ ዘመቻ ቢሮ እኛ ወደ ምንገኝበት ሚግ ሃያ ሶስት በረራ መስመር አቅጣጫ ሄልሜቱን በግራ እጁ አንጠልጥሎ እየመጣ ነበር ። ቁመቱ ዘለግ ያለው ወጣት አብራሪ በልዩ አኳኋኑና አረማመዱ ማንነቱን ከሩቅ ለመለየት ቀላል ነበር ። ይህ አብራሪ በፊልም እንደ ምንመለከታቸው የአሜሪካን ፓይለቶች በራስ መተማመኑ ጐልቶ ይታያል ። ግዛቸው የተባለው የበረራ መስመር ቴክኒሺያን የእሱን አውሮፕላን ሲያስበርር መመልከት በራሱ አንድ ትዕይንት ነበር ። ግዛቸው ከአውሮፕላኑ በስተግራ በኩል ለአብራሪው እንዲታይ በመሆን ወደፊት ይቆም እና የአውሮፕላኑን መቆጣጠሪያ እንዲያነቃንቅ በእጅ ምልክት ለአብራሪው ያሳያል ። በዚህ ጊዜ ግዛቸው በዘመኑ የነበረውን የብሬክ ዳንስ ያክልበት እና ሁላችንንም ያስፈግገናል ። በመጨረሻም በዳንስ መልክ ወታደራዊ ሰላምታን ያክልበተና አጸፋውን ከፓይለቱ ይቀበላል ። የሚገርመው ነገር ይህን አይነቱ ትዕይንት በዚህ ባለንበት በአሜሪካን አገር ብሉ ኤንጀልስ (ሰማያዊ መላዕክት) በመባል የሚታወቁት የወታደራዊ አውሮፕላኖች በሚያደርጉት የአየር ትርኢት ላይ ወደ መንደርደሪያቸው ከመሄዳቸው በፊት ሁሉም መካኒኮች በተቀናጀ ሁኔታ ሲያደርጉት ተመልክቻለሁ ።

አብራሪው በአውሮፕላኑ ዙሪያ የሚያደርገውን ፍተሻ ጨርሶ ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ ገብቷል ። ለቀናት ተቋርጦ የነበረው በረራ መጀመሩ አስደስቶናል ። በየትኛውም የአየር ኃይል ጣቢያ የአውሮፕላን ድምጽ ሲያጓራ ፣ አውሮፕላን ሲያርፍና ሲነሳ በዙሪያ ገባው ሕይወት ይዘራበታል ። እናም ለቀናት የተቋረጠው በረራ ዛሬ በመጀመሩ ከሃዘኑ እያገገመም ቢሆን ደስታ አይታይበትም ።

ሚግ ሃያ ሶስት በምብ ጣዩ አውሮፕላን በዝግታ ከመቆሚያው ወደ መንደርደሪያው በመሄድ የመጨረሻው ፍተሻ ከተደረገለት በኋላ ድምጹን ከፍ በማድረግና ከኋለኛው ክፍሉ እሳት በመትፋት እያስገመገመ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመንደርደር ወደ ሰማይ ተመነጠቀ ። ከመቅፅበትም ወደቀኝ ዘንበል በማለት ዘወትር የተለመደ አነሳሱን አሳይቶ ከዓይን ተሰወረ ።

በተጠበቀው ሰዓት ተመልሶ ማረፍ የነበረበት አውሮፕላን ባለመመለሱ መጥፎ ነገር አጋጥሞታል በሚል ተረበሽን ። እንዲህ አይነት ነገር ሲፈጠር የሚታሰበን በአብራሪውና በአውሮፕላኑ ላይ አንዳች ክፉ ነገር እንደገጠማቸው በማሰብ እንጨነቃለን ። ሁላችንም ዓይናችን የሚችለውን ያህል ርቀት እያማተርን ከአሁን አሁን ድምፁን እንሰማለን ስንል ሳይሳካልን በመቅረቱ በውስጣችን ፍርሃት ነገሰ ። ምን ውስጥ ገብቶ ይሆን ?

እስከ ዛሬ በርካታ አብራሪዎች የተሰጣቸውን ግዳጅ ለመወጣት እንደወጡ ቀርተዋል ። አብዛኛውን ጊዜ የሚነሱት ሁለትሁለት በመሆን ሲሆን አንደኛው ሲመለስ በአልተመለሰው አውሮፕላን ላይ የተፈጠረውን ለመገመት

አንቸገርም ነበር ። ዛሬ ግን የበረረው አንድ ብቻውን ነውና ምን እንደገጠመው ለማወቅ ተቸገርን ። በኋላ ግን በራሪው ወደ ሱዳን መኰብለሉን ሰማን ። በአየር ኃይል ታሪክ ያ ቀን አንድ ምዕራፍ የተከፈተበት ዕለት ነበር ። በአገሪቱ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ላይ በማናለብኝነትና በጭካኔ የተወሰደው እርምጃ ተከትሎ ሀ ብሎ ተቃውሞ የተጀመረበት ዕለት ሆኖ ተመዝግቧል ። በቀጣዮቹ ቀናትም በርካታ አብራሪዎችና የጥገና ሙያተኞች አውሮፕላኖችን በመያዝም ሆነ በመጥለፍ መኮብለል ጀመሩ ። እንደ ፀሃፊው አስተሳሰብ የአገሪቱ አገዛዝ በጀብደኝነትና በአረመኒያዊነት የአገር ባለውለታ የነበሩትን የጦር አዛዦች መፍጀቱ ስርዓቱ የተንጠለጠለበትን ቅርንጫፍ በገዛ እጁ መቁረጡን የሚያሳይ የተቃውሞ ምልክት ነበር ።

ሰኞ ነሓሴ ፰ ቀን

ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሆነ ዳሽ - ስድስት ባለ ሁለት ሞተር አውሮፕላን ከአዲስ አበባ ወደ ጋምቤላ ሲጓዝ ባልታወቀ ምክንያት ፉኝዶ በተባለ አካባቢ ተከስክሶ መጥፋቱ የኢትዮጵያ ሬዲዮ በቀትር የዜና ስርጭት ለሕዝብ ጆሮ አደረሰ ። ከመንገደኞቹ ውስጥ የአሜሪካ ኮንግረስ አባል የሆኑት ኮንግረስ ማን ሚኪ ሊላንድ ይገኙበታል ። ኮንግረስ ማኑ ወደ ኢትዮጵያ የተጓዙት ለበጎ አድራጎት ስራ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ እውቅና ያገኙ ፖለቲከኛ ነበሩ ።

በተፈጠረው አደጋ ምክንያት የአሜሪካ አየር ኃይል ዩ-2 የስለላ አውሮፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የአየር ክልል ውስጥ እንዲበር ከመንግስት ፈቃድ አገኘ ። በማስከተልም ለፍለጋው ሁለት ሲ አምስት ጋላክሲ በመባል የሚታወቁት ግዙፍ ወታደራዊ ማጓጓዣ አውሮፕላኖች አራት ብላክ ሃውክ ሄሊኮፕተሮችን በመያዝ ለአሰሳ ገቡ ። በእነዚህ የፈልጐ ማዳን አውሮፕላኖች የግንቦት ስምንቱ የመንግስት ግልበጣ ሙከራ በዋና ተዋናይነት የሚጠቀሱትና በሕይወት የተረፉ ብቸኛው ጄነራል ቁምላቸው ደጀኔ ከአገር መውጣታቸው እርግጠኛ ባይሆንም በሰፊው ተወራ ።

የትግራይ ነፃ አውጪዎች እንደሚሉት ተራሮችን አንቀጥቅጠው መሃል አገር አልገቡም ። ነገር ግን ጦሩ በተንዛዛና አሻጥር በበዛበት ጦርነት በመሰላቸቱና በተጨማሪም መሪዎቹን በጭካኔ በማጣቱ እንዲሁም በመጨረሻም የአገሪቱ መሪ በአልታሰበና ባልተገመተ አኳኋን ከአገር በመውጣታቸው ምክንያት ነበር ። ሰራዊቱም ፍጹም ስነ-ስርዐት በሞላበት ሁኔታ እንደ ታጠቀ ወታደር ሳይሆን መሳሪያውን ወርውሮ ወደ ትውልድ አገሩ ከመሔድ ሌላ ተደራጅቶ መዋጋትም ይሁን የዝርፊያ አዝማሚያ ያላሳየው ምን ያህል ሕዝቡን እና አገሩን አክባሪ ሰላም ፈላጊ በመሆኑ ነው ። በአሜሪካ እና በሌሎች የአውሮፓ አገሮች አደራዳሪነት የኢትዮጵያ የልኡካን ቡድን ሰላማዊ ድርድር ለማድረግ ተጉዟል ። እውነታው ግን ኃያላኑ አገራት በኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፋንታ ላይ እየወሰኑ መንገዱን ለሕወሃት አልጋ በአልጋ እያደረጉ ነበር ። ለዚህ እና ለሌሎች ውለታዎች የትግራይ ነፃ አውጪ አሁንም የአሜሪካንን መንግስት በሎሌነት እያገለገለ ይገኛል ።

የከርሞ ሰው ይበለን ።

----------------///---------------

የአባቴ አሻራ

ከመጽሔቱ ዝግጅት ጋር በትብብር የቀረበ

ክፍሉ ሁሴን አሕመድ

በኢትዮጲያ ጦር ኃይል ውስጥ ሁለት ታዋቂ ሁሴን አሕመዶች ነበሩ። አንደኛው ደርግ እስኪወድቅ ድረስ በሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥነት አገልግለው እስከ ሜጀር ጀኔራልነት ማዕረግ የደረሱ የምድር ጦር ባልደረባ የነበሩ የሐረር አካዳሚ ምሩቅ ሲሆኑ፤ ሌላኛው አየር ኃይል አፍርቷቸው በበረራ ሙያ እስከ ሻለቃ ማዕረግ ካገለገሉ በኋላ ወደ አየር መንገድ ተዛውረው ለሰላሳ ዓመታት ያህል በአብራሪነትና በአሰልጣኝነት ያገለገሉት ናቸው። ክፍሉ ሁሴን የኝህኛው የበኩር ልጅ ነው ።

እነዚህ ሁለት ሁሴን አሕመዶች የሚምታቱባቸው ሰዎች ነበሩ ። አሁንም ሊኖሩ ይችላል ። ወደ ዋናው ታሪካችን ከመግባታችን በፊት እንዴት የምድር ጦሩና የአየር ኃይሉ ሁሴኖች አንዳንድ ሰዎችን እንዳምታቱ ክፍሉ ያጫወተንን እንንገራችሁ ።

ሁለቱ መኮንኖች እስከ አባት ስማቸው ሞክሼ ከመሆናቸውም ባሻገር የክፍሉ አባት የአየር ኃይሉ ሻለቃ ሁሴን ገና በማለዳ ከአየር ኃይል ለምድር ጦሩ የአየር ድጋፍ እንዲሰጥ ወደ ተቋቋመው የምድር ጦር አየር ክፍል (Army Aviation) ይዛወራሉ። አርሚ አቪዬሽን ዋና ምድቡ አዲስ አበባ ልደታ እንደመሆኑ ለሻለቃ ሁሴንም ፖፑላሬ ተብሎ በሚታወቀው የመኮንኖች ሰፈር የመኖሪያ ቤት ይሰጣቸዋል። ከዓመታት በኋላ የንጉሰ ነገሥቱ መንግስት ሊወድቅ አንድ ሀሙስ ሲቀረው የምድር ጦሩ ሁሴን አህመድም ፖፑላሬ ይገባሉ፤ የዚያን ጊዜ ሻለቃ ነበሩ የክፍሉ አባት የአየር ኃይሉ ሻምበል ሳሉ። ያም ሆኖ በአብዮቱ ፍንዳታ ማግስት የሻለቅነት ማዕረግ ይሰጣቸውና ከሞክሼነታቸው በተጨማሪ ማዕረጋቸውም ገጠመ። ፖፑላሬ በአብዛኛው የምድር ጦር ሰራዊት መኮንኖች ሰፈር ቢሆንም የክፍሉ አባት ይለብሱት ከነበረው በማራኪነቱ ለየት ያለው የአየር ኃይል የደንብ ልብስ አኳያና በሰፈሩ ቀድሞ በመግባት ከመታወቅ አንጻር እንግዳ መጥቶ የሰፈሩን ህጻናት "የሻለቃ ሁሴን ቤት" ሲል የሚጠቆመው አርሚ አቪዬሽንን መሰረት ያስያዙት የአየር ኃይሉ መኮንን ቤት ነበር ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የክፍሉ አባት የአየር ኃይሉ ሻለቃ ሁሴን በሻለቅነት ማዕረግ ብዙም ሳያገለግሉ አርሚ አቪዬሽንን ለቀው ሰራዊቱን ተሰናብተው አብዩቱ በፈነዳ በሁለት/ሶስተኛው ወር 1966 ዓ.ም አየር መንገድ በመግባት የሲቪል ሕይወታቸውን በቻርተር አውሮፕላን አብራሪነትና በበረራ አስተማሪነት ይጀምራሉ። ወቅቱ ገና አብዩቱ ያልሰከነበትና ያንንም ይህንንም ንብረት ከባለሀብቶች በሰፊው ህዝብ ስም የሚወረስበት ወቅት ነበርና ደርጉ "የማምረቻና ማከፋፈያ መሳሪያ ፋብሪካዎችን" በቁጥጥር ስር ሲያውል የአንድ ጣሊያን የነበረ አስመራ የሚገኝ ባራቶሎ ኮቶኒፊኮ በመባል የሚታወቅ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን ይወርሳል ።

ጣልያኑ ሰፊ የጥጥ እርሻ ተሰኔ የነበረው ከመሆኑም ባሻገር ይኸው እርሻ ተባይ እንዳያጠቃው መድሀኒት የሚረጭበት ሁለት ባለአንድ ሞተር አውሮፕላኖችና አንድ ባለሁለት ሞተር የመጓጓዣ ሴስና አውሮኘላኖችም ነበሩት። አውሮፕላኖቹን ይበሩለት የነበረው ጣሊያኖች ሲሆኑ ደርጉ ፋብሪካውን ሲወርሰው ካልጠበቀው ከዚህ ችግር ጋር ተፋጠጠ። በጊዜው የኢንዱስትሪ ሚኒስትር የነበሩት አቶ/ጓድ ተስፋዬ ዲንቃ ይዘይዱና ለአየር መንገዱ ፓይለት በውሰት (secondment) እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። በዚሁ መሰረት ሻለቃ ሁሴን እነዚህን አውሮፕላኖች እንዲበሩ፣ እንዲያስተዳደሩ ከጥሩ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ጋር ለሁለት ዓመት ከአየርመንገድ ወደ ባሮቶሎ አስመራ ተዛወሩ። ዘመኑ ከ1968 መጨረሻ በተገንጣዩቹ የሚደረገው ጦርነት ተባብሶ ተሰኔ የሚገኘው የጥጥ እርሻ በአውሮፕላን መድሀኒት መረጨቱን እስካቋረጠበት 1969 ዓም ድረስ ይዘልቃል።

አጋጣሚ ሻለቃ ሁሴን በሲቪል ሕይወት አስመራ በተዛወሩበት ጊዜ የምድር ጦሩም ሁሴን አህመድ በሻለቅነት ወይም በሌተና ኮሎኔል ማዕረግ እዚያው ኤርትራ ከተገንጣዮቹ ጋር በመፋለም ላይ ነበሩ። ደርጉ በዚያው ሰሞን ለሰራዊቱ አባላት የማዕረግ እድገት ሲሰጥ የሁሴን አህመድን መሾም የሰማ የክፍሉ አባት የሜዳ ቴኒስ ይጫወቱ በነበረበት የግሪክ ክበብ አባል የነበረ አንድ ሲቪል የሻለቃ ሁሴንን አስመራ መቀየር እንጂ ዝርዝሩን የማያውቅ፣ ስለጦር ሰራዊቱ ሁሴንም ሰምቶ የማያውቅ ሹመቱን እንደሰማ የደስደስ ሊል በሌ የሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ሄደ። የክፍሉ እናት የሻለቃ ሁሴን ባለቤት ወ/ሮ

ለምለም ሁኔታውን አስረድተው በነገሩ በመገረምና በመሳቅ ከሰውዬው ጋር ተለያዩ ።

ማሕበራዊ ድህረ-ገጾችን የሚከታተል ሰው ክፍሉ ሁሴን ማን እንደሆን በቀላሉ የሚረዳ ይመስለኛል። ሃሳቡን ፊት ለፊት ከመግለጽ ወደ ኋላ የማይል ጎላ ብሎ የሚታይ የድህረ-ገጾቹ ቋሚ ታዳሚ ነው። ክፍሉን ለዚህ መጽሔት ስንጋብዘው አላቅማማም። የአየር ኃይል ጉዳይ እንደ እግር እሳት ከሚያንገበግባቸው ሰዎች መሃከል አንዱ ነው። ስለድርጅቱ ያለው ዕውቀት እኛ የትነበርን የሚያሰኝ ነው። አየር ኃይል ውስጥ እነማን እንደነበሩ፣ ምን እንደተፈጸመና ማን እንደፈጸመው ማወቅ የፈለገ ሰው ክፍሉን መጠየቅ አለበት። ኢንስይክሎፒዲያው ያለው እሱ ጋ ነው። ሰለአባቱና ቤተሰቡ እንዲነግረን ነበር ቀድመን የጠየቅነው። እናም ልጅ ስለአባቱ የተናገረውን በአጭሩ ይዘን ቀርበናል ።

ሻለቃ ሁሴን አህመድ በሥራ ላይ

ሻለቃ ሁሴን አሕመድ በአባታቸው ኤርትራ ውስጥ የሚገኘው የአሳውርታ ጎሳ ደም አለባቸው። ተወልደው ያደጉት ግን ጅማ ውስጥ ሲሆን እናታቸው እዚያው የጅማ ሰው ነበሩ። ባለቤታቸው ወይዘሮ ለምለም ረዳ ደግሞ የተወለዱት ከጎጃሜ ወገን ቢሆንም ያደጉት መቀሌ ነው። ለዚህ ይመስለኛል እንደ ብዙዎቻችን ሁሉ ለክፍሉም ኢትዮጲያን በክልል አጥብቦ የማየት አመለካከቶች እንቆቆልሽ የሚሆኑት።

ሻለቃ ሁሴንና ወይዘሮ ለምለም በወጣትነት ዕድሜያቸው አምስት ወንዶች ልጆች ወልደው ለቁምነገር አብቅተዋል። ሴት ልጅ ፈልገው አልተሳካም። ወይዘሮ ለምለም አራተኛ ልጃቸውን ጸንሰው ሳለ ሻለቃ ሁሴን ለትምህርት አሜሪካ ይሄዳሉ። እናት አሁንስ ሴት ናት በዚህ ተወዳደረኝ ይላሉ። አባት ደግሞ አይመስለኝም ከሆነች ደግሞ እሰየው ነው ፣ ማለፊያ የዕራት ልብስ ይዤልሽ እመጣለሁ! ሴት ካልሆነችስ እጅሽ ከምን? ይላሉ ሻለቃ ። ጋቢ አሰርቼ እጠብቅሃለው ይላሉ ወይዘሮ ለምለም። የእግዜር ፈቃድ ሆነና ወንድ ልጅ ተወለደ። ያን ጊዜ አባት ወሬውን እንደሰሙ ይሁና ! ነገር ግን እኔ በውርርዱ አሸናፊ ሆኛለሁና ልጄን "አሸናፊ" ብዬዋለሁ ይላሉ። እናም አራተኛው ልጅ አሸናፊ ተባለ ። ዛሬ ኢትዮጲያ አየር መንገድ ውስጥ ድሪም ላይነር ተብሎ የሚታወቀውን ቦይንግ 787 እና 777 ን ያበራል። ልጅ አባትን ተክቷል ።

ሻለቃ ሁሴን አየር ኃይል የገቡት እ.ኤ.አ በ1959 መጨረሻ አካባቢ ነው ። ሚኒስትሪ የሚባለውን የ8ኛ ክፍል ፈተና እንዳለፉ ከጅማ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ተፈሪ መኮንን ሲማሩ ነው አየር ኃይል የመለመላቸው። ኮርሳቸው ፒ-11 ይባል ነበር ። ስልሳ ሆነው ስልጠናውን ከጀመሩት ውስጥ አስራ ስምንቱ የበረራ ክንፋቸውን እ.ኤ.አ በ1961 ተቀበሉ። ሻለቃ ሁሴን ከዚያ ውስጥ አንዱ ናቸው። ክፍሉ ከሚያስታውሳቸው መካከል ኮሎኔል ግዛው ድረባ፣ ኰ/ል ብርሃነመስቀል ኃይሌ፣ ኰ/ል ማሞ ጉደታ ፣ ሌ/ኮሎኔል አረጋ ወንደማገኘሁና ሻውል ኃይሌ እንዲሁም ሻለቃ ጌታቸው ከበደና ሀብተወልድ ገብረወልድ ብሎም በዲሲፕሊን ጉድለት ከአየር ኃይል ከተባረረ በኋላ አውሮፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ የጠለፈው መለሰ ቢራራና በግዳጅ ላይ እንዳለ በኤርትራ ተወላጅነቱ የተነሳ ካንቤራ የሚባለውን በምብ ጣይ አውሮፕላን ይዞ ወደ ሶማሊያ የከዳው ሻለቃ አፈወርቂ መኮንን የዚሁ ኮርስ አባል ነበሩ ።

ሻለቃ ሁሴን ከምረቃ በኋላ የተመደቡት ቲ-28 ላይ አስመራ ነው ። ቀጥሎም አርሚ አቪዬሽን ሲቋቋም ከመስራቾቹ አንዱ ሆነው መጀመሪያ ደብረዘይት ከዚያም አዲስ አበባ ለረዥም ጊዜ በመስራት በወቅቱ የነበሩትን ባለ አንድና ሁለት ሞተር ኦተር፣ ሴስና 185 ወዘተ የተለያዩ አውሮፕላኖች ያበረሩ ከመሆኑም በላይ ዩኤች 1ኤች ወይም ሂዌ በሚለው ቁልምጫ የምትታወቀውን ዝነኛ ሄሊኮፕተር እ.ኤ.አ በ1968 እዚሁ አሜሪካ አላባማ በመምጣት ቀደምታቸው ከነበሩትና በማዕረግም የበላያቸው ከነበሩት አየር ኃይል ካፈራቸው አንጋፋ ፓይለት ሌተና ኮሎኔል ቶላ ቢነጋ ጋር ሰልጥነው በሄሊኮፕተር አብራሪነትም የኢትዮጲያን የአየር ክልል በማካለል መንደሯን ጓዳ ጎድጎዳዋን ሁሉ አይተዋል። ለመሰረታዊ ስልጠና ጭምር ፓይለቶችን አሜሪካ እየላከ የሚያሰለጥነውን አርሚ አቪዬሽን አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ተብሎ በሚታወቀው አጭር የልደታ ማኮብኮቢያ ሜዳ ዋና የማረፊያ እግሯ (main landing gear) በአፍንጫዋ በኩል በሆነው ሴስና 185 ማሰልጠን አይቻልም የሚሉ ወገኖች ቢኖሩም ይቻላል ብለው በወታደራዊ ተራድኦ ስምምነት መሰረት ድጋፍ ለመስጠት በብዛት ኢትዮጲያ የነበሩት አሜሪካኖችም ደግፈዋቸው የመሰረታዊ የበረራ

ማሰልጠኛ ት/ቤት አርሚ አቪዬሽን እንዲኖረው ፋና ወጊ በመሆን አኩሪ ውጤት እንዳስገኙ ዛሬ በሕይወት የሚገኙ ጥቂት ጓደኞቻቸውና ተማሪዎቻቸው ይመሰክራሉ ።

ክፍሉ አባቱን “ሁሴን” እያለ ነው የሚጠራቸው። ወታደራዊ ዲስፕሊኑ እንዳለም ቢሆን ሊብራል ነበሩ ይላቸዋል። ለዚህ ምክንያት የሆነው ስልጣኔ ያመጣውን አዳዲስና ፕሮግሬሲቭ የሆኑ ነገሮችን ለማየትና ለማወቅ እድሉ ሰለነበራቸው ነው ይላል። ብዙ ጊዜ ውጭ ሃገር ተመላልሰዋል ። ሌላው የደረሰበትን አይተዋል። የውጭ መጽሐፎችና መጽሔቶች ይዘው ይመጡና ያነባሉ ። በማንበብ ያምናሉ። ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆኑ የመንደሩ ልጆችም እንዲያነቡ ያበረታታሉ ። እጃቸው ክፍሉ ላይ ያረፈው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ቲቸር አርጋውን ግን አጣጥለውበታል ።ይህንን አሁንም ያስታወሳል። እንዲህ ነበር ።

ዘመኑ የአፍሮ አሜሪካ ባሕል ወደ ኢትዮጲያ የገባበት ጊዜ ነው። አፍሮ፣ ቤል ቤተም ሱሪና ሌላም ፋሽኖች የወጣቱን ቀልብ ሰርቀዋል። የነክፍሉ አስተማሪ ቲቸር አርጋው ደግሞ በዚህ ተዋጥቶለታል። አፍሮ ያበጥራል፣ ቤል ቤተም ሱሪ ይለብሳል፤ እንዲያው በአጠቃላይ የጊዜው ዘናጭ ነው። በዚህ ረገድ የክፍሉና የታናናሾቹ አይኮን ሆኗል። ታዲያ አንድ ቀን አባት እንደተለመደው ልጆቻቸውን ጸጉር ለማስተካከል በመኪና ይዘው ሲሄዱ ቲቸር አርጋውን መንገድ ላይ ያዩታል። ልጆች አስተማሪያችን ነው ብለው በኩራት ለአባታቸው ያሳያሉ። አባት ደግሞ ይሄ ነው ልጆቼን የሚያስተምረው ብለው በምሬት ስሜታቸውን ይገልጻሉ። ክፍሉ ዛሬ ይሄ ያስቀው እንጂ ያን ጊዜ ስሜቱ ተነክቷል ። ይሁን እንጂ ዛሬ አባቱን ለመግለጽ እንደ ጥሩ ምሳሌ ያነሳዋል ። አባቱ ወርቃማውን አማካይ መንገድ የሚመርጡ ሰው ነበሩ። ፈረንጆቹ ዘ ጎልደን ሚን የሚሉትን አይነት ።

ሻለቃ ሁሴን አርሚ አቪዬሽን ከተዛወሩ በኋላ ቦሌ ቤት ሰርተው እስኪሄዱ ድረስ ለረዥም ጊዜ የቤተሰቡ መኖሪያ ፖፑላሬ ሆኖ ነበር ። አባቱም ቴኒስ ለመጫወት አዘውትረው ይሄዱ የነበሩት የቀድሞው ጦር ኃይሎች ክበብ ስለነበር ከብዙ የሰራዊቱ አባላት ጋር የመተዋወቅ አጋጣሚውን አግኝተዋል ። ክፍሉ የአባቱ ልጅ ነው ። እንደአባቱ መሆን የሚፈልግ። አየር ኃይል ፓይለት መሆን ይፈልግ ነበር። በልጅነቱ የደረሰበት በሽታ በቀኝ እግሩ ላይ ባስከተለው መጠነኛ ጉዳት የተነሳ ሕልሙን ማሳካት አልቻለም ። የህልሙን አለመሳካት ከካሳ ተሰማ ዜማ "ምን ያለ አሞራ ነው ከዛፍ ይሟገታል ከሚወዱት ሰው ጋራ ማን ሲኖር አይቶታል !" በሚለው እንደሚያጽናናም አጫውቶናል ። ይሁን እንጂ ልቡ አሁንም አየር ኃይል ነው ። የአየር ኃይል ልጅ በመሆኑ ይኮራል ።

የአየር ኃይል ታሪክ የኔም ታሪክ ነው ይላል። በአደረጃጀቱና በዘመናዊነቱ ብቻ ሳይሆን ለሃገሪቱ ከከፈለው መስዋትነት አንጻር ግዙፍ የነበረው የአየር ኃይል ታሪክ በበቂ አልተጻፈም እያለ ይቆጫል ። ሌሎች ከፈጸሙት ጋር እያነጻጸረም ያዝናል ። አባላቱንም ይወቅሳል። ቤቱ የብዙ ጀግኖች ቤት ነበር እንዴትስ የጀግና አባቶቻችሁን ታሪክ አትጽፉም እያለ። እሱ በበኩሉ ግን የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ አንድ ቀን ይህንን አደራ እንደሚወጣ ይናገራል ።

ሻለቃ ሁሴን ከቤተሰባቸው ጋር

ክፍሉ ውልደቱም እድገቱም አዲስ አበባ ነው ። አጋዚያን ፣ ፍሬሕይወት ፣ መሰረተ ክርስቶስ ፣ ምስራቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ከዚያም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሕግ ፋክልቲ ገብቶ በዲፕሎማ ተመርቋል ። በዚሁ ሙያም አቦካቶ ሆኖ ብዙ ድርጅቶችን ወክሎ ፍርድ ቤት ቆሟል ። ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፣ ኢትዮ ሊቢያ ካምፓኒ ፣ የኢትዮጲያ መድን ድርጅት ፣ ዓሣ ኮርፖሬሽንና ሌሎችም በታ ጠበቃ ሆኖ ሰርቷል ። በመጨረሻ ከሃገር ያስወጣው በሃገር ጉዳይ የሚያሳየው የነቃ ተሳትፎ ፣ በተለይም በቅንጅት ጊዜ ጎልቶ መታየቱ በአገዛዙ የለየለት የፈጠራ ክስ ለአንድ ዓመት ከመታሰሩ ጋር የተያያዘ ነው ። የቅንጅት አባል ግን አልነበረም አክቲቪስት ከሚባል በቀር ። የሕግ የበላይነትንና የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን ባጋጠመው መድረክ ሁሉ አንስቶ አገዛዙን ሞግቷል ። በዚህ ምክንያት በደርግ ጊዜ የታወጀውን የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሁሉ ወያኔ ጠቅሶ "በስልጣን አላግባብ መጠቀም" የሚል የክስ ናዳ ከምሮብት በሕይወት ዘመኑ ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሳለ ለእሱ ቢሮ ብቻ ከተመደበች ሀሊማ ከምትባል ምስኪን ተላላኪ ውጪ አዝዞ የማይውቀው ሰው አላግባብ ሊጠቀምበት የሚችለው ስልጣን እንደነበረው ተደርጎ በወያኔ መታገቱን ክፍሉ ታዝቧል። መጨረሻ ላይግን ክሱን ሲያዳትቱ ቆይተው በዚያ ፍሬ ከርሲኪ ክስ መፍረድ የማይመች የሆነባቸው ሁለቱ ዳኞች

ክሱን ውድቅ አድርገው በወያኔ የተሰየመውን የመህል ዳኛ ቅር ላለማሰኘት አንዷን ክስ አንጠልጥለው ከአንድ ዓመት እስር በኋላ በ"ፍጥነት" በዋስ እንድወጣ "መልካም ፈቃዳቸው" ሆነ! ይላል የእስር ዘመኑን ክፍሉ ሲያጠቃልል።

ከምርጫው ጋር በተያያዘ በወቅቱ ለቢቢሲ ኔትወርክ አፍሪካ ልኮት የተነበበለት ደብዳቤና ሌሎችም ተጨማምረው ገዢዎቻችን ክፍሉ በገዛ ፈቃዱ ለቶት የነበረው የጊዜው ሰዎች የሚዘውሩት የኢትዮጲያ መድን ድርጅት የነበሩ ፈሪ ሹማምንት ራሳቸውን ለማዳን ያቀበሏቸው የሀሰት በትር ለመታገቱ ይበልጥ ሁኔታዎችን እንዳመቻቸ ክፍሉ ይገልጽና ለቂም በቀል ሳይሆን "መዝገብ ለማስተካከል ዕድሜ ከሰጠ ይህ ሂሳብ ይወራረዳል" ሲል ይቋጫል ። ይህን የሕይወቱን ክፍል በተመለከተ።

ከተፈታ በኋላ ክፍሉ የስደት ቤቱን ያደረገው ዩጋንዳ ነው ። 2007 ላይ ጨርቁን ጠቅሎ ቤተሰቡን ይዞ ካምፓላ ዩጋንዳ ዋና ከተማ ሄዶ ሰባት ዓመት ኖረ ። ለዩጋንዳ ውለታ አለብኝ ይላል ። ልጆቹ ዩጋንዳን ሲወዱ አይጣል ነው ባይ ነው። ዩጋንዳን ለቆ ዛሬ ይኸው ዳላስ ቴክሳስ ውስጥ ሲኖር ሶስት ዓመት አልፎታል ። ክፍሉ ትዳር የመሰረተው እ.ኤ.አ በ1994 ሲሆን ሁለት ሴት ልጆችም አፍርቷል ። በዚህ ረገድ የአባትና የእናቱን ሳይሟላ የቀረ ፍላጎት አሟልቷል ። እናቱ ወይዘሮ ለምለም ዛሬም በሕይወት አሉ ። ሻለቃ ሁሴን ግን እ.ኤ.አ 2000 ላይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ከክፍሉ ጋር የተሰነባበትነው የአምላክ ፈቃድ ከሆነ ጁላይ ላይ ሲያትል ለመገናኘት ነው ። በእግሩ ለመቆም የራሱን ቢሮ ለመክፈት እየጣረ ነው ። ያሰበው ቀደም ብሎ ከተሳካ አልቀርም ባይ ነው ።

እስከዚያው ግን አንድ የቀረ ጥያቄ ነበረን በውጭ ላለው የአየር ኃይል ዲያስፖራ የሚለው ነገር ካለ ብለን ለጠየቅነው ጥያቄ እንዲህ ብሏል። የአባትና የእናቶቻችንን ታሪክ መዘከርና ለልጆቻችንም ማስተላለፍ የሁላችንም ሃላፊነት ነውና ጉዳዩን ለጥቂቶች አትተውት ይላል። ተስፋም እንዳንቆርጥ ያበረታታል። በታሪክ ውስጥ መውደቅና መነሳት ያለ ነው። ዘላለማዊነት የለም። የወደቀ ይነሳል። የተነሳም ይወድቃል። ይህንን ከታሪክ ተምረናል። ዋናው ነገር ያለማቋረጥ በጎውን ማሰብ፣ ማቀድና መስራት ነው። እጅን አጣጥፎ መቀመጥ እራስን መበደል ነው። ከዚህ የከፋ በደል በራሳችን ላይ አናደርስም። የክፍሉ ምክር እኛም "ተነሳ ተራመድ"ን እንድናስታውስ አስገድዶናል ። "ተነሳ ተራመድ" መዝሙር ብቻ አይደለም መርህም ጭምር እንጂ ። ክፍሉ ካለው ጋር አይሄድም ትላላችሁ ?

ያሰንብተን ።

ሻለቃ ሁሴን እየበረሩባት የነበረቾው አውሮፕላን እንጦጦ ላይ አደጋ እንደደረሰባት

ሴሲና የመጀመሪያ ደረጃ በረራ ማስተማሪያ

------------///-----------

የጄኔራሉ ልጆች

ጁላይ የበጋ ወቅት ሲመጣ በስራ የደከመ አካልንም ሆነ አእምሮን ማሳረፊያ ፍለጋ ሲታሰብ የአየር ኃይል አባላትና ቤተሰቡ የሚገናኙበትን ዕለት በናፍቆት የማይጠብቅ የለም ። እንደ ልማድም እንደ ባሕልም ሆኖ ዛሬዛሬ የሰሜን አሜሪካውን የስፖርት ፌስቲቫል እየተከተሉ በቀጠሮ መገናኘት ቋሚ ሆኗል ።

ለዚሁ የሕብረት ግንኙነት አድማቂ የምትሆነን ዓመታዊ መፅሔት ለማዘጋጀት ከአየር ኃይል ቤተሰብ ውስጥ ማንን እንግዳ እንደምናደርግ ስናስብ እጅግ ጨዋታ አዋቂና ከሁሉም ጋር ተጋባቢ የነበሩት ጄነራል ትዝ አሉን ።

ጄነራሉ ለአየር ኃይል ውድ ኔጥ ነበሩ ። የአየር ኃይሉን ከረር ያለ ወታደራዊ ቢሮክራሲ ላላ የሚያደርጉ ፣ ሕይወት የሚዘሩበትና ቤተሰባዊ ቅመም የሚጨምሩበት ናቸው ። የሐረሩ ልጅ ብ/ጄ ዑመር አደም ።

ለረዥም አመታት ግዙፉን የአየር ኃይል ድርጅት መምሪያን ሲያዙ የማያውቃቸው የለም ። ዛሬ በሕይወት አብረውን ባይኖሩም የአብራካቸው ክፋይ የሆኑና አየር ኃይሉን እንደ ቤተሰባቸው ከሚቆጥሩት ልጆቻቸው መካከል ፀደይን ደውለን ስለ አባቷ እንድታጫውተን ስንጠይቃት በደስታ ተቀበለችን ። እንዲያውም እኔ ብቻ ሳልሆን የተቀሩት ወንድሞቼም አብረውኝ ሊያነጋግሯችሁ ፈቃደኞች ይሆናሉ ስትለን በእጅጉ ደስ አለን ። እግዚአብሔር ያክብርልን እንላለን ።

ፀደይ ዑመር ትባላለች ። ኑሮዋን ሰሜን አሜሪካ ካደረገች ዓመታት አስቆጥራለች ። ባለትዳርና የአንድ ወንድ ልጅ እናት ናት ።

በፀደይ በኩል ወንድሞቿንም አገኘናቸውና ወጋችንን ቀጠልን ።

ቤተሰቡ ለአየር ኃይል መስሪያ ቤትና ለአባላቱ ከፍተኛ ፍቅር አላቸው ። ስለ አየር ኃይል ሲናገሩ ከፍቅር ብዛት ቃላቶች እያጠራቸው ይቸገራሉ ።

“አየር ኃይል ለእኛ .... ማንነታችን ፣ ፍቅራችን ፣ ስብዕናችን ፣ ትምህርታችን ፣ ጤናችን በአጠቃላይ እኛነታችን ነው ።” ይላሉ በአንድ ድምፅ ።

“ እኛ ልጆቻቸው በሰራዊቱም ሆነ በቤተሰብ ውስጥ ምንም ቢመጣ አባላቱ የሚያሳዩት የተረጋጋ ፣ ወጥነት ያለው ባህሪና አካሄድ እያየን ስላደግን ሁሌም በራስ መተማመን እንዲኖረን የረዳን ማዕከል ነው ። ”፣ ያላሉ።

ይህንን ከላይ የጠቀስነውን ጸደይና ወንድሞቿ ሰለአባታቸው ሰለ ብ/ጄ ዑመር አደምና ስለ አገለገሉት የአየር ኃይል መ/ቤት የሚያጫውቱን ካለ ብለን በጠየቅናቸው መሰረት ስለ አየር ኃይሉ ጠቅለል አድርገው ከነገሩን ላይ ቀንጭበን የወሰድነው ነው ። ይህንን ሰለ አየር ኃይል የተሰጠ ምስክርነት አጠቃላዩ የአየር ኃይል ቤተሰብ አባላት በሙሉ ድምፅ እንደሚጋሩት ከልምድ አረጋግጠናል ።

ጄኔራሉና ባለቤታቸው ወይዘሮ ትብለፅ ዘዮሐንስ በወለዷቸው በሰባት የአብራካቸው ክፋይ ልጆች ተባርከዋል ። አስቴር ፣ ዳንኤል ፣ የምስራች ፣ አስክንድር ፣ ፀደይ ፣ ሚካኤልና ቢኒያም ይባላሉ ።

ከልጆቻቸው መካከል ጸደይ ቤታቸው የፍቅር ቤት እንደሆነ አጫውታናለች ። ጄኔራል ዑመር በስራቸው ላይ ጠንቃቃና ኮስታራ ይሁን እንጂ ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ጋ ሌላ ሰው ነበሩ ። ቀልደኛ ፣ ርሁሩህና ለልጆቻቸውም የጓደኛ ያህል ቅርብ የሆኑ አባት ናቸው ። “እቤት ውስጥ ግን ሌላ ጄኔራል አሉ”፣ አለችን ፀደይ እየሳቀች ። እናትዋን ማለትዋ ነበር ። ወ/ሮ ትብለፅ ዘዮሃንስ ።

አባት ከውጭ ሰርተው ይግቡ እንጂ ቤቱን ቀጥ አድርገው በሃላፊነት የሚያስተዳድሩት እናት ወይዘሮ ትብለፅ ናቸው ።

*በዚሁ ምክንያት ይመስላል ጄነራሉ ቀልድ ሲያምራቸው ባለቤታቸውን “**ጄኔራል**” ! እያሉ የሚጠሩት ። በእርግጥ “እኒ” እያሉም አሞካሽተው የሚጠሩበት ጊዜም ብዙ ነው ። ባለቤታቸው ወ/ሮ ትብለፅ ለጄነራሉ የዕንቁ ያህል ናቸው ይላሉ ልጆቻቸው በአንድ ድምፅ ። ስለ አባታቸውም ሲመሰክሩ ደግሞ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ባለቤታቸውን አክብረውና አፍቅረው ያለፉ ፍቅር አዋቂ ባልና ለልጆቻቸው ደግሞ ደግ አባት እንደነበሩ ሲናገሩ ድምፃቸው ውስጥ ጥልቅ ሃዘንና ትዝታ እየተሰማ ነበር ።*

ስለ እናታቸው ሲመሰክሩ ደግሞ በምላሹ አባታቸውን አንዳንዴ “ሸሜ” ሌላ ጊዜ ደግሞ “አባዬ” እያሉ እንደሚጠሯቸው አጫውተውናል ።

ጀ/ል ዑመር አደም

ጄኔራል ኡመር ከስራ ሲመለሱ ዩኒፎራማቸውን ቀይረው ጋቢ ይደርቡና በርጬማ ላይ ተቀምጠው ከወይዘሮ ትብለፅ ጋር ቡና መጠጣት ከሚወዱትና ከሚያዘወትሩት ልማድ አንዱ ነበር ። ሌላው የሚወዱት ነገር በዕረፍት ጊዜያቸው ቅዳሜና ዕሑድ ልጆቻቸውን ይዘው ዱከምና ሞጆ ፣ በእሳቸው አጠራር “ሞጆ ዲሞጆ” ለሽርሽር ይዞ በመሄድ ማዝናናት ነው ።

የጄኔራሉ ልጆች ደብረዘይት የሚገኘውን የመኮንኖች ክበብ በከፍተኛ ፍቅርና ትዝታ ያስታውሱታል። አባት ልጆቻቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር እሑድእሑድ ይዘው ይሄዱ ነበር ። ከመብል ከመጠጡ በኋላም ቪዲዮ እያዩ መጨዋት አለ ።

ጄኔራል ዑመር ቢቢሲ ማዳመጥና የእንግሊዝ ፕሪሜር ሊግ እግር ኳስ ጨዋታን ማየት ይወዳሉ ። ከሰፈር ትናንሽ ልጆች ጋር ማውራትና ከቅርብ ጓደኞቻቸው ጋር ተገናኝቶ መጫወትም ያዘወትሩ ነበር።

ጄኔራል ኡመር ከአባታቸው ከአቶ ኡመር ወዳጆ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወርቅነሽ ተሰማ ሐረር ውስጥ ልዩ ስሙ ቆጬር ወረዳ ነው የተወለዱት ። አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዚያው ሐረር ውስጥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ሐረር መድሐኔያለም ከአጠናቀቁ በኋላ ነው በፈረንጆቹ 1953 አየር ኃይልን የተቀላቀሉት ። በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ከምክትል መቶ አለቅነት እስከ ብርጋዴዬር ጄኔራል ማዕረግ አገልግለዋል ። በእነዚህ የአገልግሎት ዘመናቸው ውስጥ በአውሮፕላን ቴክኒዮሎጂ ሰልጥነው ተመርቀዋል ። ለተጨማሪ አውሮፕላን ቴክኒዮሎጂ ሙያም አሜሪካ ፣ በኋላም እንግሊዝ ሃገር ተልከው በካንቤራ አውሮፕላን ላይ ሰልጥነዋል ። በኋላም በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የሎጅስቲክስ መምሪያ ሃላፊ በመሆን መንግስት እስኪለወጥ ድረስ ሲሰሩ ነበር ። ከሰላሳ ስምንት ዓመታት አገልግሎት በኋላ መንግስት ሲለወጥ እንደ አብዛኛው የአየር ኃይል ሰራዊት ያለፍርድ ለሁለት ዓመታት በእስር እንዲቆዩ ተደርገዋል ። ከሁለት ዓመታት የእስር ቆይታ በኋላ ሲፈቱ ግን ጡረታቸው ተከብሮላቸው በሰላም ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ ሳለ በአደረባቸው ሕመም ምክንያት የካቲት 1989 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

ጸደይ አባቷንና አየር ኃይልን የምታስታውሰው በናፍቆት ነው ። 27 ሆነው ከአባቷ ጋር የመሰረቱት የ1953 ዓም ቅጥር አባላት ማሕበር የቤተሰቧ ማሕበር ነው ። አሁንም ድረስ አባላቶቹን የምታያው እንደ ቤተሰቧ አባላት ነው ። እንደ ወንድማማችና እሕትማማች የሚተያዩት የማህበሩ አባላት ዛሬም በሕይወት ያሉት በክፉም ሆነ በደግ በቅርበት ይጠያየቃሉ ። ይደጋገፋሉ ።

አባቷ ቀልደኛና ለሚያውቋቸው ሁሉ ቅጽል ስም ማውጣት ይወዳሉና የሚያውቃቸው ሰው ሁሉ ጋሽ ኡመር ኮሚክ ናቸው ይሏቸው እንደነበር ጸደይ ትናገራለች ። ከትንሹም ከትልቁም ጋር መግባባት የሚችሉና ሰው መርዳት የሚወዱ ሰው ነበሩ ። ዕኩለ ለሊት ላይ በራቸው ከተንኳኳ ምጥ ያያዘት ሴት ፣ ወይንም አስቸኳይ ሕክምና የሚያስፈልገው ሰው አለ ማለት ነው ። ሰፈሩ ውስጥ ሌላ ተሽከርካሪ ያላቸው ሰዎች ቢኖሩም ለእርዳታው የሚመረጡት ጄኔራል ኡመር ናቸው ። አምቢ አይሉማ !

ጸደይ እንደነገረችን ከሆነ ጄኔራል ኡመር ታስረው በተፈቱ ጊዜ በራቸው ያለወትሮው ቀን ቀን ለተከታታይ ቀናት ክፍት ሆኖ ሰንብቷል ። ደስታውን ለመግለጽ የሚጎርፈው ሰው የማያቋርጥና ከልክ በላይ ሆኖ ። ጸደይ፣ እሕቷና ወንድሞቿ አባታቸውን እንዲህ ነው የሚያስታውሱት ።

አየር ኃይልም "አስተማሪዎች አዘጋጅቶ ማታማታ እያስተማረ ለማትሪክ እንድንዘጋጅና በማንኛውም ረገድ የትምህርት ድጋፍ በመስጠት ጥሩ ቦታ እንድንደርስ አግዞናል"፣ ይላሉ። ከዚህም በላይ በክረምት ወራት አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ ከሰራዊቱ እኩል አውቶብስ (ትራንስፖርት) በመመደብ በመረጡት የስፖርት አይነት ስልጠና በመስጠት አሳድጎናል ባይ ናቸው። ከሁሉም በላይ አየር ኃይል ሁሉንም የሰራዊቱን አባል እና ሲቪሉን አስተባብሮ ሐረር ሜዳ ሞዴል ት/ቤትን በመስራት ያበረከተ ባለውለታ መሆኑንም ይናገራሉ።

-------------////--------------



የአየር ኃይል ከፍተኛ አመራሮች

የጄኔራሉ ጸሐፊ

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

ወ/ሮ ሐረገወይን ከፍያለው

ዘመኑ ኢትዮጲያ በገዛ ልጆቿ ጦርነት የተከፈተባት ዘመን ነበር ። ከብዙ መስዋትነት በኋላ የምስራቁ ጦርነት በድል ቢጠናቀቅም ሠራዊቱ ዕረፍት ሳያገኝ ፣ ቤተሰቡንም ሳያይ በዚያው ወደ ሰሜን እንዲያቀና ታዟል ። ሁሉም ነገር ወደ ሰሜን ጦር ግምባር ተብሏል ። መደበኛውን ሠራዊት ለማጠናከር የብሔራዊ ውትድርና ስልጠናም በጥድፊያ ተጀምሯል ። ወጣቶች ከየአሉበት እየተለቀሙ ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያዎች ገብተዋል ። ስልጠናውን ከጨረሱ በኋላ አብዛኞቹ ወደ ሰሜን ግንባር የሚላኩት በአየር ኃይል አንቶኖቭ ነበር ። መነሻቸውም ደብረዘይት ሐረረ ሜዳ ።

የአንደኛው አየር ምድብ አዛዥ ይህ ስራ በታቀደው መሰረት መከናወኑን ለማየት ከቢሮአቸው ወጥተው የመጓጓዣ አውሮፕላኖቹ የቆሙበት አካባቢ ተገኝተዋል ። ያለልኩ የለበሰውን ዩኒፎርም በእጇ ሰብስቦ አውሮፕላኑን ለመሳፈር የሚጠባበቅ ትንሽ ወጣት ወደ ጄኔራሉ ሲያመራ ጸሐፊያቸው ደንግጣ ትከተለዋለች ። ያን ጊዜ ነበር የጄኔራሉ ዓይኖች በእንባ መሞላታቸውን ያየችው ።

ወይዘሮ ሐረገወይን ከፍያለው ትባላለች ። ዛሬ በጋብቻ ምክንያት ሌላ አንድ ተጨማሪ ስም ከፊትለፊት አክላ ሐረገወይን ከፍያለው ብራወር ትባላለች ።

ዕንባ ያዘሉ የጄኔራል ሰለሞን በጋሻውን ዓይኖች እንዳስተዋለች ይህንን ገና ለዓቅመ-ዓዳም ያልደረሰ ወጣት ትጠጋና "ምን ብለሃቸው ነው?" ፣ ብላ ትጠይቀዋለች ። እሱም "የአስር ብር ዝርዝር እንዳላቸው ነው የጠየኳቸው ። ካፊቴሪያዎቹ ለሻይና ለዳቦ አስር ብር አይቀበሉም" ፣ ይላታል ። ሰልጥኗል ፣ ወደ ጦር ሜዳ ለመሄድም ዝግጁ ነው የተባለው ወጣት በወይዘሮ ሐረገወይን አገላለጽ ከእናቱ ጉያ መወጣት አልነበረበትም ። የጄኔራል መዕረግም ለይቶ አለማወቁ መሆን አለበት በቀጥታ ለአስር ብር ዝርዝር ጄኔራሉን የቀረባቸው ። ለጄኔራሉም ዕንባ ምክንያት የሆነው ይሄው ነው ። ለካንስ ወጣቱ ወደ በርሃ ለውጊያ ከመሄዱ በፊት ሻይ በዳቦ አምሮት ኖሯል ። ጄኔራሉ ጸሐፊያቸውን ብሩን ዘርዝራ ፣ ሻይና ዳቦውንም ገዝታ እንድትሰጠው ያዟታል ። ያንንም ትፈጽማለች ።

ወይዘሮ ሐረገወይን ይህንን ታሪክ ያጫወተችን ለስድስት ዓመታት በጸሐፊነት ስለአገለገለቻቸው ጄኔራል ምን እንደምታስታውስ በጠየቅናት ጊዜ ነበር ። ሩህሩህ ነበሩ ትላለች ። በረራ ያሰለጣኗቸው የነበሩ ተማሪዎች ደግሞ ሰማይ ላይ ስላላየሻቸው ነው ይሏታል ። ስራቸው ላይ ምን ያህል ጥብቅ እንደነበሩ ነው የሚገልጸው ።

ወይዘሮ ሐረገወይን ከፍያለው ብራወር ተወልደው ያደገችው ሲዳሞ ክፈለ-ሃገር ሃገረማሪያም ነው ። በጋብቻ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣታቸው በፊት ዲላ ይማሩ ነበር ። የቀድሞ ባለቤታቸው ወንድም አየር ኃይል ነበር ። ወደ ደብረዘይት እንዲመጡም ምክንያት ሆኗል ። ደብረዘይት በታ እየተሰጠ ነውና ኑና ቤት ስሩ ይላቸዋል ። ደብረዘይት ጠቅልለው ይመጡና ጎረቤቱ ቤት ሰሩ ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ተናኘ ወርቅ ጨረሰች ። ለተወሰነ ጊዜ ለስራ ናዝሬት ተመላልሳለች ። ከዚያ በኋላ ነው በጸሐፊነት አየር ኃይልን የተቀላቀለችው ።

ሰለ ከሸፈው ኩዴታና ሰለ አለቃዋ መስዋዕት መሆን የሰማችው አሜሪካ ከመጣች በኋላ ነው ። ምን ተሰማሽ ? አልናት ። መልሷን የጀመረችው ለየት ባለ መንገድ ነበር ።

ወሬውን እንደሰማሁ "ታዲያ ከእንግዲህ ወዲያ ሃገሪቱን ማን ሊያስተዳድራት ነው ?" አልኩ ። መጀመሪያ ያዘነችው ለሃገሪቱ ነው ። ሊያስተዳድሯት ፣ ሊታደጓት የሚችሉ ምርጥ ልጆቿን ላጣችው ። በግልበጣው ሙከራ ላይ ተሳታፊ ነበራችሁ ተብለው ከተገደሉት መሃከል በቅርብ የምታውቃቸው ሰዎች ነበሩበት ። በጸሐፊነት ለስድስት ዓመታት ያገለገለቻቸው ጄኔራል ሰለሞን በጋሻው አንዱ ናቸው ። ጄኔራል ፋንታና ጄኔራል አምሐንም

እንዲሁ በሚገባ ታውቃለች ። እነዚህና በቅርብ ባታውቃቸውም እነሱን የመሰሉ ጀግኖች ናቸው የተቀጠፉት ።

ይህ እንደሚመጣ ጠርጥራ ነበር ። አንድ ቀን ልጆቿን ይዛ ደብረ ዘይት ቀበሌ አንድ ይገኝ ወደነበረው ጂስ ቤት ትሄዳለች ። በር ላይ አንዱ አዋክቦ ወደ ውስጥ ይወስዳትና ጄኔራሉ ለብርቱ ጉዳይ በአስቸኳይ እንደሚፈለጓት ይነግራታል ። የልጆቿ ጂስም ይቀርና ወደ ቤቷ ትከንፋለች ። እዚያ ጄኔራሉን ታገኛለች ። ትደነግጣለች ። ድንገት ቢፈለጉ እንኳን ቤቷ ውስጥ ስልክ የለም ። ለማንኛውም በጨዋታቸው መሃከል በጊዜው የኢትዮጲያ ጉዳይ ላይ ያን ጊዜ የተናገሩትን አትረሳም ። ሃገራችን ችግር ላይ መሆኗን አንስተው "…እንዲህ ሰው ቀስ በቀስ ከሚያልቅ አንድ ፊቱኑ የሆነው ሆኖ ቢለይለት ይሻላል…"፣ የሚል ቃል ከአፋቸው ይወጣል ።

ወ/ሮ ሃረገ ወይን ከልጅ ልጆቻቸው ጋር

በሌላ አጋጣሚም እንዲሁ ለዓመት በዓል እቤታቸው በእንግድነት ስትሄድ የማታውቃቸው ሌሎች ከፍተኛ መኮንኖች መንግስትን ሲተቹ አድምጣለች ። ይሄ ሁሉ ለእሷ ምልክቶች ነበሩ ። በመንግስት ላይ የአመጹ ልቦች ለመኖራቸው አስተውላለች ። ከእሳቱ በፊት ጭስ አይታለች።

ወይዘሮ ሐረገወይን ወደ አሜሪካ የመጣችው በ1988 ዲሰምበር አካባቢ ነው ። የመፈንቅለ-መንግሰቱ ሙከራ ከመደረጉ አምስት ወራት በፊት ። ዛሬ "ኢትዮጲያን ኤንድ አዘር አፍሪካን ኢሚግራንት ኮሚዩኒቲ ሰርቪስስ" ተብሎ የሚጠራ ግበረ-ሰናይ ድርጅት ሜሪላንድ ውስጥ ሲልቨር ስፕሪንግ ከፍታ የራሷን ቢሮ ታስተዳድራለች ። አራት ወንድ ልጆች ለቁምነገር አድርሳለች ። ሶስቱን ወልዳ ፣ አንዱን በጉዲፈቻ አሳድጋ ። እነሱም በተራቸው የአስራአንድ የልጅ ልጆች አያት አድርገዋታል ።

አየር ኃይልን ምንጊዜም አትዘነጋም ። ዘመናዊ ማሕበረሰብ ተገንብቶ የነበረበት ቤት ነበር ትላለች ። ሲቪሉ ከወታደሩ ፣ ሴቱ ከወንዱ ዕኩል እንደ አንድ ቤተሰብ የሚታይበትና የሚከበርበት ቤት እንደነበረ ነው የምታውቀው ። አየር ኃይልን ባገለገለችበት ዘመን ውስጥ ፍቅር የተሞላበት ማሕበራዊ ሕይወት አይታለች ። ያንን ሳትጠግብ ነው ለሌላ ሕይወት ውቅያኖስ የተሻገረችው ።

ከአየር ኃይል ስምንት ሺህ ማይልስ ርቃ ብትሄድም ታዲያ አየር ኃይልና ማሕበራዊ ዕንድምታው አሁንም አብሯት አለ ። የዲሲውን የቀድሞ አየር ኃይል ማሕበር ከመሰረቱትም ሰዎች መሃከል አንዷ ናት ። አሁን በስራ ብዛትና በአድራሻ ርቅት የተነሳ እንደልቧ ተሳታፊ ባትሆንም አልፎአልፎ ግንኙነት አላት ።

ይህ አዲሱ የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዓለም አቀፍ ሕብረትም ከከተሞች ባለፈ ዓለም አቀፋዊ መሰረት ይዞ በቦታ ርቀት ተበታትኖ የሚኖረውን የአየር ኃይል ማሕበረሰብ በኔትዎርክ በማገናኘት ረገድ የሚጫወተውን ሚና ታደንቃለች ።

የወይዘሮ ሐረገወይን ከፍያለው ብራወር የሃገር ፍቅር ስሜት የሚገርም ነው ። ከሃገሯ ከተለየች ሰላሳ ሰባት ዓመታት አልፏል ። ሰለሃገሯ ያላት ፍቅር ግን በጊዜ ብዛት አልዛገም ። አንድ ቀን ሁሉም ነገር ወደ በጎ ይለወጣል ። ያን ጊዜ ጨለማው በብርሃን ይተካል የሚል ጽኑ ዕምነት አላት ።

ያ አስር ብር ለመዘርዘር ጄኔራሉን የተጠጋ ወታደር ዛሬ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል ። ምናልባትም ገና ሻይ በዳቦ በልቶ ሳይጠግብ ጦር ሜዳ ላይ ተሰውቶ ሊሆን ይቻላል ። ዕንባ የቋጠሩለት ጄኔራል ግን መስዋዕት መሆናቸውን እናውቃለን ። ይህ ሁሉ የሆነው ኢትዮጲያ ለምትባል ሃገር ነው ። አልነበረችም የሚሏትን ይቅር ብላ ፣ መኖር የለባትም የሚሉትንም ታግሳ የሁላችንም ቤት ለመሆን ምንጊዜም እጇን ለዘረጋቸው ኢትዮጲያ ።

-----------------------////-----------------------

የሔሊኮፕተር ምርኩና

የኛ ሰዎች በአስመራ

ክንዴ ዳምጤ (የበረራ አስተማሪ)

የስራ መውጫ ሰዓት ደርሷል ። ባልተለመደ ሁኔታ ሁለት ኢትዮጵያውያን የበረራ ሙያተኞች ከኤርትራ አየር ኃይል አዛዥ ቢሮ በጥድፊያ ወጥተው ከጭቃ የተሰራች በምትመስልና እንግዳ በሆነች ላንድ ክሩዘር መኪና ተጭነው በፍጥነት ከጊቢው ተፈትልከው ሲወጡ ተመለከትኩ ። ምን ተፈጠረ ? ወዴት ነው ይዘዋቸው የሚሄዱት ? ለምንስ ሁለቱን ብቻ ? በማለት እራሴኑ በጥያቄ አጣድፍኩት ። በዚህ ዓይነት ጥድፊያ እነዚህ ሁለት ሰዎች መወሰዳቸው ከነከነኝ ።

በእርግጥ ከዚህ ቀደም እንዲሁ ሳይታሰብ በአስቸኳይ ትፈለጋላችሁ ተብለን በአካባቢው የነበርነውን ኢትዮጵያውያኖች አየር ኃይሉ አዛዥ ቢሮ የተጠራንበትን ዕለት አስታውሳለሁ ። ያኔ በሻብያና ወያኔ መካከል ግጭት ተፈጥሯል እየተባለ ከዚህም ከዚያም የተለያዩ ተባራሪ መላምቶች የሚናፈሱበት ሰሞን ነበር ። ወደ አስር የምንጠጋ ኢትዮጵያውያን አዛዡ ቢሮ ተገኝተን ... "ዛሬ የሰበሰብኳችሁ ሰሞኑን ከግራም ከቀኝም ለሚናፈሰው ወሬ ባይተዋር እንዳትሆኑና ማወቅ የሚገባችሁንም አንዳንድ ጉዳዮች ለማሳወቅ ነው"። ብሎ የኤርትራው አየር ኃይል አዛዥ ኰማንደር ኃብተፅዮን ኽድጉ ንግግሩን ጀመረ ። "ከወያኔ ጋር ከረር ወደ አለ ግጭት ሳንገባ አንቀርም ። ምን አልባትም የከፋ ጦርነትም ሊከሰት ይችላል ። ይሁን እንጂ የቱንም ያክል በደም የተጨማለቀ ጦርነት ቢፈጠር ከእናንተ ዘንድ የሚደርስ ምንም ነገር አይኖርም ። በሰላም የመኖር መብታችሁ እንደተጠበቀ ይቆያል ። እኔ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ይህ ቃሌ አይታጠፍም ። እኔ ከሌለሁ ግን የሚሆነውን ለመገመት እቸገራለሁ ። በእርግጥ ቤተሰቦቻችሁን ጥላችሁ እንጀራ ፍለጋ የመጣችሁ ጓደኞቼና ወንድሞቼ መሆናችሁን በሚገባ አውቃለሁ ፤ የቤተሰብ ፍቅርም ምን ያክል እንደሚጎዳም ይገባኛል ። የቤተሰባችሁ ጉዳይ አሳስቧችሁ ወደ አገር ቤት የመመለስ ውሳኔ ካላችሁ በግል እየመጣችሁ ንገሩኝ ። እኔን ብላችሁ ፣ እኔን አምናችሁ እንደመጣችሁ ሁሉ እኔም ቃሌን በመጠበቅና ውሳኔያችሁን በማክበር በየትም ይሁን በየት መልሼ ከቤተሰቦቻችሁ እንድትቀላቀሉ አደርጋለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ ሁኔታውን እዚሁ በመቆየት ለማየት ከወሰናችሁም ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ ከእናንተ የሚደርስ አንዳችም ነገር አይኖርም ፤ ይህ አገር የእናንተም አገር ነውና በሰላም መቆየት ትችላላችሁ ። እንግዲህ ውሳኔያችሁን በግል እየመጣችሁ አሳውቁኝ "። እንዳለን አስታውሰዋለሁ" ። ዛሬ ለምን ሁለቱን ብቻ ይዘዋቸው ሄዱ ? ታፍነው እየተወሰዱ ይሆን እንዴ ? በማለት ነው የተሸበርኩት ።

ከአመት በፊት ሜይ 28 ቀን 1998 ዓም ሻብያ ሁለት የአየር ኃይል በራሪዎችን አፍኖ ወሰዳቸው የሚል ዜና በግል ጋዜጣ ያነበብኩበትን ጊዜ አስታወስኩ ። ጋዜጣውንም ይዤ አዛዡ ቢሮ በመግባት አስነበብኩት ። ለምንና እንዴት ሊታፈኑ እንደቻሉ ምክንያቱን ጠይቆ እንዲነግረኝና እንዲያስለቅቃቸውም አጥብቄ ተማፀንኩት ። አዛዡም ለደቂቃ ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ "እንዲያው አንተ ስታስበው ሻብያ እነዚህን ጁኒር በራሪዎች በምን ምክንያት ሊያፍናቸው ይችላል ብለህ ታስባለህ ? ዝም ብሎ በየጋዜጣው የተፃፈውን እውነት ነው ብለህ ትቀበላለህ ማለት ነው? በእርግጠኝነት ወያኔ እራሱ አፍኗቸው ዞር ብሎ ደግሞ በጋዜጣ ሻብያ ነው ያፈናቸው ብሎ እንደሚያስወራ አልጠራጠርም ። ሻቢያ እነ ኰ/ል በዛብህ ጴጥሮስንና ሻለቃ ጥላሁን በዛብህን በነፃ አሰናብቶ እነዚህን ወጣት በራሪዎች የሚያፍንበት ምን ምክንያት ይኖረዋል ? ደግሞም በዚህ ላይ ያሳደኳቸው ልጆቼ መሆናቸውን አትርሳ ። ለነገሩ ነገ ከነገ ወዲያ እውነቱን ታውቀዋለህ" ያለኝን ሙሉ ለሙሉ በአዕምሮዬ ከለስኩት ።

ዛሬ ደግሞ ስለ እነ ኰ/ል ማርቆስ ምን ብዬ እንደምጠይቀው እያሰላሰልኩና ልቤ እያመነታብኝ የደመነፍሴን በቀስታ እየተጐተትኩ ወደ ቢሮው ተጠጋሁ ። በሩን ለማንኳኳት እጄን እንደዘረጋሁ ከውስጥ የሰዎች ድምፅ ሰማሁና ባለሁበት ቆምኩኝ ። ለነገሩ ከውስጥ የሚነጋገሩትን ሰዎች በድምፃቸው ለመለየት አልተቸገርኩም ።

ድምፁ ከፍ ብሎ የሚሰማው ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ ነበር ። ኰሎኔል ዋቅጋሪ በተፈጥሮው ድምፁን ዝቅ አድርጎ መናገር የማይሆንለት ፣ እንደ ልቡ በነፃነት የፈለገውን የሚናገር ሰው መሆኑን ከድሮም አውቃለሁ ። ሲበዛ ቅንና የዋህ ሰው ነው ።

ሁለተኛው በሳቁ የለየሁት ሰው ደግሞ ዶ/ር ኤፍሬም ይባላል ። ሰውነቱ ሁሉ እስኪንዘፈዘፍ ድረስ ስለሚስቅ አሳሳቁ በዙርያው

ያሉትን ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲስቁ ያደርጋቸዋል ። ጨዋታ ወዳጅ ፣ ለጓደኞቹ ልዩ ፍቅር ያለውና ለመዝናናት ሙት የሆነ ሰው ነው ።

ዶ/ር ኤፍሬም ፍሰሃን አስመራ እስከማገኘው ድረስ የጅማ ልጅ አድርጌ ነበር የምቆጥረው ። በእርግጥም ተወልዶ ያደገው ጅማ ነው ። በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ የአቪዬሽን ዶ/ር ሆኖ ሲያገለግል አውቀዋለሁ ። ከሁሉም የአየር ኃይል አባላት ጋር ጥሩ ግንኙነት የነበረውና ከትንሹም ከትልቁም ጋር አብዝቶ ተግባቢ ሰው ነው ። በስራም ሆነ በግል ጉዳዮች በተደጋጋሚ የተገናኘን በመሆኑ ከመግባባት የዘለለ ጥሩ እውቂያ ነበረን ። በአሁኑ ሰዓት በኤርትራ አየር ኃይል ውስጥ የአቪዬሽን ዶ/ር ሆኖ እየሰራ ይገኛል ። ያው እንደ ድሮው ከኢትዮጵያውያኖች ጋር እጅግ የቀረበ ወዳጅነትና መግባባት አለው ።

የአዛዡን ቢሮ ለማንኳኳት ሳልደፍር ደፉ ላይ እንደቆምኩ በሩ ድንገት ተከፈተና ውስጥ የነበሩት ሰዎች ተያይዘው ከቢሮ ወጡ ።

አዛዡ ኰማንደር ሃብተፅዮን ሃድጉ- በቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በተለያዩ ተዋጊ ስኳድሮን ውስጥ ሲያገለግል የነበረና በ1990 መጀመሪያ ላይ አውሮፕላን ይዞ የመን የገባ ሲሆን ከመንግስት ለውጥ በኋላ የኤርትራ አየር ኃይል አዛዥ ሆኖ እያገለገለ ነው።

ኰ/ል አብርሃም ዕቁባ ስላሴ- ቀደም ሲል በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በበራሪነት ሲያገለግል ቆይቶ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ተዛውሮ ሲሰራ የነበረና ከመንግስት ለውጡ በኋላ ወደ ኤርትራ በመምጣት አየር ኃይሉ ውስጥ ም/አዛዥነት ሆኖ ይሰራል።

ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ የወለጋ ሰው ነው ። በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በተለያዩ ተዋጊ ስኳድሮኖች ውስጥ ሲያገለግል የነበረና ከፍተኛ ልምድ ካላቸው ኢትዮጵያውያን በራሪዎች መካከል አንዱ ነው ። ከመንግስት ለውጥ በኋላ በስደት ሌላ ጐረቤት አገር ሲኖር ቆይቶ በአሁኑ ሰዓት ኤርትራ ውስጥ ይኖራል ።

ኰ/ል ታደሰ ሙሉነህ ተወልዶ ያደገው ባህር ዳር ነው ። እንደ ኰ/ል ዋቅጋሪ ሁሉ በኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊ ስኳድሮን ውስጥ ከፍተኛ ልምድ ያለው በራሪ ነው ። ከመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ ኤርትራ በመምጣት በአየር ኃይሉ ውስጥ በበረራ አስተማሪነት እያገለገለ ያለ ነው ። አብሯቸው ዶ/ር ኤፍሬም ፍሰሃም አለ ።

ከሁሉም ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ኰ/ል ታደሰ ገንጠል ብሎ ወደ እኔ በመጠጋት ወዴት ነህ ? ... እንሂድ እንጂ አለኝ ።

የስራ መውጫ ሰዓት በመድረሱ ወደ ቤት እንሂድ ማለቱ ነበር ፤ ልቤ ነገር እንዳረገዘ እሺ ብዬው ተከተልኩት ።

ከኰ/ል ታደሰ ጋር ወደ መኪና ውስጥ ልንገባ ስንል ኰ/ል ወቅጋሪ ገመቹ ድምፁን ከፍ በማድረግ ባለቤቴን ወደቤት አድርሺያት ቶሎ እመለሳለሁና ቱሉ ጋ ጠብቁኝ በማለት እየተጣደፈ ወደ አየር ኃይል ሆስፒታል አቅጣጫ ባለቤቱን ዶ/ር ሊያ ጋቢሳን ሊያነሳ ሲሄድ እኛም ወደ ቤት መሄዱን ትተን ቱሉ ወደ ሚገኝበት አቅጣጫ አቀናን ።

የኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ ባለቤት ዶ/ር ሊያ ጋቢሳ ይባላሉ ። በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ እስከ መንግስት ለውጥ ድረስ በሃኪምነት ሲያገለግሉ ነበር ። ከ1998 ዓም በኋላ ግን እዚህ አስመራ በመምጣት በኤርትራ አየር ኃይል ውስጥ እንደቀድሞው በሃኪምነት እየሰሩ ነው ።

ከኰ/ል ታደሰ ጋር ወደ ከተማዋ አቅጣጫ መንዳት እንደጀመርን ትኩር ብሎ እየተመለከተኝ ምን ነው ? ምን ሆነሃል ? ችግር አለ እንዴ ? ብሎ አከታትሎ ጠየቀኝ ። በውስጤ የቋጠርኳትን ነገር ፊቴ ላይ እንዳነበበ ገባኝ ። ፈጥኜም እነ ጂሚ ከአዛዡ ቢሮ ወጥተው እየተጣደፉ ጭቃ በመሰለች መኪና አሳፍረው ሲወስዷቸው አይቼ ጉዳዩ አሳስቦኝ ነው አልኩት ። ቀጥዬም ሁኔታውን በተመለከተ የሚያውቀው ነገር እንዳለ አክዬ ጠየቅኩት ? ። ማ/ቴክ ግርማ ለማን "ጂሚ" በሚል የተለምዶ ስያሜ እንጠራዋለን ። ከ1991ቱ የመንግስት ለውጥ በኋላ አስመራ በመምጣት ኤርትራ አየር ኃይል ሄሊኮፕተር ስኳድሮን ውስጥ በበራሪ ቴክኒሻንነት የሚያገለግል ሲኒዬር መካኒክ ነው ።

አንዳች ነገር ትዝ እንዳለው ሁሉ .. እእ .. በማለት ጀመረ ኰ/ል ታደሰ ። አስከትሎም እነ ጂሚማ ወደ ባድመ ዘምተዋል በማለት ፊቱን ወደ እኔ እየመለሰ ፈገግ ብሎ መለሰልኝ ። ፈገግታውን አልወደድኩለትም ፣ በደምብ ያላዳመጠኝና ያልተረዳኝም መሰለኝ ። እናም ድምፄን ከፍ አድርጌ ... እውነቴን

እኮ ነው ፤ በሆነ መኪና ጭነው ወስደዋቸዋል እያልኩህ ነው ብዬ ስጋቴን ደገምኩለት ። ነገሩን እንዳላጤነውና እንዳልገባው ሁሉ ።

እኔም እውነቴን ነው ። ባድሜ አካባቢ አንድ ሚ-35 ወድቃ ተገኝታ እሷን ለማምጣት ወደዛ ዘምተዋል አለኝ ... ከረር ባለና እርግጠኛ በሆነ ድምፅ ።

ጭራሽ አሁን የባሰውን ግራ ገባኝ ። እንዴት ነው ሄሊኮፕተር ወድቆ የሚገኘው ? ዛሬ ደግሞ ሔሊኮፕተር እንደ ሳንቲም መሬት ወድቆ ይገኝ ጀመር እንዴ ? ለመሆኑ መቼ ነው ወድቆ የተገኘው ? የትስ ነው የተገኘው ? ፓይለቶቹስ የት ገቡ ? በማለት መላ ቅጡ የጠፋውን ጥያቄን አከታትዬ ደረደርኩለት ።

ኰ/ል ታደሰ እንደተምታታብኝና እንደ አመረርኩ በመገንዘብ ... ወደ ባድሜ ግምባር .. ማይድማ ከሚባል አካባቢ ነው አሉ ፤ አለኝ መቀለዱን በማቆም ። ሄሊኮፕተር ማርከናል ነበር የተባለው ፤ እኔ ግን ክሩዎች ስላልተገኙ ነው ወድቆ ተገኝቷል ያልኩህ በማለት ግልፅ ሊያደርግልኝ ሞከረ ። ከዚህ ውጪ ብዙ ዝርዝር ነገሮችን አልሰማሁም ነገር ግን ነገ ከሄዱበት ሲመለሱ ሁሉንም ታሪክ እንሰማዋለን አለኝ በረዥሙ እየተነፈሰ ።

የማይመስል ነገር ! አልኩት ጥርጣሬ ውስጤ እንደተቀበረ በሚገልፅ ቅላፄ ። እየነገረኝ ያለውን ታሪክ ለማመን እየተቸገርኩ ።

ሚ-35 ተዋጊ ሔሊኮፕተር

ጦርነት እኮ ነው ! አለኝ በጨኸት ንግግሬን አቋርጦ ። አስከትሎም የጦር መሳሪያ ወድቆ ልታገኝ ትችላለህ ፣ ታንክ ልትማርክ ትችላለህ ። ሔሊኮፕተርም እኮ የጦር መሳሪያ ማለት ነው ። በጦርነት ላይ ምንም ሊከሰት እንደሚችል ማወቅ አለብህ ፤ ምኑ ነው ያስደነቀህ ? ... አለኝ ። እንዲህ እየተነጋገርን ሳናስበው ቱሉ ዘንድ ደረስንና ሰላምታ ተለዋወጥን ።

ቱሉ ሁልጊዜ ሲያገኘን ይደሰታል ። እንደ ወንድሞቹም ይመለከተናል ። እኛም እሱን ለመጠየቅ ስንል አዘውትረን ወደ እሱ ጋ ጐራ እንላለን ። እናንተን ሳገኝ ውስጤን ደስታ ይሰማዋል ይለናል ።

ቱሉ ሰላሌ ተወልዶ ያደገ ለግላጋ ወጣት ነው ። በእናቱ ወይም በአባቱ ከኤርትራ በመወለዱ ምክንያት የሻብያና ሕውሃት ግጭት እንደተጀመረ ከኢትዮጵያ ተባረረ ። የኤርትራን ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጠው ከኢትዮጵያ ተባሮ የመጣ ጊዜ ነው ። ትግሪኛ ጀሮውን ቢቆርጡት እንኳ አይሰማም ። እሱ እንደሚለው ከሰላሌ ፈፅሞ ወጥቶ አያውቅም ።

ከሁሉም የተቸገረበት ጉዳይ ማንም በኤርትራዊነት ሊቀበለው ያለመቻሉ ነው ። አብዛኛው ኤርትራዊ ቱሉ እባላለሁ ብሎ ሲተዋወቃቸው የሚያሾፍባቸው እየመሰላቸው ከት ብለው ይስቁበታል ። ቱሉ ብሎ ኤርትራዊ እያሉ ፊት ለፊት ይሳለቃሉ ። ቱሉ ታድያ በእጅጉ ይዝናል ። ይኼኔ ተወልዶ ያደገባትን ሰላሌን ይናፍቃል ፣ የሚወዳትን ሰላሌን ተነጥቋልና ይቆጫል ።

ቱሉ ዘወር ሲልልን እኔና ኰ/ል ታደሰ ቀደም ብለን ወደ አቋረጥነው ጨዋታችን በመመለስ "የሚወራው እውነት ከሆነ ሻብያ አንድ ተዋጊ ሄሊኮፕተር ቀናው ማለት ነው" አለኝ ኰ/ል ታደሰ በሹክሹክታ ። አያይዞም "አየህ ባለሙያን አክብሮ መያዝ ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው ። ኰ/ል ማርቆስ እዚህ ኤርትራ መኖር ባይችል ኖሮ ይህቺን ሄሊኮፕተር በዚህ ፍጥነት ለማምጣት ማን ይሄድ ነበር አለኝ ?" በወቅቱ ድፍን ኤርትራ ቢታሰስ ተዋጊ ሔሊኮፕተሮችን ለመብረር ከኰ/ል ማርቆስ ውጪ ሌላ ብቁ በራሪ ያለመኖሩን በመገንዘብ ። "አየህ ባለሙያ ወርቅ ማለት ነው ። በክፉ ቀን ይጠቅምሃል ። ለዚህም ነው ሃገር ከፍተኛ ሃብት የምታፈስበቸው ። ሃብተፅዮን የባለሞያን ጥቅም ስለሚያውቅ በቀላል ወጪ ተገቢውን ሙያዊ ክብር እየሰጠን አዲሱን አየር ኃይላቸውን እንድንገነባ ያደርጋል" ። በማለት በአገራችን ሁኔታ እየተቆጨ ነገረኝ ።

እኔና ኰ/ል ታደሰ ሞቅ ባለ ጨዋታ ውስጥ ሰጥመን ሳለን ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ እየተጣደፈ በመግባት ድምፁን ከፍ አድርጐ ቱሉን በኦሮምኛ ሲያናግረው ሰማን ። " አካም ጅርታ ቱሉ " ...... ። ቱሉ እናቱ የመጣችለት ያክል ፊቱ ሁሉ ጥርስ በጥርስ ሆኖ ወደ ኰ/ል ዋቅጋሪ በመጠጋት በደስታ ይፍነከነካል ። በላይ በላዩ እየተጣደፈ ኦሮምኛውን ያስኬደዋል ። ሁለቱም ከጣሪያ በላይ ይስቃሉ ።

የኰ/ል ዋቅጋሪ በራስ መተማመን የሚገርም ነው ። በኦሮምኛም በአማርኛም .... ሲያሰኘውም ትግሪኛም እየቀላቀለ ድምፁን ከፍ አድርጐ ይጫወታል ። ለእርሱ አዲስ አበባም አስመራም ... መቀሌም ሆነ ነቀምት ልዩነት የላቸውም ።

እንደልቡ ድምፁን ከፍ አድርጐ በፈለገው ቋንቋ መናገር ያደገበትና የኖረበት በመሆኑ ዕከሌ ምን ይለኛል ብሎ አይሸማቀቅም ። ቱሉም ለዚህ ይመስለኛ የመሃል አገር ሰዎችን በሩቅ ሲመለከት በደስታ የሚፍነከነከው ።

ይኼኔ ጥሩ አጋጣሚ ስለአገኘሁ ፊቴን ወደ ኰ/ል ዋቅጋሪ መልሼ " ጌታዬ .. መጀመሪያ አስመራ ከእነ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ ጋር ያገኘሁህ ጊዜ በኦነግነት አምተንህ ነበር " አልኩት ። ያኔ እንዳየሁት ወደ ቤቱ ሄጄ ለኰ/ል ግርማ ጫላ ኰ/ል ዋቅጋሪን ከእነ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ ጋር ቆሞ አየሁት ብዬው የነገርኩትንና ኦነግ ሆኖ መጥቶ መሆን አለበት ብለን ያማነውን በማስታወስ ።

ንግግሬ ያስቆጣው ኰ/ል ዋቅጋሪ በስጨት ብሎ " አንተ! ምነው ባክህ ? አየር ኃይል እኮ ነው ያሳደገኝ ... ተማሪ ሆነን እንኳ ዶርሚተሪያችን (መኝታ ቤታችን) ቤጌምድር ፣ ወለጋ ፣ ወሎ ... ነው እንጂ ኦሮሞ .. አማራ የሚል ስያሜ አልነበረውም ። እንዴት እዚህ ድረስ ዝቅ አድርገህ ትገምተኛለህ ? እኔ እኮ ከአየር ኃይል ጋር የኖርኩ ፣ በዘር ዘምቢል ውስጥ ገብቼ ልኖር የማልችል ባለ ሰፊ ማህበረሰብ አካል ነኝ " አለኝ ከልቡ ውስጡን እየተሰማው ። ለነገሩ እኔም ይህንን አውቃለሁ ። አየር ኃይል ከመላው አገሪቷ እየዘረ የሚያመጣቸውን አዲስ ምልምሎች በሶስት ወራት ስልጠና ብቻ እንዴት አድርጐ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በሆነ ብሄራዊ መንፈስ እንደሚቀርፅና ከአንድ እናት የተፈጠርን ወንድማማች አድርጐ እንደሚያወጣን በውስጤ እየመሰከርኩ ። እናም ጥፋተኝነት ተሰምቶኝ ከመቀመጫዬ ብድግ ብዬ ኰ/ል ዋቅጋሪን ይቅርታ ጠየቅኩት ።

በመንግስት ለውጡ ሳቢያ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሙሉ ለሙሉ እንዲበተን ከተፈረደበት በኋላ ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ሰኔ 1998 ዓም አስመራ አየር ኃይል ቤዝ ውስጥ ከፕሬዝዳንት ኢሳያስና ከጀ/ል ስብሃት ኤፍሬም ጋር ቆመው ሲያወሩ ነበር ። ሰላም ለማለት ሰስቱ ወዳሉበት አቅጣጫ ስጠጋ ድንገት ያስተዋለኝ ኰ/ል ዋቅጋሪ አፉን በመዳፉ እየሸፈነ በመደነቅ "አንተም ኤርትራዊ ነህ " ? ያለኝ ምንግዜም አይረሳኝም ። ድሮ አብረን ስንኖር የቱ ከኤርትራ የትኛው ደግሞ ከትግሬ መሆኑን ለመለየት እንደማንጠያየቅ በሚያስታውቅ ቅላፄ ።

"የለም ጌታዬ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ፤ እዚህ ኤርትራ ለስራ መጥቼ ነው" በማለት ሶስቱንም በየተራ ጨበጥኳቸው ። "አሃ! እንደ እነ ኰ/ል ታደሰ ነሃ" ብሎኝ በሌላ ጊዜ በሰፊው እንደምንገናኝ ገልፆልኝ እንደተለየኋቸው አስታውሳለሁ ።

ኰ/ል ዋቅጋሪ ኢህአዴግ አገሪቷን እስኪቆጣጠር ድረስ የሶስተኛው አየር ምድብ (ድሬዳዋ ቤዝ) አዛዥ ነበር ። በመጨረሻዋ ደቂቃ ከሌሎች በራሪዎች ጋር በአንቶኖቭ 12 አውሮፕላን ወደ ኬንያ ይሰደዳል ። ከኬንያም ወደ ኡጋንዳ በመሻገር በኡጋንዳ አየር ኃይል ውስጥ በበራሪነት አግልግሏል ። ሙያውን እየሸጠ ጥሩ ኑሮ ነበረው ።

ከሰባት ዓመታት የኡጋንዳ ኑሮ በኋላ ኤርትራና ሕውሃት ወደ ግጭት ሲያመሩ ሕውሃቶች ቀርበው ሊያግባቡት ይሞክራሉ ። " አገራችን በባዕዳን ተወራለችና ይህንን የድፍረት ወረራ ልዩነታችንን በማቻቻል አብረን እንመክት " ይሉታል ። አገር የመከላከሉን ጉዳይ ኰ/ል ዋቅጋሪ አልጠላውም ። ነገር ግን አንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሳቱ ከሕውሃት ተወካዮች ጋር ሊግባባ አልቻለም ። ወደዚህ ወደ ኤርትራም ለሶስተኛ ጊዜ እንዲሰደድ ያደረገውም ይኸው የሕውሃቶች ትንኰሳ እንደሆነ ይናገራል ።

ኰ/ል ዋቅጋሪ እኛን ተቀላቅሎ እንደተቀመጠ ስለ ኰ/ል ማርቆስና ማ/ቴክ ግርማ ጉዳይ መነጋገራችን ቀጠልን ።

ኰ/ል ማርቆስ ሰለሞን በቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል በሔሊኰፕተር ስኳድሮን ውስጥ ታዋቂና ሲኒየር በራሪ ነበር ። ተወልዶ ያደገው ሐረር ውስጥ ከወታደር ቤተሰብ ነው ። በኋላም ሐረር የጦር አካዳሚ በመግባት በመኰንንነት ተመርቆ በአርሚ አቭዬሽን ውስጥ ቀጥሎም በኢትዮጵያ አየር ኃይል የተለያዩ ስኳድሮኖች ውስጥ በበራሪነት አገልግሏል ። የመንግስት ለውጡን ተከትሎ እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል በራሪዎች በአዲሱ መንግስት በሌሉበት የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው ውስጥ አንዱ ሆኗል ። በስደት ወደ ኤርትራ በመምጣትም በኤርትራ አየር ኃይል ውስጥ በሔሊኰፕተር በራሪነትና በአስተማሪነት ያገለግላል።

እነሆ ዛሬ በባድመ ግምባር ማይድማ አካባቢ አንድ ሔሊኰፕተር ወድቃ ተገኝታለች መባሉን ተከትሎ ወደ ባድመ በመሄድ ሔሊኮፕተሯን ለማምጣት መዘመታቸውን ኰ/ል ታደሰ እየነገረን ቢሆንም እንዴት ተበላሽታ የወደቀች ሔሊኰፕተርን አስነስተው ሊያመጡ ይችላሉ ? በማለት ግራ እየገባኝ ያለውን ጉዳይ ጠየቅኩ ።

ኰ/ል ዋቅጋሪም ሃሳቤን በመቀበል ሌላ ተጨማሪ ስጋት ይሆናል ያለውን ሃሳብ ሰነዘረ ። "እንዲያው የፈለገውን ያክል የዘመኑን የአየር ኃይል ኃላፊዎች አሳንሰን ብናያቸውም ይህቺን ሔሊኰፕተር ለጠላት አሳልፈው የሚሰጡ አይመስለኝም ፤ በፍጥነት ያለችበት ድረስ በመሄድ ለማውደም መሞከራቸው አይቀርም ። በዚህ ላይ ዘመቻውን በአማካሪነት እያገለገሉ ያሉት ስመ ጥሩው ብ/ጀ ተጫነ መስፍን መሆናቸውን አንርሳ ። ጀ/ል ተጫነ ሔሊኰፕተሯን ማውደም እንደሚገባ የሚጠፋቸው ሰው

አይደሉም ። ስለዚህ ይህ ዘመቻ ለእነ ኰ/ል ማርቆስ አደገኛ ሊሆን ይችላል በማለት ስጋቱ ገለፀ ።

ጄ/ል ተጫኔ መስፍን ኩረም ወሎ ተወልደው ያደጉ ናቸው ። በፈረጀቹ 1955ዓም አየር ኃይልን ተቀላቅለው በተለያዩ ተዋጊ ስኳድሮኖች ውስጥ በተዋጊ በራሪነት ካገለገሉ ምርጥ በራሪዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን በቅተዋል ። በጀ/ል ማዕረግ ወደ መከላከያ ሚንስቴር ተዛውረው በዘመቻ መምሪያ ውስጥ ለበርካታ አመታት አገልግለዋል ። ኢህአዴግ አገሪቷን እስኪቆጣጠር ድረስ በሌሊት እየተነሱ ከአዲስ አበባ ደብረ ዘይት ድረስ በመንዳት በጀት በረራ ማሰልጠኛ ስኳድሮን ውስጥ እኔን ጨምሮ ተዋጊ በራሪዎችን ያስተምሩ የነበሩ መንፈሰ ጠንካራ የአየር ሰው ናቸው ። በዚያ ዘመን የነበሩትን ወጣት በራሪዎች ሁሉንም ማለት ይቻላል እርሳቸው ያላስተማሩት ሰው አይገኝም ። በተዋጊ ጀት አውሮፕላን በራሪነት ያከማቹት ሰዓት በአፍሪካ አህጉር ሻምፒዮናነቱን እንደያዙ እንዲቆዩ አድርጓቸዋል ። ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣ ማግስትም ወህኒ በመውረድ ለሰባት ዓመታት ከርቸሌ ተከርችሞባቸዋል ። በ1998 ዓም በሻብያና ወያኔ ግጭት ሳቢያ ሙያቸውን ለመጠቀም ከእስር ተፈተው በአየር ኃይል ዘመቻ መምሪያና በዘመቻ አማካሪነት እያገለገሉ ነበር ።

ይህንን የጀ/ል ተጫኔን ዕምቅ ልምድ ነው ኰ/ል ዋቅጋሪ የፈራው ። እኚህ የተዋጣላቸው የአየር ኃይል ባለሙያ አማካሪነት አይደለም አየር ኃይሉን እራሱን የማዘዝ ብቃት አላቸው እያለን ነው ፤ ኰ/ል ዋቅጋሪ ። ስለዚህ የእነ ኰ/ል ማርቆስ ወደ ባድመ የመዝመቱ ጉዳይና ወደቀች የተባለችውን ሔሊኰፕተር ወደ አስመራ እየበረሩ የማምጣቱ ጉዳይ የሚሳካ እንዳልሆነ በዝርዝር አወጋን ።

አያይዘም "ጀ/ል ተጫኔ በአማካሪነት መመደባቸውን የሰማሁ ግዜ እጅግ ተደስቼ ነበር አለን ። ሁኔታዎች ይሻሻላሉ ብዬም ተስፋ በማድረግ ወደ አገር ቤት ለመመለስም አስቤ ነበር ። የታሰሩት ይፈታሉ ፣ የተሰደዱትም ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ። አየር ኃይልም ወደ ነበረበት ተመልሶ ለአገር ጠቃሚ እንደሆነ ይቀጥላል ። ቂምና በቀልም ያከትማል ብዬ ሙሉ ለሙሉ አስቢያለሁ ። ፖለቲካውና ሙያው ይለያያሉ ። ስለ አገራችንም ሆነ ስለ አየር ኃይል በአዲሶቹ መሪዎች በኩል የተሻለ ግንዛቤ አግኝቶ ... ሁላችንም አገራችንን መልሰን የምናገለግልበት ሁኔታ ይመቻቻል እያልኩ ነበር ።

"አገር ተወራለች ፣ ዳር ድንበራችንም ተደፍሯል .. ልዩነታችንን አስወግደን አገራችንን በጋራ መከላከል አለብን ብለው ሲያነጋግሩኝ መጀመሪያ ፈቃደኛ ሆኜ ነበር ። "በኋላ ግን አንድ ጥያቄ አቀረብኩላቸው ። "እዚህ ድረስ እኔን መጥታችሁ እንዳናገራችሁኝ ሁሉ እዚያው አገር ውስጥ በእስር ላይ ያሉትንስ ጠይቃቿኋቸዋል ወይ? "ብዬ ጠየቅኳቸው ።

"አይይይ ... እነሱ እኰ በቀይ ሽብር ጉዳይ ተከሰው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ያሉ ሰዎች ናቸው" ብለው ሲመልሱልኝ እንደዋሹኝ አረጋገጥኩ ።

"በእስር ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ጓደኞቼ ናቸው ። ከአየር ኃይል ስራ ውጪ ከቀይ ሽብር ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ጉዳይ እንደሌለ እራሴን የማውቀውን ያክል ጓደኞቼን አውቃቸዋለሁ ። ስለዚህ ነገሩ ሁሉ አላምር አለኝ ። ጓደኞቼ በቀይ ሽብር ሳቢያ ነው ከርቸሌ የወረዱት የሚለውን የውሸት ክስ አምኜ ወደ አገር ከምመለስ ብሞት ይሻለኛል ብዬ የአብሮ እንስራ ጥያቄያቸውን አልቀበልም ብዬ እምቢ አልኳቸው።

አያይዘም በጄ/ል ተጫኔ ግን እስከ መጨረሻው ተስፋ አለኝ ። የአየር ኃይልን የበቀለ ክስ ያስቀለብሳሉ ። በግፍ እስር ቤት የሚማቅቁትን ጓደኞቻችንና በሌሉበት የሞትና የዕድሜ ልክ ፍርደኞችን ነፃ እንዲወጡ ይጥራሉ ብዬ አስባለሁ ። ይህንን ሳይፈፅሙ ቀርተው ከህውሃት ጋር አብረዋቸው በመስራት የሚዘልቁ ከሆነ ግን እንተዘዘባለን" ብሎን በረዥሙ ተነፈሰና ወጉን ጨረሰ ።

እንደ ፈራነው ሳይሆን በነጋታው ጠዋት ከስራ መግቢያ በፊት የባድሜዋ ሔሊኮፕተር በቀድሞው ባለቤቶቿ አማካኝነት አስመራ አየር ማረፊያ በሰላም ደረሰች ። በፍፁም ሊታመን የማይችል ነው ። በስርዓቱ እየሰራች ያለች አውሮፕላን ለጠላት ጥሎ መሄድ ምን የሚሉት ቸርታ እንደሆነ መገመቸ አስቸጋሪ ሆነ ። ሄሊኰፕተሯን መብረር ባይቻል እንኳ ጠላት እጅ ገብታ መጠቀሚያ እንዳትሆን ማውደም ማንን ገደለ ? በአለም የምርኰ ታሪክ የዚች ሄሊኰፕተር ጉዳይ የመጀመሪያው መሆን አለበት ። እንዲሁ እንቅልፍ እንዳጣሁ ስገላበጥ አድሬ ንጋት ላይ ገና ሸለብ እያደረገኝ በነበረበት ሰዓት ነው የሄሊኰፕተር ድምጽ በመኖሪያችን አናት ላይ ሲያልፍ የሰማሁት ። ዘልዬ ከአልጋዬ ላይ በመነሳት ወደ አየር ኃይል ግቢ አመራሁ ። በረራ መስመር ስደርስ አዛዣን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ሄሊኰፕተሯን ከብበው

በአሸናፊነት ይመለከታሉ ። ኢትዮጵያዊው የአርማሜንት (የጦር መሳሪያ) ስፔሺያሊስት ማ/ቴክ አርጃ ጴራ በደቂቃዎች ውስጥ ሄሊኮፕተሯ የታጠቀችውን መሳሪያ ሁሉ ፈታትቶ መሬት ላይ ዘረገፈው ። ሄሊኮፕተሯ ጥይትና ሮኬት ታጥቃ ነበር ። ውስጤ ሲሸማቀቅና የመዋረድ ስሜት አንገቴን አስደፋኝ ። እንዴት እንደዚህ አይነት ስህተት ይሰራል ። በምንስ ምክንያት ይህቺን ሄሊኮፕተር ባለችበት ማውደም ከበድ ሆነ ? እጅግ አሳፋሪ ሆኖ ተሰማኝ ።

አዛዡ ኮክፒት ውስጥ ያገኛቸውን ቁሳቁሶች ይዞ ወረደ ። ከበራሪዎቹ ጋር የነበሩ ፎቶ ግራፎች ተገኙ ። የማውቃቸው ጓደኞቼ ናቸው ። ከፎቶ ግራፎቹ መካከል የቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ዜጎችም ይገኙበታል ። በዚህኛውም ወገን አስመራ ያሉት የቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ዜጎች በፎቶ ግራፉ ላይ የሚመለከቷቸውን በራሪዎች ያውቋቸዋል ። አለም እንደዚህ ናት ። በዚህም ወገን ሆነ በዚያኛው ወገን በገንዘብ የተገዙ ጓደኛሞች ኖረዋል ጦርነቱን የሚዋጉት ።

የኤርትራው አየር ኃይል አዛዡ የደስታና የአሸናፊነት ስሜት ጐልቶ ይንፀባረቅበታል ። ኮ/ል ማርቆስንና ማ/ቴክ ግርማን እያቀፈ አድናቆቱን ይለግሳቸዋል ።

ሄሊኮፕተሯን ዞሬ ስመለከት ከሆዷ ስር ዙ-23 በሚመስል ጥይት መመታቷን አስተዋልኩኝ ። ጥይቱ የነዳጅ መስመሩን ጐድቶት ኖሮ ነዳጅ እየፈሰሰ እንደነበረ በሚገባ ያስታውቃል ። ለሄሊኮፕተሯ መውደቅ ምክንያት የሆነው በአየር ላይ ሆና ከምድር በተተኰሰ የአየር መቃወሚያ መመታቷ እንደሆነ ተገነዘብኩኝ ።

በኋላ ግን ኰማንድ ፖስትና ጠቅላይ መምሪያ ሆነው ጦርነቱን የሚመሩትን ሰዎች አምርሬ ረገምኩ ። እንዴት እንዲህ አይነት ስህተት በመስራት በአየር ኃይል ስሟ የገነነውን አገር ያዋርዳሉ ብዬ ወቀስኳቸው ። የዚህ ሁሉ ዝብርቅርቅ ክስተት ተጠያቂ ማን ነው ብዬ ሳስብ ሙያዊ ብቃት በሌላቸው ሰዎች የመመራቱ ጦስ እንደሆነ ደመደምኩ ። ሙያና ባለሙያ እንዲለያዩ ተደርጓል ። ኢትዮጵያ አገራችን በአፍሪካና በዓለም ደረጃ የነበራትን የአየር ኃይል ብቃት በማዋረድ በኩል ሌት ተቀን ተሰርቷል ።

በዚህ ሁኔታ አገር ሊገነባ እንደማይችል ግልፅ ነው ። ለዘመናት የአገር ኃብት የፈሰሰበትን ባለሙያ በአንድ ጀንበር አውድሞ ለባዕዳን ገፀ በረከት እንዲሆኑ ማድረግ አገርንም ሕዝብንም እንደሚጐዳ እያየነው ነው ።

ሚግ-21 ስኳድሮን ፣ አሥመራ

ኮ/ል ዋቅጋሪ ፣ ኮ/ል ታደሰ ፣ ኮ/ል ግርማ ፣ ኮ/ል ማርቆስ ፣ ማ/ቴክ ግርማ ፣ ማ/ቴክ አርጃ ..... ስንቱን ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ቆጥሬው እንደምዘልቀው አላውቅም ። ግን እነኚህ ሁሉ አገራችን በሚያስፈልጓት ሰዓት በክፉ ቀን ያልሆነ ቦታ ላይ የተገኙ ነበሩ ።

ኮ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ ከባለቤታቸው ከዶ/ር ሊያ ጋቢሳ ጋር

የአዛዥ ሹፌር

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል



ሻ/ባሻ ታደለ አሼቦ

ከ66ቱ አብዮቱ ቀደም ብሎ የአዛዥ የጄኔራል አበራ ወልደማሪያም ሹፌር ነበሩ። ቤተ መንግስት የሚገቡ የሚወጡ። ያን ጊዜ የግብር አበላል ሶስት ደረጃዎች ነበሩት። ሁሉም አንድ ላይ በአንድ ገበታ ላይ አይቀርብም። እሳቸው ሁለተኛው ደረጃ ላይ እንደነበሩ ነው በኩራት የነገሩን።

በጃንሆይ መንግስት ላይ የነበረው ተቃውሞ ከትምህርት ቤት አልፎ ወታደር ካምፕ ውስጥ ይገባና የደምዎዝ ጭማሪ ጥያቄ ይነሳል። የንጉሰ ነገስቱ አስተዳደርም ለወታደሩ ሰባት ብር ጭማሪ አድርጊያለሁ ይላል። አመጹን ለማብረድ። ይህንኑ ተከትሎ ከየጦር ክፍሉ የተወጣጡ የሠራዊቱ አባላትም ለግብር ኢዮቢሊዩ ይጠራሉ። ጃንሆይም እንግዲህ ሃገራችን ከዚህ በላይ አቅም የላትም። የቻልነውን አድርገናል ብለው ይናገራሉ። ሠራዊቱ በጭማሪው አልረካምና ግብሩ እንደተጠናቀቀ እንደተለመደው "ጃንሆይ ለዘላለም ይኑሩ!"፣ ሳይል ውልቅ ይላል። በሌላ ጊዜ ይህንን ውጥረት ለማላላት እንደገና የጦሩ ተወካዮች ወደ ቤተ መንግስት ይጋበዛሉ። ከአየር ኃይልም አንድ አውቶብስ ሙሉ የሠራዊቱ ተወካዮች ተመርጠው ተልከዋል። ይሁን እንጂ ጃንሆይ ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ሠራዊቱ ከአዳራሹ መውጣት ይጀምራሉ። ለዚህ ባሻ ታደለ የዓይን ምስክር ናቸው። በቤተ መንግስት ባሳለፉት አስራ ስድስት ቀናት ይህንንና ሌሎች ነገሮችን አይተዋል።

ልብ አድርጉ ባሻ ታደለ እዚህ ደረጃ የደረሱት ተስፋ ሳይቆርጡ ያለ ዕረፍት ብዙ ስለተጓዙ ነው። አየር ኃይልም እንዳንኳኩ ወዲያው በሩን አልከፈተላቸውም። የልጅነት ሕይወታቸው አልጋ በአልጋ አልነበረም ለማለት ነው። እሳቸው እራሳቸው በቅጡ በማያውቁት ቀንና ዓመት ምህርት ሲዳሞ ክፍለሃገር፣ ሃድያና ከምባታ ውስጥ ጥማባሮ በምትባል በታ ተወለዱ። ከአባታቸው ከአቶ ሻሄቦ ሳና እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወርቄ ቢጆሬ።

በ1949 ገደማ አጎታቸው ሻሸመኔ ለሚሽን ትምህርት ቤት ሲያስመዘግቧቸው በግምት የሰባት ዓመት ልጅ ነበሩ። በዚህ ስሌት የተወለዱት በ1942 አካባቢ ይሆናል የሚል ግምት ወስደናል። ለማንኛውም ትንሹ ታደለ እዚያው ሻሸመኔ ውስጥ እስከ ስምንተኛ ክፍል ገፍተው ከተማሩ በኋላ ዘመድ ወደ ደብረዘይት ያመጣቸዋል። ለተሻለ እንጀራ ፍለጋ። ዕድሜያቸው ብቻ ሳይሆን ሰውነታቸውም ትንሽ ነበር። ይሄ ደግሞ ያሰቡትን ወዲያው ለማግኘት እንቅፋት ሆኖባቸዋል።

ደብረዘይት ያገኙትን እየሰሩ ሰነባብተው ሲስተር ሣራን ይገናኙሉ። በዚያ ጊዜ ሲስተር ሣራ አየር ኃይል ውስጥ የሕክምና ባለሙያ ሆነው ይሰራሉ። በ1954 ላይ አየር ኃይል ለድሬሰር ሙያ እየመለመለ መሆኑን ያውቁ ነበርና ባሻ ታደለን ለማስቀጠር ወደ አየር ኃይል ይዘዋቸው ይሄዳሉ። መልማዩቹም ይሄ ልጅ ኮሳሳ ነው ከሲቪል ስራ ይልቅ ወታደርነት ቢቀጠር የሰጡትን እየበላ ሰውነቱም ይፋፋል ይሉና ይመልሷቸዋል።

በዓመቱ ሌላ በር ይከፈትላቸዋል። አየር ኃይል ውስጥ ወታደር ሆኖ ለመቀጠር። አሁንም ያው ኮሳሳ ሰውነታቸው ምክንያት ሆኖ ለውትድርና ገና ነው ይባሉና ግብር ቤት በአስተናጋጅነት እንዲሰሩ ይደረጋል። ዓመት ሳይሞላ ግን ሕልማቸው መጨረሻ ላይ ዕውን ሆነ። 1955 ጥር ላይ ከሌላ በታ ተመልምለው ከመጡ ወጣቶች ጋር ፍቼ ለወታደራዊ ሙያ ስልጠና ተላኩ። ከስድስት ወራት ስልጠና በኋላ ተመርቀው ወደ አየር ኃይል ይመጡና ኤየር ፖሊስን ይቀላቀላሉ። ከዚያ በኋላ ነው ብቃታቸው ተመዝኖ ወደ ሹፌርነት ሙያ የገቡት። በዚያ ጊዜ፣ ምናልባት አሁንም ጭምር የአዛዥ ሹፌር መሆን መቼም ከብዙዎች መሃከል መመረጥን ይጠይቃል።

ባሻ ታደለ የአዛዥ ሹፌር ሆነው ብዙ አገልግለዋል ። የመጨረሻዎቹን ቀናትም ከጄኔራሉ ጋር አሳልፈዋል። የቤተሰብ ያህል።ለአዛዡም ታምኝነታቸውን እስከፍጻሜው አሳይተዋል።

ስርአቱ ግን መለወጥ እንደነበረበት ያምናሉ። መሬት በጥቂቶች አጅ ነበር። የወታደሩም ሕይወት ጎስቋላ እንደነበረ ያውቃሉ። የአዛዡን የመጨረሻ ቀን ከማወቃቸው በፊት አባታቸው መታመማቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል። አባታቸውን ለመጠየቅ ፈቃድ ሲጠይቁ አይቻልም ይባላሉ። የአዛዡ ሹፌር ናቸዋ። የአየር ምድቡ አዛዥ ጄኔራል አሰፋጋ ሄደው አቤት ቢሉም መልሱ አንድ ይሆናል። አዛዡ ብቻ ናቸው መፍቀድ ያለባቸው ይባላሉ። እናም አዛዡ ዘንድ ቀርበው ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው። ከዚያ በኋላ ከጄኔራል አበራ ጋር አልተያዩም። መታሰራቸውንም የሰሙት በኋላ ነበር።



ባሻ ታደለ አየር ኃይልን በአጠቃላይ ለሃያ ስምንት ዓመታት አገልግለዋል። በዚህ የአግልግሎት ዘመናቸው አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፉት ሐረር ሜዳ ቢሆንም በሌሎች የአየር ኃይል ጣቢያዎችም ተዘዋውረው ሰርተዋል። በጥሩ የምግብ አዘገጃጀቱ ሐረር ሜዳ ውስጥ በመላ ሠራዊቱ ይታወቅ የነበረውን የኤየር ፖሊሲን ካፊቴሪያም በሃላፊነት መርተዋል።

ኢሕዲግ አየር ኃይልን ከተቆጣጠርበት ጊዜ ጀምሮ ወደ አየር ኃይል አልተመለሱም። ለስድስት ወራት ያህል ዴዴሳ ታስረዋል። ከዚያም ለስራ እንፈልግሃለን የሚል ተደጋጋሚ ጥሪ ቢቀርብላቸውም ሴት ልጃቸውን ያስታምሙ ስለነበር ጥሪውን አልተቀበሉም። ስራ ፈተው ግን አልተቀመጡም። መጀመሪያ ለበርታ ኮንስትራክሽን፣ ከዚያም ኡጋዴን ቤንዚን ፍለጋ ላይ ለተሰማራ አንድ የአሜሪካኖች ኩባንያ፣ ቀጥሎም ለግለሰብ የሕዝብ ማመላለሻ ተቀጥረው ሰርተዋል። መጨረሻ ላይ ተቀጥረው የሰሩት ደብረዘይት ውስጥ ኤልካ ተብሎ ለሚጠራ አንድ ድርጅት ነው። የሚገርመው ነገር ለእነዚህ ከላይ ለጠቀስናቸው ስራዎች ሁሉ የጋበዝዋቸው ቀደም ብለው የሚያውቋቸው የአየር ኃይል አባላት ነበሩ።

አየር ኃይልን የእናት ቤት ብለው የሚጠሩትም የሄ ተጨምሮ መሆን አለበት። አየር ኃይል የነበረ ሁሉ የአንድ ቤተሰብ አባል ነውና የትም ይሆን የት እርስበርሱ ይረዳዳል። ይደጋገፋል። አየር ኃይልን ውስጥም ሆነ ውጪ ሆነው የሚያውቁ ሰዎች በዚህ አባባል ይስማማሉ።

ባሻ ታደለ አየር ኃይል በነበሩበት ዘመን ቅር የተሰኙበትን ሁለት ጉዳዮች አልሸሸጉንም። አንደኛው አስመራ ሄደው ሶስተኛ መንጃ ፈቃዳቸውን ካወጡ በኋላ ለተሻለ ክፍያ ሌላ ስራ መግባት ይፈለጉና መለቀቂያ ይጠይቃሉ። ሰባት ዓመት አገልግሎት ሰለሰጡ ሕጉም ይፈቅድላቸው ነበር። ተከለከሉ። ሁለተኛው ጎዴ ሆነው ለመኮንንነት ኮርስ ፈተና ይወስዱና ያልፋሉ። ይሁን እንጂ ኮርሱን ሳይቀላቀሉ ይቀራሉ። በሁለቱም ጊዜ የተሰጣቸው ምክንያት አንድ አይነት እንደነበረ ነው የነገሩን። አንተን የመሰለ ጎበዝ ሰራተኛ አንለቅም፣ የሚተካህ ሰው ሰለማናገኝ የሚል።

ዛሬ አሜሪካ ውስጥ ከሴት ልጃቸው ጋር ሜኒሶታ ይኖራሉ። ወደዚህ ወደ አሜሪካ የመጡት 2010 ላይ ነው። 1993 ላይ በሞት ከተለይዋቸው ከባለቤታቸው ከወይዘሮ እሌኒ አሰፋ ጋር ስደስት ወልደው አራቱ በሕይወት አሉ። ሁለት ወንድ ሁለት ሴት። አያማርሩም። አየር ኃይል የትም ሄዶ በሙያው ሰርቶ መብላት የሚችል ነው፣ አየር ኃይሉ በሚገባ አሰልጥኖ ያዘጋጀው ማንኛውንም ፈተና እንዲቋቋም ነው የሚል የጸና ዕምነት አላቸው።

ባሻ ታደለ አየር ኃይል ውስጥ በኤር ፖሊስ ተቋም ውስጥ የተለያየ አገልግሎት ከሰጡት መሃከል አንዱና ጎልተው የሚታዩ ሰው ናቸው። በሹፌርነት ብቻ ሳይሆን የአየር ኃይሉን ደህንነትና ጸጥታ በማስጠበቅና በሌላም የሙያ መስክ አግልግሎት ያበረከቱ ኤየር ፖሊሶች ብዙ ናቸው። እንደሰማነው ከሆነ እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ይህንኑ ግዳጃቸውን ሲፈጽሙ መስዋት የሆኑም አሉ። ታሪካቸውን መዘከር ይገባናል።

-------------///-------------

ደጀኖቹ

ያኔ አልረሱንም ፤ ዛሬ እኛም አንረሳቸውም

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል



አቶ ገ/የስ የዛሬ አቋማቸው

አየር ኃይል የመለዮ ለባሾች ቤት ብቻ እንደሆነ የሚገምቱ ሰዎች የሉም ማለት አይቻልም። እኛ ውስጥ አዋቂዎች ካልተናገርነው በቀር። ለዚህም ነው አብራሪዎቹ ሰማይ ላይ ይዘውት የሚወጡትን አውሮፕላን የጠገኑና ያስታጠቁ፣ ለመጠገኛ የሚውለውን መለዋወጫ ሰፐላይ ውስጥ ያደራጁ፣ ወር መግቢያ ላይ በናፍቆት የምንጠብቀውን ደምወዝ ያዘጋጁ፣ ሃሳባችንን፣ዕቅድና ፕላናችንን የተየቡ፣ መልዕክታችንን ከአንድ ቢሮ ወደ ሌላው በታማኝነት ያቀበሉ፣ ክለብ ውስጥ ሰርተው የመገቡንና እንዲሁም ሰፍተው ያለበሱንን ሲቪል አየር ኃይሎችበመጽሔታችን የምንዘክረው።

ለዛሬው እዚሁ አሜሪካ ሃገር ሜሪላንድ፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ውስጥ ያገኘናቸውን ደጀን ብለን ከምንጠራቸው ሰዎች መሃከል አንዱን ይዘን ቀርበናል። አቶ ገብረየስ ቱና ይባላሉ። ሲልቨር ስፕሪንግ አካባቢ አበሾች የሚያዘወትሩብት ቤት ብቅ ለሚል ሰው አዲስ እንግዳ ላይሆኑ ይችላል።

በአየር ኃይል ረዘም ላለ ጊዜ በተለያየ ክፍል ያገለገሉ ሰው ናቸው። ከዝቅተኛ ስራ መደብ በመነሳት የአንድ ክፍል ኃላፊ እስከመሆን ደርሰዋል። የግል ታሪካቸውንና ገጠመኞቻቸውን እንዲያወጉን ጠይቀናቸው ፈቃደኛ ሆነው ከአቶ ገብረየስ ቱና ጋር ለመገናኘት በሲልቨር ስፕሪንግ አካባቢ ወደ ሚያዘወትሩበት ካፌቴሪያ አመራሁ። ከቀጠሯችን ሰዓት ቀደም ብለው በቦታው ተገኝተዋል። ጨዋታ አዋቂ፣ ሰው ወዳድና ተግባቢ ስለሆኑ ይመስለኛል ምንጊዜም ቢሆን እሳቸው በተቀመጡበት ጠረጴዛ ዙሪያ ታዳሚ አይጠፋም።

ዛሬም ብቻቸውን አልነበሩም። ሁለት ወጣቶች አብረዋቸው ተቀምጠው ያወጋሉ። ከተቀመጡበት ተነስተው ልባዊ በሆነ ፈገግታ ተቀበሉኝ። ቁመታቸው ረዥም ሰውነታቸው ደልዳላ ሲሆን ብርማ ፀጉራቸው አሁንም ግንበራቸው ድረስ ግጥም እንዳለ ነው።

አቶ ገብረየስ ቱና መሰረታቸው የገበሬ ቤተሰብ ነው። የተወለዱት በ1938 ዓ/ም ከአባታቸው ከአቶ ቱና ጎበና እና ከእናታቸው ከወ/ሮ በሪቴ ባቴ በአርሲ ክፍለሃገር አርባጉጉ አውራጃ፣ አሰኮ ወረዳ፣ በርኬ በተባለ ቀበሌ ሲሆን የቄስ ትምህርትም የወሰዱት እዚያው በተወለዱበት አካባቢ በመድኃኒ አለም ቤተ ክርስቲያን ነው።

ዘመናዊ ትምህርት ለመከታተል ግን የቄስ ትምህርታቸውን ማቋረጥ ነበረባቸው። ዘመናዊ ትምህርቱን ለማግኘትም ጉና ዘመድ ወደ አለበት ወደ ጉና ከተማ ይሄዳሉ። ትምህርታቸውን ለመከታተል። ጉና ስምንተኛ ክፍል እንዳጠናቀቁም ወደ አቦምሳ በመሄድ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ጨረሱ።

አቦምሳ የነበረ የአንድ ጓደኛቸው አባት በወቅቱ የፓርላማ ተመራጭ በመሆን ወደ አዲስ አበባ መሄድ ለወጣቱ ገብረየስ መልካም ዕድልን አመቻቸ። ጓደኛቸው ከአባቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ እሳቸውም አቦምሳን የኋሊት ጥለው ከጓደኛቸው ጋር 1954 ላይ አዲስ አበባ ገቡ ።

አዲስ አበባ እንደደረሱም ኢዮቤልዩ ቤተመንግስት ውስጥ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ከነበሩት ከኮሎኔል ፍላቴ ቤት ይቀመጡና ቴሌ ኮምዩኒኬሽን ላወጣው ክፍት የስራ ቦታ ተወዳድረው ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ በማለፍቸው ይቀጠራሉ።

በዚያው ስራ በመከላከያ ምኒስትር ውስጥ ተመድበው ጥቂት እንዳገለገሉ ወደ ደብረ ዘይት ይቀየራሉ። ያን ጊዜ ነው አቶ ገብረየስ ለዘመናት ያገለገሉበትን የአየር ኃይል በር ያንኳኩት።

ደብረዘይት ሄደው ብዙም ሳይቆዩ አየር ኃይል የተላላኪነት የስራ ማስታወቂያ በማውጣቱ ለዚሁ ስራ ተወዳድረው ያልፋሉ። ተፈላጊውን መመዘኛም ያሟሉና ህዳር 3 ቀን 1956 አየር ኃይል በተላላኪነት ይቀጠራሉ ።

በአየር ኃይል የመጀመሪያው የስራ መደባቸው የአየር ኃይል ዘመቻ መምሪያ (ኮማንድ ፖስት) ውስጥ ነበር። በዚያ ወቅት የዘመቻ ኃላፊ የነበሩት ጄኔራል አሰፋ ገ/እግዚ ነበሩ ። ይህ የተቀጠሩበት የስራ መደብ ስሙ ዝቅተኛ ቢመስልም ከፍተኛ ወታደራዊ ምስጢሮች እና ሰነዶችን በሃላፊነት እና በጥንቃቄ መያዝን የሚጠይቅ በመሆኑ በሰራዊቱ ውስጥ የተዋቀረው የወታደራዊ ደህንነት የቅርብ ክትትል ያደርግባቸዋል ። እጃቸው የሚገባውን ምንኛውንም ሚስጥራዊ ሰነዶች በጥንቃቄና በታማኝንት ይይዙ እንደነበረም ቅርበው ይመለከቷቸዋል ። ታዲይ በማንኛውም ጊዜ ፈተናውን ወድቀው አያውቁም ነበርና የበለጠ ዕምነት ተጥሎባቸው በክፍሉ ውስጥ የሚመጡ የስልክ ጥሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ እንዲመልሱ የፈቀድላቸዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ ለአንድ አመት ካገለገሉ በኋላ በደረጃ ዕድገት ወደ አየር ኃይል ማተሚያ ቤት ይዛወራሉ። ማተሚያ ቤቱ ከተለያዩ ቅፆች አንስቶ የትምህርት መርጃ መጽሐፎችችን ፤ መፅሔቶችንና ማስታወቂያ የመሳሰሉትን ሁሉ የማተም እና የመጠረዝ አገልግሎትን የሚሰጥ በሃገሪቱ ከነበሩት ማንኛውም ማተሚያ ቤቶች የተስተካከለ እና ዘመናዊ ማተሚያ ቤት እንደነበር ነው አቶ ገብረየስ የሚያስታውሱት።

በወቅቱ የማተሚያ ቤቱ ኃላፊ የነበሩት ኮሎኔል ጥበበ በአገልግሎታቸው ያሳዩትን መልካም ስነ-ምግባርና እና ስራ ወዳድነት በመጥቀስ ከነበሩበት ዝቅተኛ ክፍያ ያለ ተወዳዳሪ ዕድገት እንዲሰጣቸው ለአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ የሰው ኃይል አስተዳደር (ፐርሶኔል) ለኮሎኔል ታደሠ ተድላ ደብዳቤ ጽፈው በመጠየቃቸው ከማተሚያ ቤት ተነስተው በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ መዝገብ ቤት ውስጥ የመደባሉ።

እዚያም አንድ ዓመት ያህል ካገለገሉ በኋላ ለገንዘብ ያዥነት በውስጥ ለወጣ ክፍት የስራ ቦታ ተወዳድረው፣ በተሰጠው ፈተና ከተፈታኞች መሃከል አንደኛ በመውጣት በሶስተኛው አየር ምድብ ድሬዳዋ በገንዘብ ያዥነት ተመድበው ለረዥም ዓመታት ያገለግላሉ ።

ያን ጊዜ የአየር ኃይል ደምዎዝ አከፋፈል በቼክ በመሆኑ ለአሰራር አመቼ ነበር። ይሁን እንጂ አየር መከላከያ ከተቋቋመ በኋላ ለአየር መከላከያ ሠራዊት ደምዎዝ የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ ስለነበር አልፎአልፎ ጉድለት ይታይ ነበር። ለዚያ መሸፈኛ የሚሆን ምንም አይነት ማካካሻ ባለመኖሩም ችግር ይገጥማቸው ነበር ።

በወቅቱ የአየር ኃይል አዛዥ የነበሩትን ሜጀር ጀኔራል ፋንታ በላይ በተለያየ አጋጣሚ ያውቋቸው ነበር። እናም አንድ ቀን ድሬዳዋ ራስ ሆቴል አገኝተዋቸው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ሰለስራ ይጠይቋቸዋል። እሳቸውም ሰለአየር መከላከያ የገንዘብ አከፋፈል የገጠማቸውን የአሰራር ችግር ይገልጹና የተሻለ በታ ቢመደቡ እንደሚወዱ ይነግሯቸዋል።

ጀኔራል ፋንታም የክፍል አለቃቸው ደብዳቤ ጽፎ እንዲልክ እንዲነግሩት ያዟቸዋል። አለቃቸውምትእዛዙ እንደደረሰው ግለሰቡ በእስካሁን አገልግሎቱ ምንም አይነት ዕድገት ያላለፈው ስለሆነ ሌላ ዕድገት ጊዜውን ጠብቆ ያገኛል፣ አሁን ዕድገት ቢሰጠው የአየር ኃይልን የውስጥ አሰራር የሚያዛባ በመሆኑ ወደፊት ይጠብቅ የሚል ደብዳቤ ሰለጻፈ ሁሉም ነገር እዚያው ላይ ቆመ።

አቶ ገብረየስ በአየር ኃይል ገንዘብ ቤት ስራ ላይ ካጋጠማቸውና የማይረሱት ነገር ቢኖር አንድ ጊዜ የካዝና ቁልፍ አልከፈት በማለቱ ከደብረ ዘይት (ሐረር ሜዳ) ከወታደራዊ ደሕንነት ፤ ከማሽን ሾፕ ፤ ከዋናው ገንዘብ ቤት ኦዲተሮች በአጠቃላይ አስፈላጊ የተባሉ ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች አልከፈት ያለውን ካዝና ለመመርመር የመጡበትን ጊዜ ነው።

ከሐረር ሜዳ የመጣው ቡድን የምድቡን ባለሙያዎች ጨምሮ ካዝናውን ማሽን ሾፕ በመውሰድ ለመክፈት ብዙ ሰዓት ይፈጅበታል። ለሻይ እረፍት ሲሄዱ አቶ ገብረየስም ቁልፉን በመያዝ ለሻይ እረፍት ይሄዳሉ። በኋላ ካዝናው ሲከፈት ምንም አይነት ጉድለትም ሆነ ብክነት ሳይገኝ ይቀራል። በዝሁ ምክንያት እሳቸውም ከቡድኑ ከፍ ያለ ምስጋና አግኝተዋል።

ከዚህ በኋላ በሬጅሜንቱ አዛዥ ከገንዘብ ያዥነት ተነስተው በዋናው ሂሳብ ሹም ስር የሂሳብ ሰራተኛ ሆነው እንዲሰሩ ሆነው ይመደባሉ። ለተወሰኑ ዓመታት በዚሁ የስራ መደብ ካገለገሉ በኋላ የድሬዳዋ አየር ምድብ የሂሳብ ሹም በመሆን የመንግስት ለውጥ እስከ ተደረገበት 1983 ድረስ አገልግሎት ሰጥተዋል ።

ከመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ መከላከያ ምኒስትር ተጠርተው የሰራዊቱን ደምዎዝ አከፋፈልን በተመለከተ ዕቅድ እንዲያወጡ

ተደርጎ ከስምንት ቀናት በኋላ ስድስት ቡድን ወደ ምስራቅ ዕዝ ደምዎዝ ለመክፈል ይላካል። እሳቸውም ከቡድኑ ጋር ይጓዛሉ። እንደ ዕድል ሆኖ የዕጣ ድልድል ሲደረግ ደግሞ ድሬዳዋ ይደርሳቸዋል።

እዚያም ለጥቂት ጊዜ በደምዎዝ ከፋይነት ከቆዩ በኋላ ከመከላከያ ምኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ የምስራቅ ዕዝ በጀት ክፍል ዋና ኃላፊ ሆነው ለተከታታይ ሁለት ዓመታት ሲሰሩ ይቆዩና በማያውቁት ሁኔታ በቀድሞ አየር ኃይል ውስጥ ደህንነት ነበር በሚል ክስ ከሰራዊቱ እንዲሰናበቱ ይደረጋል።

ይሄ ለአቶ ገብረየስ ትልቅ ዱብ እዳ ነበር። እሳቸው እንደሚሉት የደህንነት አባል ሆነው አያውቁምና። ክሱን ግን አሜን ብለው ተቀብለው ቁጭ አላሉም።ወደሚመለከተው ክፍል በመሄድ የደህንነት አባል ሆነው እንደማያውቁ በመግለጽ በወቅቱ የፖሊስ ኮሚሽነር ከነበሩት በተፃፈ ደብዳቤ ስማቸውን አስጠብቀዋል።

አቶ ገብረየስ የሶማሌ ወራሪ ኃይል ድሬዳዋን ሊያጠቃ በተቃረበበት ወቅት እዚያው ነበሩ። ከሰራዊቱ ጎን ቆሞ ወረራውን ለምቋቋምም ከሌሎች ሲቪል ሠራተኞች ጋር ከምስራቅ ዕዝ በመጡ የሠራዊቱ አባሎች ወታደራዊ ስልጠና ወስደዋል።

ጦርነቱ እየገፋ በመምጣቱ ከድሬዳዋ ተነስቶ የጠላትን ኃይል ለመደምሰስ የማያመች ከመሆኑም ሌላ የአየሩ ሁኔታም እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ በፊት ተዋጊም ሆኑ ሌሎች አውሮፕላኖች በሙሉ ወደ ሐረር ሜዳ አየር ጣቢያ በርረው እንዲሄዱ ይደረጋል ። ይህ በሆነ በማግስቱ የሶማሊያ ሰራዊት ኃይሉን አጠናክሮ በከባድ መሳሪያ አየር ማረፊያውን ይደበድባል። በዚህ መሃል ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሆነ በይንግ አውሮፕላን ያርፍና አብራሪዎቹ የነበረውን ሁኔታ ባለመረዳት ይሁን በሌላ ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ ወደ ሆቴላቸው ይሄዳሉ።

የከባድ መሳሪያው ጥቃት እንደገና ከመቀጠሉ በፊት ግን እሳቸውና ማስተር ቴክኒሺያን ተካልኝ ጋሻው ወደ ራስ ሆቴል በመሄድ የአውሮፕላኑን አብራሪዎችና ሰራተኞች ይዘው ይመለሳሉ።እነረሱም ሳይደናገጡ በጣም በተቀላጠፈ ሁኔታ በግማሽ መንደርደሪያ ተነስተው ወደ አዲስ አበባ ለመብረር ችለዋል። እነ አቶ ገብረየስም ያንን በከፍተኛ ወጪ የተገዛ አዲስ ዘመናዊ አውሮፕላን በጠላት መድፍከመመታት በማትረፋቸው የአብዮታዊ ሰራዊት የዘማች አርማ ተሸልመዋል ።

ይህ በሆነ በማግስቱ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አውሮፕላኖች መጥተው የጠላትን ታንክ እና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ዶግ አመድ በማድረግ የተረፈውም በመጣበት እንዲመለስ አድርገዋል። የሶማሊያ ታንኮች የተመቱት ከላይ መሃል ለመሃል በመሆኑ የአብራሪዎቹንኢላማ የመምታት ችሎታ ከፈተኛ ለመሆኑ አቶ ገብርየስ የዓይን ምስክር ናቸው።

አቶ ገብረየስ ደሬዳዋን ከተማን በጣም ከሚወዱ ሰዎች መሃከል አንዱ ናቸው። የፍቅር ከተማ ይሏታል። አየር ምድቡም እንዲሁ ነው። እንደ ከተማው ሕዝብ ሠራዊቱም እንግዳ ተቀባይ ነው። እርስ በእርሱም ሲፋቀር የኖረ ነው። በስራ ላይ ካልሆነ በስተቀር ማን ሲቪል ማን መለዮ ለባሽ የሚል ልዩነት አልነበረም። ለእሳቸው የአየር ኃይል አባላት መልካምነት ከምንም በላይ አይዘነጋም።

በውይይታችን መገባደጃ ላይ አንድ ሳይጠቅሱት ማለፍ ያልፈለጉትን ታሪክ እንዲህ አጫውተውናል።

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን አየር ኃይል በአይነቱ ልዩ የሆነ የአየር ላይ ትእይንት ተዘጋጅቶ ለህዝብ ቀርቦ ነበር። በወቅቱ የኬንያ የመጀመሪያው ፕሬዘዳንት ጆሞ ኬንያታ በክብር እንግድነት ተገኝተው ይህንን በአፍሪካ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን ትእይንት ለማየት በቅተዋል። ከትእይንቱ አንዱ ኢላማን በትክክል መምታት ነበር። ሁሉም ኢላማዎች በትክክል በመመታታቸው በርካቶች ተደነቁ። ነገርግን ከፊሎች ኢላማው የተመታውም ሆነ የአየር ትእይንቱ የተደረገው በኢትዮጵያውያን እንዳልሆነ በመጠራጠራቸው በሌላ ቀን እዲደገም ይወሰናል። ሁሉም ነገር ተደግሞ ለሕዝብ ከቀረበ በኋላ አውሮፕላኖቹ ሲመለሱ ካኖፒያቸውን በመክፈት የሄልሜት ቫይዘር (የፀሐይ መከለያቸውን) ከፊታቸው ላይ በማንሳት ትክክለኛ ማንነታቸው እንዲታይ በማድረግ ትርኢቱ የተከናወነው በኢትዮጵያውያን መሆኑን እንዲረጋገጥ ተደርጓል።

በሌላ አጋጣሚ ደግሞ አንድ የአየር ኃይል ከፍተኛ መኮንን ከበረራ ሲመለሱ ወደ ላውንጅ ከመግባታቸው በፊት አንድ በአየር ላይ የነበረ አውሮፕላን ድምጹን በመስማት ብቻ አውሮፕላኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳልሆነ በማወቃቸው ይህ አውሮፕላን ወርዶ ቢስተካከል ጥሩ ነው ሲሉ ሰምተዋል። ይህ ለአቶ ገበርየስ ትርጉም ነበረው። አብራሪዎቹ አውሮፕላን ማብረር ብቻ ሳይሆን አውሮፕላኑ ያለበትን የቴክኒክ ሁኔታ መሬት ላይ ሆኖ ማወቅ ይችሉ ነበር።

አቶ ገብረየስ አየር ኃይል በነበሩበት ዘመን የነበራቸው ገጠመኞችብዙናቸው።

በቅርቡ በሞት የተለዩን ብ/ጄኔራል ለገሰ ተፈራን በተለይ ያስታውሳሉ። ከሐረር አካዳሚ ወደ አየር ኃይል ከተዛወሩበት ጊዜ ጀምሮ መልካም ቅርርብ ነበራቸው። በየሰምንቱ መጨረሻ ሆራ ሐይቅ ለዋና ይገናኙ ነበር። በዚህም የተነሳ ምን አይነት ሰው እንደሆኑ ለማወቅ ችለዋል።

የሶማሊያ ጦርነት ከመጀመሩ ቀደም በሎ ከስራ በፊት ተገናኝተው የተጫወቱትን ያስታውሳሉ። "ይሄን ጦርነት እንዴት ማሸነፍ የምንችል ይመስልኸል?"በማለት ለጠየቋቸው ጥያቄ የመለሱላቸው "እንግዲህ አርባ ሚግ እና አስር ኢፍ-5... እስቲ እናያለን" በማለት ነበር ። ሙያ በልብ እንዲሉ ሁላችንም እንደምናውቀው በዚያ ጦርነት ዋና ተዋናይ እንደነበሩ እናስታውሳለን።

ሌላው የኪዩባ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብና ሰራዊት ጎን በመቆም ብዙ የሕይወት መስዋእትነትን መክፈሉን አቶ ገብረየስ በሚገባ ያስታውሳሉ። ያደንቃሉም።

አንድ ቀን ከኪዩባውያኑ አብራሪዎች መሃከል አንዱ ያበረው የነበረው አውሮፕላን ክፉኛ ተመትቶ ወደ አየር ማረፊያው ተቃርቦ ለማረፍ ሲሞክር መንደርደሪያውን ጨርሶ ተንሸራቶ ከአሸዋ ውስጥ ይቆማል። የአብራሪውን ሕይወት ለማትረፍ ብዙዎች ወደ ስፍራው በሩጫ ይሄዳሉ። እሳቸውንም ጨምሮ። አብራሪው ግን ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስበት ከአውሮፕላኑ ይወጣል። የድንጋጤም ይሁን የመረበሽ ስሜት ግን ከቶም አይታይበት ነበር ። አቶ ገብረየስ በረጅሙ የአየር ኃይል አገልግሎታቸው ይህ ነው የማይባል የሕይወት ልምድ አካብተዋል። እንደሚሉት ከሆነ ዛሬም እንደ ድሮው ከቤታቸው ይልቅ አየር ኃይልን አብልጠው ይወዳሉ። ባሳለፉት የሕይወት ጉዟቸው አብረውኝ ከጎኔ ቆመው የነበሩ የአየር ኃይል የሲቪል ሰራተኞችንም ሆነ መለዮ ለባሾችን ሁሉ የምወደው ዘመን በማይለውጠው ወንድማዊነት ነው ይላሉ።

አቶ ገብረየስ ታሪካቸውን ፈቃደኛ ሆነው ስላካፈሉን ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው ። ረዥም ዕድሜና ጤናም እንመኝላቸዋለን።

---------------------////--------------------

The power of

UNITY &

TOGETHERNESS

From J/Tech's Dossier

Sports in Former Ethiopian Air Force (part-1)

J/Tech Assefa Abebe

J/Tech Assefa Abebe is an advocate of our children who don't read and write in Amharic. That is why he chooses to write his articles in English. He wants our children read and understand the history of Ethiopian Air Force. In this article he takes us back to one of the stories of Air Force soccer team known as "NEB"



ጁ/ቴክ አሰፋ አበበ

A story from Soccer game in the Imperial Ethiopian Air Force history(1962-1972)

The Ethiopian Air Force Soccer team known as NEB was made up of the following players. Those were the trail blazers who elevated the game of soccer and led the team into the final championship match against the most experienced and popular St George team that we all grew up idolizing.

1. Lt. Zeleke (Army Aviation), 2. M/Tech. Feleke Habte, 3. M/Tech. Denbu W/ Senbet, 4. M/Tech. Ejigu Zenebe, 5. M/Tech. Tekola Astatke, 6. M/Tech. Demissie Mekonnen 7. M/Tech. Wondimu Demissie, 8. M/Tech. Michael G/Tatios, 9. M/Tech. Wondimu Ayele, 10. M/Tech. Engida Malde, 11. M/Tech. Beyene Berhe, 12. M/Tech Gebrehiwot Zemikael, and 13. Ato Kiros (civilian employee)

*Here it is worth to remember that **M/Tech. Engida Malde**, although he was part of the Air Force team's roster, on this occasion he did not play the game instead he sat out. As he told me, a few days ago, he just returned from the United States of America, after completing the training he was sent to study and that did not give him ample time to practice with the team. The Early 1960's was a time when the young energetic, fast running, and hard striking Air Force soccer team known as NEB for the first time in the history of soccer game had become a force to be reckoned with against the St. George team. Everyone knew that St. George soccer team was a well established, well experienced, and highly formidable team whose name was synonymous with soccer dynasty, and highly liked by most Ethiopians because of its popularity in winning numerous games.*

The day they played against the NEB team, like any other winning and popular team elsewhere the St. George team entered the stadium with arrogance and impatience looking down on the NEB team as a new kid on the block, ready to be taught a lesson that they would never forget for years to come. They thought playing the fast running and hard striking Air Force team, was going to be a cake walk for them. Unfortunately the new kids on the block were not strangers to the block, when it came to playing the game of soccer. Instead the NEB team arrived on the block as a new sheriff in town ready and prepared to enforce the law by any means, even if it had to come to chasing out the trouble makers out of the block.

It was a highly anticipated and highly talked about soccer match of the decade. The people of Debre Zeit and the whole members of the Air Force personnel went to the stadium to root for the NEB team. The stadium was filled to its capacity and the supporters of St. George team out numbered the supporters of the NEB team. The spectators were chanting and whistling to encourage their own team members. After high dignitaries and government officials had arrived and took their seats, the players lined up and took their positions to start the show down that was considered to be the biggest game of the decade between the two titans.

NIB football team

The referee blew the whistle and the game started. The St. George team although known for its winning streaks in the past this time they couldn't, because the NEB team's ***defence was impregnable****, the* ***attack was lethal****, and the* ***goal keeper*** *was phenomenal and* ***leaping like a projectile*** *not allowing any thing to pass through his fingers.*

The NEB team armed with such a high quality of defence and attack agility had managed to score the first goal and led ***1-0.*** *Such a quick lead in score had helped to quiet down the ear deafening noise made by St. George supporters, and at the same time it energized its own supporters. The St. George team tried everything they could to break the impasse but they couldn't overcome the psychological fear they were going through. As the game continued with the other side still not able to score no matter how hard they tried the NEB team again scored the second goal and led 2-0. The second goal decimated their egos and sent a shock wave of fear, and anxiety down the spine of St. George's team.*

The tide seemed to have turned against the St. George team. The Air Force team who came on the block as a new sheriff in town had certainly proved who they were in accomplishing their mission impossible game with finesse, against the more experienced, talented , and well liked St .George team.

The NEB team accomplished what other team was unable to do. ***They simply shattered the 1960's long standing myth of St. George's team of invincibility by trouncing them 2 to 0.*** *Thus St. George which was synonymous with soccer dynasty for many years with its winning streak seemed to have come to* ***a screeching halt****.*

The fast and powerful Air Force's NEB team became a force to be reckoned with, for the remaining minutes of playing time left on the clock. The clock was ticking down and the game became an upward hill battle for St. George team.They started feeling butterflies in their stomach and ran out of steam.They were caught between a rock and deep blue sea. Thus their era of superiority in playing and winning soccer game was about to eclipse their hopes, and crumble into pieces like a building hit with explosive dynamites by the arrival of a new kid (NEB) on the block.

St. George team had something up in their sleeve, being a seasoned team comprised of many talented individuals recruited from all walks of life, might try to ***pull their dirty tricks*** *with the* ***help of the referee*** *to change the game's dynamics to upset the NEB team.*

At one instance one of St .George's players was tackled outside of the ***penalty encroachment arc****, and purposely jumped inside into the penalty zone and started rolling over several times holding his leg up to make it look like he was hit inside the penalty zone. This type of foul opened up a perfect door of*

opportunity for the referee who was also an ardent supporter of the St. George team. Instead of allowing a penalty kick from outside of the encroachment arc, he gave them a ***free penalty kick from the penalty mark.***

Now St. George scored their first goal with the help of the referee and now trailing 1- 2. Such a broad day light favoritism was a vindication by the NEB team to suspect that the referee was against them all the way from the beginning until then. Such lack of impartiality towards them did not sit well with the Air Force team. Having realized the referee's biased attitude towards them, they tried their very best to avoid any minor contacts. As usual one of the star players of St. George team pulled his second dirty trick and the referee gave them another free ***penalty kick*** *out of the blue.*

Now the score is tied 2-2, and this time temper flared up among Air Force players. The St. George team and the referee were deliberately working hand in glove and continued to mess around with the nest of the honey bee.

The collusion between the referee's hands off approach when it came to the rough playing techniques of St. George team, provoked the bees to come out of its bee hive and started stinging the referee and the players of the St. George team one after another. The first bee sting landed on the chin of the referee by none other than ***M/tech. Feleke Habte****, who knocked him down cold to the ground. The fight broke out and the bees continued stinging them with head butts, punches, and kicks that turned the court into into a mini- battle field.*

The referee was carried out of the field and the game stopped in a tie without a winner.

One thing the readers have to understand is most of the officials who were running the Ethiopian Foot Ball Federation at that time were ones former players of the St. George team, and understandable what the ramification of the result of this game would look like.

After few days of deliberation as expected the foot ball federation having carefully analyzed its post mortem evaluation of the game they were absolutely convinced that the St. George team couldn't win against the fast and powerful NEB team even if a rematch was scheduled. Therefore they scrapped out the rematch and used every incident that took place in the game to their disposal to preserve the reputation of the St. George's team and declared them the winner of the game by forfeit. ***Surprises!!! (a kangaroo-court verdict.)***

M/tech Hagos Desta

The well known air force football coach

However a heavy penalty was also imposed on the Air Force team. M/tech. Feleke Habte who knocked down the referee was suspended for life not to ever play soccer game again. Adding insult to injury because of the altercation between the two teams the federation also passed a rule to protect its own darling team (St. George) from future defeats , injuries, and humiliation in the hands of the Air Force team kicked the NEB team out of the federation for ever once and for all. This means the Air Force team would never play against any civilian teams in the future again.

The travesty of justice imposed to severely penalize the fast running, hard striking, and impregnable

defense of the NEB team to be robbed of their talents at this crucial young age was a testament that the few officials who sat at the helm of the foot ball federation were biased, and lacking ethical and moral obligations to see beyond the tips of their nose. Those young players would some day could have become the star players representing the Ethiopian national team. Unfortunately their wings were clipped off by a scandalous, and corrupt referee and foot ball federation officials at this young tender age so they couldn't sore high to the top of the mountain where they would have aimed to reach.

Therefore the lack of impartiality by the referees and the propensity of officials to side only with a certain team would be a recipe for the decline of soccer games, and a disaster to other sports activities in Ethiopia for many years to come. Over the years most of the early 1960's NEB team was replaced by the following players. ***Unfortunately their group picture is not available, except for few of them.***

The 1st Ethiopian nation Team

1. M/tech. Girmaye Teferi (Aba-habesh),** 2. **M/tech. Yirgu G/ Selassie, 3. M/tech. Belay W/Gabriel, 4. M/tech. Esayas Negatu, 5. M/tech. Endale Tolessa, 6. M/tech. Kassa Tessema, 7. S/Acmn Eshetu Alemu, 8. M/tech. Eshetu G/Mariam, 9. M/tech. Desalegn G/Selassie, 10. M/tech. Petros Haile, 11. M/tech. Hagos Desta, 12. M/tech. Afework Bekele 13. M/tech. Alemayehu Ourgie.

<u>Note</u>: Everyone here is addressed with the last military rank they have attained while serving in the Air Force.

-------------////-------------

አበበ ተገኝ

አበበ ተገኝ

አምና

ከዳመና በላይ ከዳመና በታች
ያገሪቷን ታሪክ ሰማየ ሰማይ ላይ..
በክብር የፃፋችሁ፣
ድንበር ሰርሳሪውን
ክብር ደፋሪውን
ከውስጥ ፍልፈል ጋር
ሸር ሸራቢውን
ከፍ ዝቅ አርጋችሁ
ቁምስቅል ያሳያችሁ፣
በባለ ግርማው አርማ
ባንዲራው ጋሻችሁ
እንደ ጉግሳ ፈረስ
ጎበና አባ ጥጉ
ሚግና አንቶኖቭ ጄት የጋለባችሁ
በነጎድጓድ መብረቅ ባገሬ ሰማይ ላይ
ወራሪ ስድ ላይ ያጉረመረማችሁ
እንደ ኢያሪኮ የጠላትን ምሽግ
የደረመሳችሁ
ዝነኛው ያየር ኃይል ጡንቻ የነበራችሁ
የጠራርው መብረቅ
ገናናው ስማችሁ
ያየር ላይ ኢጋንንት
ጠላትን ያሸናችሁ
ይኸው እስከዛሬ
በየጦር አውድማው
ሲጨስ የሚኖረው
ባሩድ ጅራፋችሁ
እናንት የሰማይ ላይ ሽቅርቅር ኮከቦች
የኤርፎርሱ ግርማ
የብረት አለንጎች
ይኸው በተአምሩ ኢድሜና ሞገሱን
እንደለበሳችሁ
ዘመን ተሻጋግረን
ቶሮንቶ መድረክ ላይ ደግመን አየናችሁ::


DREAMS
" Some people follow their dreams, while others wake up and make them a reality."

1266